መዝገበ ታሪክ



ክፍል ፪

«ተዘከሩ መሪንቲክሙ ዘነገሩክሙ ቃለ እግዚአብሔር»
ዕብ 13:7

«የእግዚአብሔርን ቃል የነገሩአችሁን መምህሮቻችሁን አስቡ»
ዕብ 13:7

ከመምህር ኅሩይ ኤርምያስ
ጥቅምት 1995 ዓ.ም
አዲስ አበባ

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

ታህሳስ 2001 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አንደኛ ዕትም 1995 ዓ.ም
ሁለተኛ ዕትም 1997 ዓ.ም
ምስተኛ ዕትም 1999 ዓ.ም
አራተኛ ዕትም 2000 ዓ.ም
አምስተኛ ዕትም 2001 ዓ.ም
ስድስተኛ ዕትም 2004 ዓ.ም
ሰባተኛ ዕትም 2004 ዓ.ም
ስምንተኛ ዕትም 2005 ዓ.ም
ዘጠነኛ ዕትም 2006 ዓ.ም

ይህን መጽሐፍ በእቲላ አቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም በቅኔ መምህርነት ተመድቤ ላስተምር በ1988 ዓ.ም አዘጋጀሁት፤ በልዑል እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ በጥቅምት ወር 1995 ዓ.ም አሳተምሁት::

ማስታወሻነቱ

ከ46 ዓመታት በላይ ጉባዔ ሠርተው በማስተማር እያሉ ምሁራንን ለቅድስት ቤተክርስቲያን ላበረከቱት ለእኔም በመንፈስ ቅዱስ አባቴና መምህሬ ለሆኑት ታላቁ የቅኔ ምሁር ለከቡር መምህር መንግሥቱ ዘለዓለም ይሁንልኝ::

በመጽሐፉ ሙሉ ዝግጅት ላይ አስፈላጊውን ሙያዊ አስተያየት ለሰጡኝ የቅኔና የወንጌል መምህራን ለመምህር ዓምደ ወርቅ ደሴ እና መምህር ኢያሱ ገ/አልፋ፣ ለከፍል ፩ መጽሐፍ ሕትመትና እገዛ ላደረጉልኝ ለወንድሜ ፈቃዱ ገ/መልድና ለንግድ ማተሚያ ድርጅት ኃላፊዎች እንዲሁም በማሥራጨት ለተባበሩኝ በሙሉ፡ አስተያየት ለለገሱኝ እና ይህን ጽሑፍ በኮምፒውተር በመጻፍ ለተባበሩኝ ለወ/ት ውበነሽ አዲሱ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

ተራ ቁ		አርእስት
1		መግቢያ
2	ምዕራፍ	1 መዝገበ ታሪክ ዘመጋቢት
3	"	2 መዝገበ ታሪክ ዘሚያዚያ
4	"	3 መዝገበ ታሪክ ዘግንቦት
5	"	4 መዝገበ ታሪክ ዘሰኔ
6	"	5 መዝገበ ታሪክ ዘሐምሌ
7	"	6 መዝገበ ታሪክ ዘነሐሴ
8	"	7 መዝገበ ታሪክ ዘጳጉሜን
9	የግዕዝ ቅኔያት	

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፡-

ክርስቶስ ኢየሱስ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በዕሪና የሚመሰገን፣ በዚህ ጊዜ ተገኘ በዚህ ጊዜ ያልፋል የማይባል በባሕርይ ሁሉን የሚያውቅ የሚመረምር እርሱ ግን የማይመረመር ሁሉን በከሀሊነቱ ያስገኘ ለርሱ ግን አስገኝ የሌለው ሁሉ በእርሱ የሆነ፣ ምንም ምን የሚላነው የሌለ ዓለማትን ፈጥሮ የሚገዛ፣ በኋለኛው ዘመን ሰውን በኃጢአት ምክንያት ኸት ቦታውን ልጅነት ክብሩን ያጣ ሰውን ወደ ቦታው ወደ ክብሩ ይመልሰው ዘንድ ከንጽሕት ድንግል ማርያም ፡ማይመረመር ግብር ሥጋና ነፍስን ተዋሕዶ በድንግልና ተወልዶ በፈቃዱ ሞትን ሞቶ በትንሣኤው ድል ነሥቶ ለዓለም ፍጹም ድኅነትን የሰጠ:: በክብር በምስጋና እንዳረገ እንዲሁ ለጻድቃን ሊፈርድላቸው በኃጥአን ሊፈርዳባቸው በግርማ መለኮት በይባቤ መላእክት ዳግመኛ የሚመጣ ለኅልፈት የተፈጠረውን የሚያላልፍ ለኅልፈት ያልተፈጠረውን በትንሣኤ የሚያጸና የጌቶች ጌታ የንጉሦች ንጉሥ፣ የአግልክት አምላክ ገብሬ ፍጥረታት /ዮሐ 1:1፣14፣ ዮሐ፡ 7:24፣ ሐዋ 1:11 ቆላ 1:14 20፣ዮሐ 5:20/ መሆኑን የምታሳውቅ የምታስረዳ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተገኘች እውነተኛና ቀጥተኛ ሃይማኖት ናት::

ይህች ሃይማኖት ለሰው ልጆች ድኅነት /ሕይወት/ መሠረት ናት:: ስለዚህም ክርስቶስ መሠረታት ነቢያት ፲ትንቢት ሐዋርያት በሰብኮት ገለጣት፣ ሰማዕታት በዐላውያን ፊት መስክረው አንገታቸውን ለሰለት ሰውነታቸውን ለእሳት ሠጡላት፣ ጻድቃን ዓለምን ንቀው ራሳቹውን ክደው ተከተሉአት ተገዙላት/ ሊቃውንት ከመናፍቃን ተከራክሩላት መክራም ተቀበሉላት፣ አምን የነርሱ ቤዛነት ተዋሕዶን በአጋንንት በመናፍቃን ከመዋጥ ታደጋት:: ቤተክርስቲያን መክራውን ታግሠው ተቀብለው ይህችን ርትዕት ሃይማኖት ጠብቃ በማቆየትና ለተተኪ በማስተላለፍ ታላቅ ውለታ የዋሉ /በጎ ሥራ የሠሩ/ ነቢያት ሐዋርያትን ጻድቃን ሰማዕታትንና ሊቃውንትን ሁሌም ስታስባቸው በጎ ሥራቸውንም ስትመሰክርላቸው ትኖራለች::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከሐዋርያት ከሊቃውንት ሲያያዝ በመጣ ትምህርተ ሃይማኖትና ሥርዓት ላይ

በተለያየ መንገድ ትችት የሚያቀርቡ በተለይም እኒህን ራሳቸውን ለሃይማኖት አሳልፈው ዜሣ አድርገው የሠው ቅዱሳንን "ከበዝ" ማዘጋጀን የሚታሙ፣ ባይረዱትም ተቀብለናል የሚሉትን ወንጌልን በዘሀጲዎችና ከተመ ራማሪዎች የከሀደት መንጋጋ ከመቀረጣጠፍ ታድገው ያቆዩላቸውን ባለውለታዎቻቸውን መዘንጋታቸው ግልጽ ነው። በሃይማኖትና በበጎ ምግባር አርአያ የሚሆኑ ቅዱሳን ሃይማኖታቸውና በጎ ምግባራቸው ወንጌል በተንገረበት ሁሉ ለንጥረላቸው ሊመሰክርላቸው እንደሚገባ ጌታ ክርስቶስ ሊየሱስ እማን እብለክሙ በገበተሰበበ ዝ ወንጌል በውስተ ኩሉ

ዓለም ያንብቡ ላቲ ዘገብረት ላቲ ብእሲት መይዝዘርኖ እውነት እላችኃለሁ። በዓለሙ ሁሉ ይህ ወንጌል በተሰበከ በት ቦታ ይህች ሴት ያደረገችውን ይናገሩ ያስቡአት ማቁ 26:13 ሲል ማርያም እንተ ዕፍረት ቸቱ በቀባችው ጊዜ ለሐዋርያት የተናገረውን፡ ቅዱስ ጳውሎስም መምህርቻችሁንን አስቡ ዕብ 13:7 ያለውን ሳያነቡ ቀርተው ከሆነ ወንጌሉን ተሸክሞ ለመዝር እንጂ አንቦ ለመጠቀም ባለመታደላቸው 'የተሜነችውን አትበላም...' እንደተባለው ሆኑ ግለት ነው እጅግ ያሳዝናል። አንበውት ከሆነም እነርሱ ሊፈጽሙት ባለመቻላቸው ቁና ሙሉ ትኖት አድርባቸዋል ማለት ነው። ለማንኛውም የቤተክርስቲያን ሥርዓቷ ምንም የማይመጣለት ተገቢና እሙነኛ መሆኑን ሊረዱት ይገባል።

የዚህም መጽሐፍ ዓላማ ቤተክርስቲያን በሃይማኖትና በፀጋምግራቸው የምታስባቸውንና እንደ ወንጌሉም ታል ገደሳቸውን የምትመስክርላቸውን ቅዱሳንና ዘዓላቸውን "ግስታሠት ነው። ኪመስከረም ! የኩቲት 30 ቀን ድረስ ባሉት ዕለታት በዓል ተሠርቶላቸው የሚታሰቡትን ቅዱሳን እንዲሁም የጌታ፣ የእመቤታችንና የመላእክት በዓላት ታሪክ «መዘገበ ታሪክ ክፍል ፩» በሚል ርእስ ከዚህ በፊት ታትሞ መሠራጨቱ ይታወሳል። ይህም የዚያ ሁለተኛ /ቀጣይ/ ክፍል ሆኖ ከመጋቢት 1 ጸጉሜን 5 ቀን ድረስ ባሉት ዕለታት የሚከሰሩትን የያዘ ነው ክፍል 1 መጽሐፉን ያንበቡ ምእመናን ታሪኩ የተፈፀመበት ዘመን እንዲኖተት በጠየቁት መሠረት ከዚህ መጽሐፍ በስተመጨረሻ በተዘረዘሩ መጻሕፍት የቤኔት ሬቲቱን ዘመኑን እያካተትኩ በድጋሚ ጽፈዋለሁ። የክፍል 1 ታሪኩች በመንም በዚህ መጽሐፍ የመጨረሻ ገጽች ላይ ተገልጿል።

እንወን እንድናስተውለው የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁንልን።

አሜን።

ምዕራፍ 1

መጋቢት 5 ዕረፍቱ ለአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ

ሀገራቸው ንሂሣ (ግብጽ) ነው። አባታቸው ሰምዖን እናታቸው አቅሌስያ ይባላሉ። ልጅ አጥተው 30 ዘመን ሲያዝኑ ኖረዋል። አንድ ቀን አቅሌስያ ቤተእግዚአብሔር ገብታ ከስዕለ-ሥላሴ ሥር ወድቃ ስትማፀን "ንሥኢ ወልደ ዘይትሌዐል ቀርጉ አምኑነ ሰማዳ .. ክብሩ ከሰማይ ከፍታ የሚበልጥ ልጅ እንኪ ተቀበዪ" የሚል ድምጽ ሰማች። በዚህም መሠረት አባታችን መጋቢት 29 ቀን ተጸንሰው ታኅሳስ 29 ቀን ተወለዱ።

ዓይን በገለፁት ጊዜ ከሚታይ ነገር ላይ እንዲያርፍ እርሳቸውም በተወለዱ ጊዜ እፈፍ ብለው ተንሥተው "ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ዘአውጻእከኒ እምጽ ልመት ውስተ ብርሃን» ብለው በማመስገናቸውና ጓላም ምድራዊ መብል መጠጥ ሳይመገቡ ሳይጠጡ ለምስጋና ተግተው በመኖራቸው መላእክትን ይመስላሉ።

ሦስት ዓመት ሲሆናቸው ቅዱስ ገብርኤል ከእመቤታችንና በግኑት ካሉ ቅዱሳን ዘንድ አስባርኮ ገዳማውያን ካሉበት ምኔት ወሰዶ ከበሩ አኖራቸው። አበምኔቱ አባ ዘመደብርሃን ምልክት ተነግሮት ቢሄድ ናሁ ሐ ገጽ ሆነው አግኝቷቸዋል። አሳድጎ አስተምሮ ከመግርግ ምንኩስና አድርሷቸዋል። ከዚህ በኋላ ሀብተሥውስ ተሰጥቷቸዋል። ባንድ ቀን እልፍ ዕውራን ህንካሳን ፈውሰዋል። ጓላ ግን ኤጲስ ቆጳሳቱ ካህናቱ ዝናቸውን ሰምተው እየመጡ ግብር የሚያስፈጽቸው ቢሆን ቅዱስ ገብርኤል በስንፋ ነጥቆ ከጌታ ፊት አቁረባቸው። በገድልህ በትሩፋትህ ከሞተ ነፍስ ከርደተ ገሃነም የሚድኑ ብዙ ነፍሳት አሉና ከሰው ተለይተህ ወደ ሜካ ግባ። ኑሮህም ከ60 አናብስትና ከ60 አናምርት ጋር ይሁን አላቸው። ጌታዬ ምን ተመግበው ይኖራሉ? አሉት። "ከኬድከ እበለ-እገረከ ይልሕሱ ወበውእቱ ይጸግቡ .. የረገጥከውን ትቢያ ልሰው ያው ምግብ ሆኗቸው ይኖራሉ" ብሏቸው ውሳጤ ገዳም ገብተው ከአናብስትና አናምርት ጋር ይኖሩ ጀመር። ዳንኤል ከአናብስት ጉድጓድ በተጣለ ጊዜ አናብስቱ እንደ ድመት ከእግሩ በታች ሆነው እንደተኙ የሬገጡትን ትቢያ ይልሱ ይታዘዟቸውም ነበር።

በዚህ መልኩ 30 ዓመት ከቆዩ በኋላ ጌታ ባንድነት በሦስትነት ተገልጾ ምን ላደርግልህ ትሻለህ? አላቸው። መጀመሪያ ላሉበት መጻለይ ይገባልና የምድረ ገቢታን ሰዎች ማርልኝ አሉት። 3(ሺህ) ነጥአንን ከሲኦል አውጥቶ ገነት አግብቶላቸዋል። ከዚህ በኋላ

"ሑር ምድረ ኢትዮጵያ ወበህየኒ ሀለውነ ነፍሳት ዘታወጽአሙ .. ወደ ኢትዮጵያ ሂድ" አላቸው። ቅዱስ ገብርኤል በሠረገላ ነፋስ ሄኖ ምድረ ከብድ አድርሷቸዋል። ዳግመኛም ወደ ዝቋላ (ደብር ቅዱስ) ወስዷቸው ከዚያ ሆነው በንጽሐ ልቡና የኢትዮጵያን ሕዝብ ኃጢአት አይተው ከባሕሩ በራሳቸው ቆመው ይጸልዩ ጀመር። አርባ ቀን ሲሆናቸው መልአኩ መጥቶ "ዘገብረ ተዝካረከ ወዘጸውዐ ስመከ እምሕር ለከ ብሎሀል" አላቸው። መላ ኢትዮጵያን ካልማረልኝ አልወጣም ብለው መቶ ዓመት ሲጸልዩ ኑረዋል። ከመቶ ዓመት በኋላ ጌታ "ተንሥእ ወጻእ መሐርኩ ለከ ኩሉ ኢትዮጵያ .. ምሬልሀለው ውጣ" ብሏቸው ወጥተዋል።

ከዚህ በኋላ ምድረ ከብድ ወርደው ከምድር በላይ ከሰማይ በታች ሆነው ሰባት ዓመት እንደ ትኩል ዓምድ ሆነው፡ ዓይናቸውን ሳይከድኑ ሰባት ዓመት ቆመው ጸልየዋል። ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ቁራ መስሎ መጥቶ ዓይናቸውን አንቁሮ አሳወራቸው። ሁለት ሱባዔ ሲፈጽሙ ቅዱስ ሚካኤልና ቅዱስ ገብርኤል መጥተው እፍ ብለው አድነዋቸዋል። ከዚያ ተነስተው ወደ ዝቋላ ሲሄዱ ሥላሴን በአምሳለ አረጋውያን ከጥላ ሥር አርፈው አገኟቸው። በእግዚአብሔር ዙፋን ተማጽነናል አዝለህ አንድ አንድ ምዕራፍ ሸኘን አሏቸው። አዝለው ከሸኙአቸው በኋላ በአንድነት በሦስትነት ሆኖ ታያቸው፤ ደንግጠው ወደቁ። አንሥቶ ዝቋላ ወርደህ ጠላቶችህን ተበቀላቸው አላቸው። በዘነ መብረቅ ደርሰው ሰባቱን ሊቃነ መላዕክት አጋዥ አድርገው እልፍ አእላፍ አጋንንትን በመብረቅ አጠፉዋል።

አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ፣ አባ አንበሴ ዘሐዘሎ እና አባ ብንያም ዘግብጽ ዜናቸውን ሰምተው አናብስቶቻቸውን አስከትለው ሊጠይቋቸው መጡ። በሰባተኛው ቀን ተገለፁላቸው። አናብስቶቻቸው በርሳቸው አናብስት ተውጠው አዝነው ነበርና አናብስቶቻቸውን ጌታ ያዘዘላችሁ የእግሬን ትቢያ እንጂ ሥጋና ደም ነውን? ትፋ ብለው ካስተፏቸው በኋላ ቢባርኳቸው ተነሥተዋል እነርሱም ርኢነ መንክረ ኦ አባ እያሉ ተመልሰዋል።

ከዚህ በኋላ ወደ ምዕራብ ሀገር ወሰዳቸው። የጋረብ ንጉሥ በጣየታቱ ያደሩ አጋንንት ፈርተው ሲሸሹ ጣየታቱ ሲሰባበሩ አይቶ ሰውነታቸው የሐር ፈትል በመሰለ ፀጉር የተሸፈነ ነበርና አንተ ፀጉር ልብሱ ምንድር ነህ ሰው ነህን? አላቸው። አምን ሰማይና ምድርን በፈጠረ በኢየሱስ ክርስቶስ የማምን ሰው ነኝ አሉት። እይሁድ ሰቅለው በገደሉት ሰው ታምናለህን? አላቸው። አፍርበት መስሎህልን አንተም ብታምንበት የዘለዓለም ሕይወት ባገኘህበት ነበር አሉት። እሳት አንድዱና አቃጥሉት አለ። አነደዱ። ማንም ግድ ሳይላቸው

በፈቃዳቸው ከእሳቱ ገብተው ወጡ ከሠራዊቱ ብዙዎች አመን አሉ። ሰይፍ አስፈሯቸው። እርሳቸውንም ሊመታቸው ሲቃጣ መብረቅ ወርዶ ከነተከታዮቹ ፈጅቷቸዋል። ወዳያውም መላእክተ ጽልመት ነፍሶቻቸውን እጅ ሲያደርጉ አይተው ይህ ሁሉ በኔ ምክንያት አይደለምን? ብለው ከታላቅ ገደል እግራቸውን በገመድ አስረው ቁልቁል ተሰቀሉ። ሰይጣን ገመዱን በጠሰው። ቅዱስ ሚካኤል ተቀበላቸው። ተወኝ በራሴ ልቁም አሉት። በራሳቸው ቆመው በጥርሳቸው ደንጊያ ነክሰው 30 ዘመን አልቅሰዋል። ጌታ ምሬልሃለሁ ብሏቸው ደንጊያውን ሲጥሉት አራት ጥርሶቻቸው በደንጊያው ላይ ተተክለው ቀርተዋል።



በሌላ ጊዜ ሲመለሱ ጥርሶቻቸው በተተከሉበት ደንጊያ መዓዛው ደስ የሚያሰኝ የሸቱ እንጨት ደማቸው ከነጠበበትም ወደን በቅሉበት አግኝተዋል።

እንዲህ ለሰማዕ ዕውብ በሆነ ግብር 262 ዓመት በኢትዮጵያ ኖረው በ562 ዓመታቸው በተሰፋቸው ያመነውን በኪዳናቸው የተማፀነውን ጌታ ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ሊያርፃቸው ተስፋቸውን ተቀብለው በዚህ ዕለት - በዕለተ እሁድ ዐርፈዋል። መላእክት በአክናፈ እሳት ኢየሩሳሌም ወስደው በየማነ ምስዋዕ ቀብረዋቸዋል።

ገብረ መንፈስቅዱስ የአምላክ አገልጋይ
ለኢትዮጵያ ብርሃን ነህ ፀሐይ
አኖላበት አናምርት ሲታዘዙህ ኖሩ
የእግርህን ትቢያ ልሰው እያደሩ
ፈጣሪን በስምህ ብለተማፀኑ
ኃጥአን ከሲኦል ከገሃነም ዳኑ።

እንደሰማይ መልእክ በሆንም ኑሮህ
የአላም ልጅ ነህና አንተም ሞትን ሞትህ
ምስጋና ተሰላህህ ልብስህ የአምላክ ጸጋ
አንተን ለማወደስ ነፍሴ ሁሌም ትትጋ
የጻድቅ ሰው ጸሎት በነፍሰም በሥጋ
ታሰማለችና ለማያቋ ዋጋ።

ሮሜ 12:12 ፣ 15:30 ያዕ 5 :16

❖ ወደኢትዮጵያ የመጡት በቅዱስ ላሊበላ ዘመነ መንግሥት መሆኑ ስለሚታወቅ የነበሩት ከ9 - 14 ኛው ምዓ ድ/ል/ክ/ መሆኑ ነው።

መጋቢት 8 - ዕረፍቱ ለማትያስ ሐዋርያ

ማትያስ ማለት ምትክ ማለት ነው። ጌታ ካረገ በኋላ ሐዋርያት ሠቱ ሃያ ራሳቸውን ከእመቤታችን ጋር ሆነው በጽርሐ-ጽዮን ፡ በማርያም እመ ማርቆስ ቤት ፡ ለጸሎት ይተጉ ነበር። አንድ ቀን ቅዱስ ጴጥሮስ ከእኛ ጋር የነበረ አስቆሮታዊ ይሁዳ ዳዊት "ወይኩና መዋዕሊሁ ጎዳጠ ወጲመቶሂ ይንሣእ ባዕድ - ዘመናቱ ጥቂት ይሁኑ ሹመቱንም ሌላ ይውሰድ" መዝ 108÷8 ብሎ ትንቢት ተናግሯልና ከኛ ጋር ከሚተጉ ወንድሞች አንዱን መርጠን ይሾም አለ። ዮሴፍንና ማትያስን አቁመው እኛ ባወቅን ዮሴፍንና ማትያስን መርጠናል። እንተ እግዚኦ ግዕምረ ኩሉ ልብ አርኢ አሐደ እምእሉ ዘኀረይከ ዘይነሥአ ላዘቲ መልእክተ ጲመተ ሐዋርያት ዘኀ ደጋ ይሁዳ ይሑር ብሔሮ ... ኩሳሊት ያመላለሰውን ልብ ያሰበውን መርምረህ የምታውቅ ሆይ ይህችን የሐዋርያት ሹመት ገንዘብ የሚያደርጋትን ከእኒህ ከሁለቱ የመረጥከውን ግለጽልን "ብሎው ጸልየው ዕጣ ሲያጣጥሏቸው ለማትያስ ወጣ። የዚህ ጊዜ አሥራ ሁለተኛ ሐዋርያ ሆኖ ተቆጠረ። ሐዋ 1÷13 ፅ 20

ከበዓለ ሃምሳ በኋላ መዲናቸው ኢየሩሳሌምን ዓመት አስተምረው ዓለምን ተከፋፍለው ለማስተማር ዕጣ ሲጣጣሉ ለርሱ ሀገረ በላዕተ ሰብእ ደረሰው። በዚህ ሀገር ያሉ ሰዎች እንደ አራዊት ሥጋ

የሚመገቡ ነበሩ፤ ከአደባባያቸው ገብቶ ሲያስተምር ይዘው ዓይኑን አውጥተው እንደላም ጣር እየመገቡ ከዝግ ቤት አስቀመጡት። በ40 ቀን ዓይኑ ምድሩ ሲለወጥ አይተው ሲመገቡት ነው። ከዚህ አስቀድሞ ግን ጌታ ሐዋርያው እንድርያስን ልኮለት ዓይኑን ፈውሶት ከእስሩ ፈትቶት ወጥተው ሲያስተምሩ ሊጣሏቸው መጡ። ወደ ጌታ ቢያመልክቱ ውኃ እስከ አንገታቸው አጥለቀለቃቸው ጓላ ግን ጸልየው አድነዋቸው አምነው ተጠምቀዋል። ባሕርያቸውም ተመልሶላቸው እህል የሚመገቡ ሆነዋል። ከዚህም የበለጠ ቤተክርስቲያን አሳንጾ ተሳውሶት ዲያቆናትን ሾሞ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ደሙ ወልደ እግዚአብሔር የሚመግባቸው ሆኗል። "ከዊነ ማትያስ በላዕለ - እኩያን ጌረ፤ ሥጋ ወልድ ቅዱስ ሲሰዮሙ ወደሞ ከቡረ፤ ተወላጠ ሲሰይም ሎቱ ከመላህም ሣዕረ" እንዲል አርኬ።

ሠላሳ ዘመን ካስተማራቸው በኋላ ወንጌል ካልደረሰበት ለማሳረስ ደማስቆ ወረደ። አረማውያን በብረት አልጋ አስተኝተው ሃያ አራት ቀን እሳት ሲያነዱበት ቆይተዋል። እርሱ ግን ሰውነቱ አምሮ ገጹ ደምቆ ይገኝ ነበር። በዚህ አምነው ተጠምቀዋል። በመጨረሻም በይሁዳ ከተሞች እየተዘዋወረ አስተምሮ በዚህ ዕለት ዐረፈለም እርፏል።

ራሱን አዋርዶ ሰለወንጌል ከብር
ማትያስ እንደላም ተመገበ ሣር።
እንዲሸጋገሩ ከሞት ወደ ሕይወት
ተማሩ ቢላቸው የወንጌልን ትምህርት
እንደእህል ቀቀሉት እታመሰት በእሳት።
አዩ አለማወቅ ልብ ደንዳናነት!

አሕዛብ ተጋግዘው በግፍ ሲያሰቃዩት
ይጸልይ ነበረ እንዲያገኙ ምሕረት።
ከቃሙን በከፉ መመለስ ቀሳል
ቢከብድም መታገሥ ዋጋ ያሰጣል።
ግሰፍ በዋንት ውስጥ መከራን መታገሥ
ሞኝነት አይደለም መድኃኒት ነው ለነፍስ።

ሮሜ 12፡ 12 1 ቆሮ 4:12 2 ቆሮ 4:18

መጋቢት 10 - መስቀል

በዚህ ዕለት ጌታ የተሰቀለበት መስቀል በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ሰዎች አማካይነት ሁለት ጊዜ ከተቀበረበት ወጥቷል። መጀመሪያ በንግሥት ዕሌኒ ከኢየሩሳሌም፣ ሁለተኛ በንጉሥ ሕርቃል ከፋርስ ወጥቷል። "መበዛቲ ዕለት እንበለ ይዕዱ ጊሠመ፣ መስቀል ተረክበ እምዘተ ነብዐ ወገብረ ሰላመ፣ በኢየሩሳሌም ቅድመ ወበፋርስ ዳግመ" እንዲል አርኬ።

የኢየሩሳሌሙ በክፍል 1 መጽሐፍ በገጽ 32 ተጽፏል። የፋርሱ ግን እነሆ። መሳፍንተ ፋርስ ግብጽ ዘምተው ድል ነስተው ሲመለሱ ከመካከላቸው አንዱ ኢየሩሳሌም ወርጄ አይሁድን ማርኬ እመጣለሁ ብሎ እግረ መንገዱን ወደ ኢየሩሳሌም ወርዶ አይሁድን ማርክ ሲመለስ ንግሥት ዕሌኒ በሳልሳልታ ካሠራችው ቤተ መቅደስ ቢገባ

መስቀሉን እንደወሐደ ሲያበራ አገኘው። ቢይዘው አቃጠለው። ከዚህ በኋላ ሁለቱን ዲያቆናት አሸነሞ ሊላውንም ንዋያተ ቅድሳት ዘርፎ ወደሀገሩ ተመለሰ።

የሮሙ ንጉሥ ሕርቃል ይህን በሰማ ጊዜ እጅግ አዘነ። ግብር ገብቶ ቀኖና ይዞ አንድ ሰባዔ ሲፈጸም ፈታዴ እግዚአብሔር መሆኑን ተረድቶ በአዋጅ ዘምቶ ድል ነሣው። መስቀሉም ያለበት ጠፍቶት ሲቸገር ሲቀብር ዲያቆናቱን ሲገድል በመስኩት ሆኖ ያየች ከኢየሩሳሌም የተማረከች አንዲት ብላቴና አሳይታው አውጥቶ በልብሰ መንግሥቱ ጠቅልሎ ወደቁስጥንጥንያ ወሰዱ።
* ታሪኩ የተፈጸመው በ614 ዓ.ም ነው።/1/

መጋቢት 11 - ዕረፍቱ ለአባ አሌፍ ዘእም ፱ ቅዱሳን

መጋቢት 12 በዓሉ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መ

(1) ነገረ የቤ/ክ ታሪክ በዓመ ገጽ 145

በዚህ ዕለት ወደ በለዓም ተልኳል። ሀብተ መርገም የተሰጠው ነውና እስራኤል ከምድረ ግብጽ ወጥተው አርባ ዘመን በረሀ ለበረሃ ተጉዘው ሞአብ ሲደርሱ የሞአብ ንጉሥ ባላቅ ወልደ ሶፎር ግብጻውያንን በዘጠኝ መቅሰፍት በአሥረኛ ሞተ በኵር በአሥራ አንደኛ ስጦመት ያጠፋ፣ ጦር የማያመልሰው ጽኑ ጠላት ተንሥቶብኛል መጥተህ ርገምልኝ ብሎ እጅ መንሻ አሲሥ ላከበት። ዋሉ እደሩ አላቸው። ሌሊት ወደጌታ በጸሎት አትሂድ አለው። አልሆነም ሂዱ አላቸው። ሂዱ እጅ መንሻው ቢያንስበት መልእክተኞቹ ተራ ቢሆንብት ይሆናል ብሎ እጅ መንሻውን በርከት አድርጎ ሾማምንቱን ላከ። ዋሉ እደሩ ፈጣሪዬን ልጠይቅ አላቸው። ዋሉ እደሩ። ወደ ጌታ ቢያመለክት ሂድ ነገር ግን አትርገም አለው። ሂድ ብሎ አትርገም ማለት እንደምን ነው? ከሂድኩስ የማደርገውን አውቃለሁ ብሎ የሚራገመውን እያሰበ ሲሄድ ቅዱስ ሚካኤል ሰይፉን መዞ ለአህያው ታያት ፈርታ ቆመች፣ ሂጂ እያለ መላልሶ መታት። በሦስተኛው ከቅጽርና ከቅጽር መካከል ይዛው ገብታ እግሩን ላጠችው። አሮጌ ነቢይ ብለሽ ነው እንዲህ የምትጫወቺብኝ? ወይኔ ጦር በያዝሁ በወጋሁሽ ሰይፍ በያዝሁ በቀላሁሽ ነበረ አለ። በሰው አንደበት "አኩኑ እድግትከ ዘትጼወነኒ እምንዕስከ-ከልጅነትህ ጀምሮ የምትቀመጥብኝ አህያህ አይደለሁ ምን እስክ ባዴ ሚዳውን ሩጪ ዳጉቱን ውጪ ብትለኝ እንቢ ብዬ አውቃለሁ? አለችው። እውነትሽን

ነው አለ። በዚህ ጊዜ መልአኩ ተገለጸለት፣ ከአህያው ወርዶ ሰገደለት እነሆ መንገድህ በፊቴ ጠማማ ነውና ልቋቋምህ መጣሁ፣ ለምን አህያህን መላልሰህ መታህ? ብሎ ገሠፀው። እርሱም በግንባሩ ተደፍቶ ከሰገደለት በኋላ ልመለስን? ብሎ ጠየቀ መሄዱን ሂድ ነገር ግን እግዚአብሔር የገለጸልህን እንጂ ሌላ እንዳትናገር እወቅ አለው። ሄደ። ባላቅ ደስ አለው። ስለመጣሁ ደስ አይበልህ የምናገረው እግዚአብሔር የገለጸልኝን ብቻ ነው አለው።

ከዚህ በኋላ መሥዋዕት ሠውቶ ከመሥዋዕትህ ቁም አለው። ወደ ምሥራቅ ተሣዙር "ምንተ እረግም ዘእግዚአብሔር ኢረገመ፣ ምንተ ኢጸዐል ዘእግዚአብሔር ኢጸዐለ-እግዚአብሔር ያልረገመውን በምን ነገር እረግማለሁ እግዚአብሔር ያልሰደበውን በምን ነገር እሰድባለሁ" አለ። ርገምልኝ ብልህ ትመርቃቸዋለህን? አለው። የገለፀልኝን ብቻ እናገራለሁ አላልሁምን? አለው። ሁለተኛ መሠዊያውን ከፍ አድርጎ ሠርቶ መሥዋዕቱን ጨምሮ ሠውቶ ርገምልኝ አለው። አሁንም እያሜረተ ወደ ምሥራቅ ተሣዙር "ከተራሮች በላይ አየሁት ከኮረብታዎችም በላይ አስተዋልሁት እግዚአብሔር አምላኩ ከርሱ ጋራ ያለ ሕዝብ ክብታች ይናራል" አለ። ባላቅም ርገምልኝ ብልህ ሁለተኛ ትመርቃቸዋለህን? ብሎ አዘነ። በሦስተኛ ከሌላ ኮረብታ ወሰዶ ርገምልኝ አለው።

"ሚ ይሜኒ ተዓይኒከ ያዕቆብ ወእር አብያቲከ እስራኤል - ያዕቆብ ከተማህ ምን ያምር? እስራኤል ቤቶችህ ምን ያምር" ብሎ አደነቀ አሞገሰ። አያይዞም "ኮከብ ይሠርቅ እምያዕቆብ መየአትት ኃጢአተ እምእስራኤል" ብሎ የጌታን ሥጋዌ ተናገረ። ርገምልኝ ብልህ ሦስተኛ ትመርቃቸዋለህን? አለው። እግዚአብሔር የገለፀልኝን ብቻ እንድናገር አስታውቋህ የለምን? አሁንም የምትሻው ጥፋታቸውን ከሆነ ረግሜ ባላጠፋልህ መከሬ አጠፋልህለሁ ደናግሉን ጣእት አሳዝለህ መሥዋ ዕተ እርያ አሲዘህ ስደዳቸው፣ እንድረስባችሁ ይሏቸዋል ለጣያት ስገዱ መሥዋዕቱን ብሉ ይበሏቸው፣ ይሰግዳሉ ይበላሉ በዚህ ጊዜ አምላካቸው ተቆጥቶ ያጠፋቸዋል ብሎ መከረው።

እንዳለውም ደናግሉን ጣእት አሳዝሉ መሥዋዕተ እርያ አሲዞ ሰደዳቸው። ተሻጠባቸው። ለጣያት ሰገዱ መሥዋዕታቸውን በሉ። በዚህ ጊዜ ቸነፈር ይፈጃቸው ጀመር። የይሁዳ ቤት አለቃ ዘምሪ ከባላት ቤት አለቃ ልጅ ከከሰቢ ጋር ተጠቃቅሰው ከእልፍኝ ሲገቡ አንድ ብላቴና አይቶ ለፈንሐስ ወልደአሮን ነገረው። ሁለቱንም ከተኙበት በጦር ወጋቸው ጌታም ፈንሐስ ወልደአሮን አስተንፈስካ ለልብየ-ብሎታል። መዓቱንም በምሕረት መልሶላቸዋል። በዚህም ምክንያት ለፈንሐስ 300 መዋዕለ ክህነት ተሰጥቶታል።
ዘኁ ምዕ 22 እና 23

• ታሪኩ የተፈጸመው በ1280 ዓ.ም ገደማ ነው።

መከራና ችግር የማይለመነው
ጠላት ተመቅኝቶ የማያጠፋው
ቢታመም የሚድን ወድቆ ሚነሳው
እግዚአብሔር ከርሱ ጋር ያለለት ሰው ነው።
ያገን ምእመን በዓለም ምን ያስጨገተዋል
ጌታ ካከበረው ማን ያዋርደዋል?

ሰው ለምን ይለፋል እያባከው ገብቶ
ያለ እምነከ ፈታድ አንዳች ላይሆን ከተ።
በጎ በጎ እስበህ በጎ ከሰራህ
ሁልጊዜ ይኖራል እግዚአብሔር አብሮህ
እግዚአብሔርም ካለ ሁሉ በጎንህ
ከፈትህ ለመቆም ያፍራል ጠላትህ።

መዝ 22:4 ሮሜ 8:3

መጋቢት 13 አርብዓ ሐራ ሰማዕት

የብስጥያ የጦር ሠራዊት ነበሩ። የብስጥያው መስፍን ቢሞት ንጉሡ ቄስጠንጢናስ እልፍያኖስን መስፍኑ-ብስጥያ አድርጎ ሾመው። ለጊዜው ከክርስቲያን ጋራ እተባበራለሁ አብያተ ክርስቲያናትን አንጻለሁ ብሎ ተሾሞ ነበረ። ኋላ ግን የወርቅ የብር ምስል አቁሞ ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣዖት ሰገዱ አለ። ብዙዎች ከመሞት መሰንበትን ሽተው ሃይማኖታቸውን ክደው ለጣኦት ሲሰግዱ እኒህ አርባው ሃይማኖታችን አንክድም ለጣኦት አንሰግድም አሉ። ሥጋቸው እስኪተፈተፍ ድረስ አሰገርፎ ውርፊቱ ሰውነት ከሚበጣጥስ ጥልቅ የውኃ ጉድጓድ ጣላቸው። ሠላሳ ዘጠኝ ቀን ሲመላቸው ከሁሉ አንዱ መከራውን ጸልቶ ሥጋዩን ተሰቶ ወጣ። በግማሹ አርባ አክሊላት በሰማይ ረበው ሠላሳ ዘጠኙን ሠላሳ ዘጠኙ ሲቀዳጁ አንዲቷ ተንጠልጥላ ቀረች። ይህን አይቶ አንድ አረማዊ አምኖ ዘሉ ገብቶ ተቀብሏቷል። ከዚህ በኋላ እልፍያኖስ ጭንጭናቸውን ሰበሯቸው አለ። ቢሂዱ አርፈው ተገኝተዋል።

• ታሪኩ የተፈጸመው በ4ኛው ምዓ ድ-ል-ክ ነው።

ትጠሏ ቢመርም የተከለ ትዕግሥት
ፍሬዋ ጣፋጭ ነው እንደመጽ እዘት
ረሀብ ጥም እሰር ችግር ካለመጡ
ፀንቶ ከተገኘ ሁልጊዜ በዓላማው
የከርስቶስ ወዳጅ ቢታ እርሱ እኩ ነው።
መከራን መታገሥ ናፍቆ የንውን
መለኪያው ይሄ ነው የእውነተኞው ምእመን
የምን ተሰፋ መቁረጥ ፈጣሪ ግግረር
ከቶ ምን አለና የማያልፍ ዘለዓለ ምድር

ትናንት የነበረው ዛሬ ካልታየማ
ዛሬም ያለው ነገ ካልተደነማማ
እንዳያው ሁሉም ነገር ከቦለጠጠማ
አንዳችም አይበጅም ተስፋ መቁረጥማ
መታገሥን ግን መልካም ይሆነናል ማማ
ችኩል ተስፋው ሲበን አንዳመድ ሲከስም
የታገሠ ከብርን ሳያገኝ አይቀርም።

ሉቃ 22 ፡15 1 ጴጥ 2:14 3:14 ፡ 4:12

መጋቢት 21 ቅንጣኢ አልዓዛር

በዓሉ የጌታ በዓል ነው። በዚህ ዕለት አልዓዛርን ከሞት አንሥቶታል። መዳኑ አሐዱ ብእሲ ዘይደዩ ዘሰመ አልዓዛር

በቢታንያ ዘሀገረ ማርያ ወማርታ ይላል፡ አልዓዛር ሞተ፣ ቢሞት እኅቶቹ ማርያምና ማርታ ወዳጅህ ሞተ ብለው ላኩበት። ወያፈቅሮን እግዚእ ኢየሱስ ለማርያ ወለማርታ እኅታ ወለአልዓዛር ይላል ይወዳቸው ነበረ። ሁለት ቀን ካለበት ውሉ ኀርብ ንው ንሑር ብሔረ ይሁዳ - ወደ ይሁዳ እንሂድ አላቸው። አይሁድ በደንጊያ ወግረው በእሳት ተኩሰው ሊገድሉህ ሲፈልጉህ እንሂድ ትላለህን? አሉት። አልዓዛር ዐርክነ ሞተ ወዳጃችን አልዓዛር ሞተ አላቸው። ቢታንያ ቀርበው አደሩ። ሲነጋ ማርታ መምጣቱን ሰምታ ከመንገድ ተገናኝታ ሶበሰ ሀሎከ ዝየ እምኢሞተ እኁየ ከዚህ ኑረህ ቢሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበረ። አሁንም ጌታ (አብ) የለመንኸውን እንዳይነሳህ አውቃለሁ አለችው። ዘየአምን ብየ እመኒ ሞተ የሐዩ - በኔ ያመነ ቢሞትም ይነሳል አላት።

ማርያ(ም) ከቤት ነበረች፤ ናሁ መጽአ ሊትነ ብላ ማርታ ነገረቻት። እየተቻኮለች ተነሥታ ወጣች። አብረዋት የነበሩትም ከመቃብሩ ሂዳ ልታለቅስ ነው ብለው እያለቀሱ ተከተሏት። እጅ ነስታ አሷም እንደ እኅቷ ሶበሰ ሀሎከ ዝየ እምኢሞተ እኁየ አለችው። ወአንብዐ ካዕበ እግዚእ ኢየሱስ ይላል እንዳውን አፈሰሰ። አይቴ ቀበርከሙም - የት ቀበራችሁት? አለ። መለከቶስ ሁሉን ያውቃል እንዲህ ማለቱ ግን ሥጋን መዋሀዱን ለማጠየቅ ነው። ወሰደው አሳዩት መቃብሩ ዙሪያውን የታነጸ ከላይ በታላቅ ደንጊያ የተገጠመ ነበረ ደንጊያውን አንሡት አላቸው። ማርታ እግዚአየ ናሁ ወድአ ኢአ - ከሞተ አራት ቀን ነውና ፈጽሞ ተበላሽቶ ይሆናል አለች። ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ጸጋ ታያለሽ አላት። ወዲያውም አባቱን አመስግኖ አልዓዛር አልዓዛር ነዓ ጸአ አፍኣ - ና ውጣ አለው። ወወጽአ ውእቱ ምውት እንዘግኑዝ ወእሱር እደዊሁ ወእገሪሁ ይላል - እጅ እግሩ እንደታሰረ ወጥቷል። ለጊዜው ምትሐት መስሏቸው ነበርና ፍቱት ይሂድ አላቸው። ፈትተውት በመካከላቸው እየተመላለሰ አመሰግኗል።

ዮሐ 11:1-45

ኋላም በቆጵሮስ ኤጲስቆጶስነት ተሹሞ አርባ ዘመን አስተምሮ ግንቦት 26 ቀን በሰላም አርፏል።

• ጌታ ከሞት ያነሳው በ33 ዓ.ም አስተምሮ ያረፈው በ73 ዓ.ም ነው

ለ. አግብአተ - ግብር በቤተ ሰምዖን

ከሰቅለቱ ሰምንት ቀን አስቀድሞ ቅዳሜ ከቤተ ሰምዖን ግብር አገቡለት። አልዓዛርን ጨምሮ ደቀመዛሙርቱን ይዞ ማዕድ ቀረበ። ማርታ ባጭር ታጥቃ ታገለግላቸዋለች። ወማርያሰ ነሥአት ዕፍረተ

ልጥረ ዘናርዱ ጵስጥቂስ ዘዕፁብ ሜጡ ወቀብዐቶ ለእግዚእ ኢየሱስ ይላል ማርያም የከበረ ሽቱ ቀብታዋለች።

ይህስ እንደምን ነው? ቢሉ ይህች ማርያም ከእግር ጥፍሯ እስከ ራስ ፀጉሯ ይህ ቀረሽ የማትባል ቆንጆ ነበረች። ውበቷን በመስታወት አይታ ይህ ሁሉ ማማር ከንቱ መሆኑን ተረድታ ኃጢአቴን እንዲያስተሰርይልኝ ሽቱ ገዝቼ ከመምህሬ ዘንድ ልሂድ ብላ በአሰበ ደነስ የሰበሰበችውን 300 ወቂት ወርቅ ይዛ ልትገዛ ስትሄድ ሰይጣን የምታውቀው ወዳጇን መስሎ ከጎዳና ቆይቶ ወዲት ትሄጃለሽ? አላት ዝም አለችው። እንግዳ ወንድ መጥቶብሽ ሽቱ ልትገዢለት አይደለምን? አላት። አዎን አለችው። ዳግመኛ ፍቅሩ ያላለቀለት ወንድ መጥቶብሽ ሽቱ ልትገዢለት ይሆናል አላት። አዎን አለች። ሦስተኛ ብዙውን በጥቂት የሚሸጥ ነጋዴ መጥቶብሽ ነው አላት። አዎን አለችው። ሁሉንም አዎን አልሽኝ እውነቱ የቱ ነው? አላት። እንግዳ ወንድ አልሽኝ ከዚህ ዓለም ልዩ የሆነ፣ ፍቅሩ ያላለቀለት አልሽኝ የሰው ፍቅር አገብሮት ሊሞት የመጣ፣ ብዙውን በጥቂት የሚሰጥ ነጋዴ አልሽኝ በጥቂት ትሩፋት ብዙ በረከት የሚሰጥ ክርስቶስ ኢየሱስ መጥቷል ለርሱ የምቀባው ሽቱ ልገዛ እሄዳለሁ ብላ ሰሙን ብትጠራበት እንደጢስ ተኖ እንደትቢያ በኖ ጠፍቷል።

ከዚህ በኋላ ሐድናከ ከሚባል ነጋዴ ሄዳ ይትረከብኑ በነቢከ ቅብዐ አፈው ዘይደሉ ለነገሥት ለነገሥታት የሚገባ ሽቱ ካለህ ስጠኝ ብላ 300 ውን ወቂት ሰጠችው። ዳዊት ሰሎሞን ተቀብተውለት የተረፈ ጌታም ግብጽ ሲወርድ ጥሎስ ታቅፎት ሳለ ከልብሱ ላይ ያረፈ ወቡን ሲያጥበው ሽቱ የሆነው ተጨምሮበት የተቀመጠ መንክረ ጴና ሽቱ ነበር፣ ሰጣት። ይህን ይዛ ሄዳ ከስምዖን ቤት ስትደርስ ስምዖን ሽቱ ተቀብታ የመጣች መስሎት ገሠጻት አሳሰገባምም አላት። ጌታ መኑ ጉድጉደ እንቀጸ አፀድከ - ማን አንኳኳ ለምንስ እንዳይገባ ከለከልኸው? አለው። ኃጥአንን አትወድም ብዬ አሰው። መድኃኒት የሚያስፈልግ ለበሽተኛ እንጂ ለጤነኛ ነውን? የሰው ልጅ መምጣቱ ኃጥአንን ወደንስሓ ሊጠራ ነውና ከፍተህ አስገባት አለው። ገብታ ከወደኋላው እያለቀሰች ሽቱውን ቀባችው፣ እግሩንም በእንባዋ አርሳ በፀጉሯ አበሰች።

ይሁዳ (አስቆሮታዊ) ለምንት ኢሄጥም ለዝንቱ ዕፍረት ለሠለስቱ ምዕት ዲናር የሀብም ለነዳያን ለነዳያን ይሰጡት ዘንድ በ300 ወቂት ይሸጥ አልነበረምን? ብሎ ተቆጣ። የገንዘብ ሹም ነበርና ከአሥር አንድ የሚያገኘው ስለቀረበት እንጂ ለነዳያን አስቦ አልነበረም። ጓላም በሥላሳ ብር የሸጠው ይህን የቀረበትን ለማግኘት ነው። ነዳያን ሁልጊዜ ካንተ ጋር ናቸው፣ ይህች ግን አስመ ተዐቅቦ ለተበርየ ለምቀበርበት አስጠብቃዋለችና ተዋት አለው። እሷንም አማን አብለኝሙ በነበ ሰብኩዎ ለሠተ መንጌል ይንግሩ ውስተ-ኩሉ ዓለም ዘገብረት ዛተ ብእሲት ተዝክረ ላቲ መጽዝክርዋ - መንጌል በተነገረችበት ቦታ ሁሉ ያደረገችውን ሊነግሩላት ይገባል ብሎ ጌሠኢታን አስተሰርዮ አሰናብቷታል። ማቴ 26፣ 6-14

መጋቢት 22 - ሦሪዕና

ወሶበ በጽሐ ቤተፋጌ ወቢታንያ ኀበደብረዘይት ዘስሙ ኢሌዎን ቅዳሜን ከስምዖን ዘለምጽ ቤት ግብር ገብቶለት ዋለ። ዮሐንስ ወበሳኒታ ይላል በግንቡቱ ደብረዘይት ሲደርስ ከደቀመዛሙርቱ ሁለቱን ሑሩ ሀገረ ዘቅድሜክሙ - ከፊታችሁ ወዳለ ሀገር ሂዱ ሰው ያልተቀመጠበት የአህያ ውርንጭላ ታገኛላችሁ፣ ፈትታችሁ አምጡልኝ ለምን ትፈታላችሁ የሚል ቢኖር በሉ እግዚኡ - ይፈቅዶ - ጌታው ይፈልገዋል በሉ ብሉ ላካቸው። ሂደው ጌታው ይፈልገዋል ብለው ፈትተው አመጡለት። ወረሀኑ አልባሲሆሙ ይላል ልብሳቸውን ጎዝጉዘውለት በዚያ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ። ደቀመዛሙርቱም ሰማይ ተከፍቶ ፀሐይ ከአህያው ፊት ሁና ስትሰግድ ምድሪቱም ብርሀት ጽድልት ስትሆን መላእክትም ከሰማይ ወርደው አህያውን ከበው ሲያመሰግኑት አይተው ልብሳቸውን ከመሬት እያነጸፉ ብሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተመሰገነ ነው እያሉ አመሰግነውታል።

ኢየሩሳሌም ሲደርስ ከገጹ ብርሃን የተነሣ ከተግዋ ብርሀት ሆነች። ሕዝቡ የሆነውን ሊያዩ ወጡ። ሕፃናት ፀሐይ ስትሰግድለት መላእክት ከበው ሲያመሰግኑት አይተው በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የሰሌን ዝንጣፊ ይዘው ሦሪዕና በእርያም ሦሪዕና ለወልደ ዳዊት ቡሩክ ዘይመጽእ በስመእግዚአብሔር እያሉ አመሰግነዋል። ሦሪዕና ማለት በልዕልና ጸንቶ የሚኖር መድኃኒት ማለት ነው። ከምን አገኙት? ቢሉ ጌታ ወደ ግብጽ ሲወርድ እስሙናይን ሲደርስ ዕፀተመርት አግኝቶ ካለችበት ቦታ ተነሥታ ደብረዘይት እንድትተክል አዘዛት፣ አሜሃ ሰረረት ውሱተ አየር ወተተክለት ሠየ ይላል በአየር በራ ደብረዘይት ተተክላለች ከዚያ ቆርጠው አምጥተዋል።

ሕፃናቱ ሦስት እፍል ናቸው። የነርሱ ምስጋና ከመላእክት ምስጋና ተዋህዶ ኢየሩሳሌም ተናወጸች። ረበናተ አይሁድ ምን መጣብን ብለው ደንግጠው ቢወጡ ሕፃናቱን ሲያመሰግኑ አገኙ። እግዚአብሔር በሚመሰገንበት ምስጋና የጽዬንን ልጅ እንድታመሰግኑ ግን አስተማራችሁ? አሏቸው። እናንተ እውሮች ፀሐይ ስትሰግድለት መላእክት ሲያመሰግኑት አታዩምን? ዳዊትስ ስለኛ "እምአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስቶዳሉከ ስብሐተ" መዝ 8፡3 ያለውን አላነበባችሁምን? አሏቸው። ግሰተው የማይቻላቸው ቢሆን ሂደው ጌታን አዝዘው

ለሕፃናት ከመያርምሙ ዝም እንዲሉ ሕፃናቱን እዘዛቸው አሉት። እኒህ ሕፃናት ዝም ቢሉ ደንጊያዎች እያመሰገኑኝ መሰላችሁ? አላቸው። ወዲያው ደንጊያዎች ከደብረዘይት እየዘለሉ መጥተው ሆሣዕና በአርያም ለአምላክነ ሆሣዕና ቡሩክ ለመድኃኒነ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ብለው አመሰግነውታል። ወተደመረ ቃሉ ሕፃናት ወቃለ-አዕባን ምስለ ስብሐተ መላእክት እንዲል ዲድስ። መቅደሱን ሦስት ጊዜ ዞሮ ወገፍትአ ማዕዳቲሆሙ ለመወልጣን ይላል ኻሎችን ለቖሎችን መሸጫ መለወጫቸውን አፈራርሶ እነርሱንም በጅራፍ እየጎረፈ አስወጥቷቸዋል። ማቴ 21፡ 1013

* ይህ ሁሉ የሆነው "ተፈሥሒ ወለተጽዮን ወተሐሠዪ ወለተ ኢየሩሳሌም ነዋ ይመጽእ ንጉሢ የዋህ ወትሑት ተጽኢኖ ዲበእዋለ አድግ" ተብሎ በዘካርያስ የተነገረ ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ነው። ዘካ 9፡9

ከመጋቢት 23-28 - ሰሙነ ሕማማት

የዐቢይ ጾም ስምንተኛ ሳምንት ሰሙነ ሕማማት ይባላል። ጌታ የሰው ፍቅር አገብሮት ከሰማያት ወርዶ ከድንግል ተወልዶ ሰው ሰውኖውን ኑሮ በአይሁድ እጅ ተይዞ ተገርፎ ተሰቅሎ መሞቱን የምናዘክርበት ጊዜ ስለሆነ ነው። በእኒህ ስድስት ዕለታት ክደሰታ ከጨዋታ ተለይቶ ሕማሙን ሞቱን እያሰቡ ሊያዝኑ ቀን ከሌሊት ከቤተ ክርስቲያን ላይለዩ ሕማሙን ሞቱን የሚናገሩ መጻሕፍትን ሊያነቡ፤ ሊሰሙ መዝሙረ ዳዊት ውዳሴ ማርያም ከሰጊድ ጋራ ሊያደርሱ ይገባል። የመላእክት የጻድቃን የሰማዕት መልክእ ግን አይነበቡም። የቻለ ሁለት ሁለት ቀን ያልቻለ እስከ ዕርበተ ፀሐይ ሊጸም ይገባዋል፤ ምግቡ ጎብስት በጨው መጠጡ ጥሩ ውሃ ነው። በእኒህ ዕለታት ሥጋ የሚቆርጥ ወይን ጠጅ የሚያንቆረቁር ቢኖር ዕድል ፈንታው ጽዋ ተርታው ጌታን በመስቀል በመግደል ደስ ከተሰኙ አይሁድ ጋራ ነው። ሕሙም ድውይ ቢሆን ግን ከበዓለ ሃምሳ በኋላ ተክቶ ሊጸም ይችላል። ይልቁንም ከሌት የደረሰ ሰውነቱን ያረከሰ ዕዳ ፍዳ ይጸናበታል። አሌ ሉቱ ለዘይገብራ ለዛቲ ኃጢአት በሰሙነ ሕማማት ቅድስት
እንዲል ፍት-ነገ-አንቀጽ 24፡5

መጋቢት 23 - ዕረፍቱ ለዳንኤል ነቢይ

ዳንኤል ማለት ዳኛ እግዚአብሔር ማለት ነው። ትውልዱ ከነገደ ይሁዳ ነው። በምርኮ ፋርስ በፀሎን ይኖር ነበር። ንጉሡ ናቡከደነጾር አንድ ቀን በልቶ ጠጥቶ ከሰገነቱ ሲመላለስ የኩተገውን ሰፋት የሠራዊቱን ብዛት አይቶ እኔ ይህን ዓለም እንደ ሰም አቅልጬ እንደ ገደል ቀጥቅጬ ገዛሁት ከኔ ቀጥሎ የሚነግሠስ እንደኔ ብርቱ ይሆን? ብሎ አሰበ። ሊሊት በሕልሙ ራሱ የወርቅ አንገቱ ደረቱ የብር ወገቡ የነሐስ ጭንና ጭኑ የብረት እግርና እጁ የብረትና የሸክላ ቅልቅል ምስል ከፊቱ ቆሞ ሲያየው ከረጅም ተራራ እጅ ሳይፈነቅለው የወረደ ደንጊያ አድቆት ተመልሶ ተራራ ሲያህል አየ። ሰለደነገጠ ሕልሙ ጠፋው። ከበላው አብልቶ ከጠጣው አጠጥቶ የሚያናውራቸው መፈክራን ሕልም ነበሩት፤ አስጠርቶ ጉራም ሕልም አይቼ ሕልሙም ትርጓሜውም ጠፋኝ ንገሩኝ አላቸው። ንጉሥ ፍርድ ልበስ ሺህ ዓመት ንጉሥ የሴፍ ለፈርዖን ቢተረጉምለት ሕልሙን ነግሮት ነው። አንተም ንገረን እንተርጉምልህ አሉት። እኔግ ጠፍቶኛል። ይልቁንስ ጊዜው ሳያልፍ ንገሩኝ ነገሩ ከልቤ ይወጣል ይወርዳል ፈጠራ ፈጥራችሁ ብትነግሩኝ ወጥላችሁ አላቸው። እንኪያስ አይቻለንም አሉት። ፈረስ አይደላችሁ አልጋልባችሁ በቅሉ አይደላችሁ አላሰጠንችሁ ብሎ ያርክ የሚባል ሰይፍ ጃግሬውን ወስደህ ፍጃቸው አለው።

እንደ በግ እየነዳ ሲወስዳቸው ዳንኤል አገኘው። ወዴት ትወስዳቸዋለህ? አለው። ንጉሥ ሕልም አይቶ ጠፍቶት ንገሩኝ ቢላቸው አታታቸው፤ ስለዚህ ፍጃቸው ብሎኝ ልፈጃቸው እወስዳቸዋለሁ አለው። ቀን ሰጠኝና እኔ እነግረዋለሁ ተዋቸው አለው። ሦስት ቀን ሰጠው። ከሠልስቱ ደቂቅም ላከባቸው። ለነርሱ በሦስተኛ ቀን ተገለጸላቸው። ለርሱ ግን ዕለቱን ተገልያለታል። ስለትሕትና ሰንብቶ በሦስተኛው ቀን ገብቶ ሕልሙን ከነትርጓሜው ነግሮታል። በዚህ ምክንያት በሹማምንቱ ላይ ሾሞታል።

ከዚህ በኋላ ናቡከደነጾር አልፎ ብልጣሶር፤ ብልጣሶር አልፎ ዳርዮስ ነገሠ። ዳንኤልን በጣም ይወደው ነበር። ባቢሎናውያን ቀንተው ነገር ሠሩበት። ምነው ለአምላኬ አትሰግድም? አሉ። አይበላ አይጠጣ አይሰግ፣ ምን ብዙ እሰግድለታለሁ? አለው ካህናተ ጣዖቱ ይበላል ይጠጣል እያሉ ምግቡን በያይነቱ እየወሰዱ ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን ይዘው ይመገቡ ነበረና - እየበላ እየጠጣ? አለው። አለመ ብላ ቱንስ ታያለህ ብሎ መርቻ እንዲሆነው የኋሊት አመድ ነስንሶ ምግቡን ጠጁን ብርዙን አስቀምጠ በማኅተመ ንጉሥ አትሞ ሄደ። ቢመጡ ተዘግቶ አገኙ። በምስጢር በር ገብተው ተመገቡ። ንጉሡ ቢል ኃያል አምላክ ዳንኤልን አሳፈርኸውን አለ ... ዳንኤልም ዝ አሮ ዘመኑ-ይህ የማን ዱካ ነው? እያለ በዘንግ አሳየው። የካህናተ ጣዖቱን፤ የምስቶቻቸውንና የልጆቻቸውን አሰር አየ። ለካስ ሲሔዱብኝ ኑረዋል ብሎ በሰይፍ አስመትቷቸዋል።

ከዚህ ሌላ መንፈስ ርኩስ ያደረበት ዐቢይ ዘንዶ ያመልኩ ነበር። ያ አይበላም አይጠጣም አልህ፤ ለዚህ ለሚበላው ለሚጠጣው አትሰግድምን አለው። ይህንንም ከፈቀድህ ጦር ጋሻ ሳልይዝ እገድለዋለሁ አለው ሂድ አለው። እንዳሰለመዱት በግ አርዶ ሥጋውን አወራርዶ ሰቡን ጸጉሩን ጨርቅ ገል ጨምሮ አጨሰለት። እያስካካ መጥቶ አፉን ከፈተ፤ ሰቡን በጋለ እሉሉ ጠቅልሉ ከአፉ ጣለለት፤ ተሰንጥቆ ሙቷል። ተረ.ዳን ምዕ 1. ሃይ.አበ ዘዮሐ አፈ. ምዕራፍ 67 ባቢሎናውያን ጸልተው ተመቅኝተው ንጉሥ ወዳጅህን ጠላትህን እንድናውቅ ለሦስት ቀን አዋጅ ይነገርልን አሉት። ነገረላቸው። በሦስተኛው ቀን በሦስት ሰዓት ዳንኤል መስኩን ከፍቶ ሲጸልይ አዋጅ አፍርሶ ሲጸልይ አገኘው ብለው ለንጉሡ ነገሩት። የተፈረደበትን ሰው የሚመገቡ አናብስት ነበሩ። ወሰደው ጣሉት። በግግስቱ ቢሄዱ ላይበሉት አገኙ። ባይርባቸው ይሆናል ብለው ምግባቸውን አስቀሩባቸው። ነገር ግን ቅዱስ ሚካኤል አፋቸውን ስለዘጋ አልተተናኮሉትም።

ነቢዩ ዕንባቆም በኢየሩሳሌም ለአጫጆች ምሳ ይዞ ሲሄድ መልአኩ ሰድ ሉቱ ዘንተ ምሳሐ ለዳንኤል ዘሀሉ ውስተ ገበ ባቢሉን ለዳንኤል ውሰድለት አለው። ዳንኤል የት አለ? ባቢሎንንም አላውቃትም አለው። ወሥሥ በአሐቲ ሥዕርተ ድግሁ ይላል እንዲት ጠጉሩን ይዞ አደረሰው፤ ሳይከፍት ገብቶ መግቦት ወጥቷል።

ንጉሡ ይወደው ነበርና ፈጣሪው አድኖት ይሆንን ብሎ ቢሄድ አናብስቱ እንደድመት ከእግሩ ወድቀው እሱ ቆሞ ሲጸልይ አገኘ። ዐቢይ አምላኩ ለዳንኤል-የዳንኤል አምላክ ገናና ነው ብሎ ና ውጣ አለው። ባቢሎናውያንን ቢያስጥላቸው ከአየር እየተቀበሉ ሰባብረዋቸዋል። ንጉሡም አምኖ አሕዛብ እንዲያምኑ አዋጅ ነገሯል። ዳን 7፡ 1-28

ከዚህ በኋላ ሚጠተ እሰራኤልን ሲሻ ቀኖና ገባ። ከሚጠትም የበለጠ የሥጋዊ ነገር ተገልጸለት "እስከ ክርስቶስ ንጉሥ ትትሐነጽ መቅደስ" ብሎ ትንቢት ተናግሯል። በዚህም ዕለት ዕረፍቱ ይነገራል።

• መዋዕል ትንቢቱ ከ 556-538 ዓ.ዓ ገደማ ነው።
የመ.ት. መታ - ገጽ 208

መጋቢት 25 - ምክረ አይሁድ

በዚህ ዕለት አይሁድ ጉባዔ አስፍተው ነገር አጽንተው ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ ሲያደርግ፤ ሰንበትን ሲሽር፤ ሙሴንና አሪትን ሲያቃልል ለንጉሥ ግብር አትስጡ ሲል ሰምተነዋል ብለን አስመከረን ሰቅለን እንግደለው ብለው ምክር አጽንተዋል። (ዕለቱ ረቡዕ)

መጋቢት 26 - ሕጽበተ እግር

እስራኤል ከግብጽ የወጡበትን በዓለ ፍሥሕ፣ ፋሲካ፤ በዓለ መጸለት እያሉ በየዓመቱ አርሾ የሌለው ቂጣ ጋግረው በጉን አርደው በመብላት ያከብሩት ነበር። ዘጸ 11፡ 32 ዕ 51

ጌታም በዚህ ዕለት ከደቀመዛሙርቱ ጋር አክብሮታል። ደቀመዛሙርቱ በአይቲ ትፈቅድ ናስተዳሉ ለክ ፍሥሐ ትብላዕ ፋሲካውን ትበላ ዘንድ በየት ብናዘጋጅልህ ትወዳለህ? አሉት። ከፈታችሁ ወዳለ ሀገር ሂዱ የውሃ ማድጋ የተሸከመ ሰው ታገኛላችሁ ከገባበት ተከትላችሁ ይቤለክ ሊት አይቲኑ ጽርሕ ኀበ እበልዕ ፍሥሐ ምስለ አርዳእየ በሉት ያሳያቹሀል ብሎ ጴጥሮስን ዮሐንስንና ያዕቆብን ላካቸው።

ቢሄዱ የውሃ ማድጋ ተሸክሞ ሲሄድ አገኙት። ስምዖን ዘስምጵ ነው። ተከትለው መምህር ከደቀምዛሙርቱ ጋር ፋሲካውን የምበላበት አዳራሽ ወዴት ነው? ብሎሀል አሉ፤ ደስ አለው ለምስቱም ነገራት።

በዘጠኝ ሰዓት ጌታ ደቀመዛሙርቱን አስከትሎ ሄደ። ከደርቡ ላይ ግምጃ አንጥፎለት ያን እየረገጠ ገብቷል። ይሁዳ ወደ ኋላ ቀርቶ ነበር። ስለምን ቢሉ በደብረዘይት ጌታ አሐዱ እምኔክሙ ያገብአኒ-ከናንተ አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል። እምጌሰ ሰብ ኢተወልደ ለውእቱ ብእሲ ለዚያም ሰው ባይወለድ ይሻለው ነበር ባላቸው ጊዜ ደቀመዛሙርቱ አዝነው መኑ ዘይከህደ እምኔነ ንግረነ ገሠጼ-የሚክድ ማነው ገልጠህ ንገረን ቢሉት ከከራድዮስ ደንጊያ አንዱን እኔን አሳልፎ የሚሰጠኝ ማነው? ተናገር ብሎት በይሁዳ ራስ ሦስት ጊዜ ዞሮ ንጹሕ ደም የምታፈስ ይሁዳ ወዮልህ ብሎ መስከርበት ይህ መሠርይ ብሎ ብሎ ደንጊያ ያናግርብኝ? በማኝ ያማኝኝ ብሎ ወደ ቤተመቅደስ ሄዶ ከአይሁድ ጋር ይማከር ነበርና ስለዚህ ነው። መጥቶ ሊገባ ሲል እለእስክንድሮስ የተባለው ጠባቂ እርሱ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ሲገባ ብሩህ ግዕጠንት ይዞ ገባ፤ አንተ ግን በደም የተመላ ጽዋ ይዘህል፤ ከእንተትህ እባብ ተጠምተሞ ሊስምህ ምላሱን ያውለበልባል፤ የያዝኸው ደም ቢነተብበት ጌታዬ ስለሚያዝንብኝ ቆየኝ ብሎ ምንጣፉን ካነሣ በኋላ አስገብቶታል።

ከዚህ በኋላ ከግዕድ ተነሥቶ ወዝቦን በዝናር ታጥቆ የደቀመዛሙርቱን እግር ሊያጥብ ውሃ በክስክስት ይዞ ቀረበ፣ ርዕሰ ሐዋርያት ነውና ከጴጥሮስ ይጀምራል። እግርህን አምጣ ልጠብህ አለው። አንተኑ እግዚኦ ተሐጽቦኒ እገርየ - አቤቱ አንተ እግሬን ታጥበኛለህ? አለው። የማደርገውን

ጓላ እንጂ አሁን አታወቀውም አለው። መቼም ቢሆን እግሬን አታጥብኝም አለ። እሙ ኢሐፀብኩከ እገሪከ አልብከ ክፍል ምስሊየ - ካላጠብኸሁማ ከኔ ጋር እድል ፈንታ ጽዋ ተርታ የለህም አለው። እንዲህስ ከሆነ እጄንም እግሬንም ጨምረህ እጠበኝ አለው። ፈጽሞ የታጠበ ከእግሩ ሌላ አያሻውም አለ። አንትሙሰ ንጹሓን አንትሙ - እናንተ ንጹሓን ናችሁ፤ ነገር ግን ሁላችሁም አይደላችሁም አለ።
አጥቦ ሲጨርስ ወሶበ አነ እንዘ ሊቅክሙ ወአግዚእክሙ ሐጸብኩክሙ እገሪከሙ እኔ መምህራችሁና ጌታችሁ ሰሆን እግራችሁን ካጠብኋችሁ አርአያዬን ሰጥቻችኋለሁና እናንተም የወንድማችሁን እግር ታጥቡ ዘንድ ይገባል። ነገር ግን ከናንተ አንዱ ለሞት አሳልፎ ይሰጠኛል አለ። ማን ይሆን? እኔ እሆንን? አሉ ጎብስት ቆርሺ ከወጡ ጠቅሺ የምሰጠው እሱ ነው አላቸው። ወዲያውም ጎብስቱን ባርኮ ከአሥራ ሦስት ፈትቶ ንሥኡ ብልዑ ዝ ውእቱ ሥጋየ - ነባ በመልዕልተ መስቀል የሚሠዋ ሥጋዬ ይህ ነው እንካችሁ ብሉ፣ ብሉ ተቀብሉ አቀበላቸው። ጽዋውንም አክብሮ ለውጠ ዝ ውእቱ ደምየ ዘሐዲስ ሥርዓት ዘይትከፀው በእንተ ብዙኃን ለኅድገተ-ኃጢአት - ስለብዙኃን የሚፈስ የሐዲስ ሥርዓት ደሜ ይህ ነው። ጠጡ ብሉ ሰጣቸው። ሥጋውን ደሙን በመብል በመጠጥ ማድረጉ መብል መጠጥ ያፋቅራልና ሰውና እግዚአብሔርን የሚያፋቅር የሚያዋህድ መሆኑን ለማጠየቅ ነው። ከዚያውም ዘንድ በስንዲ በወይን ያደረገው ትንቢቱ ምሳሌው ይፈጸም ዘንድ ነው።

ትንቢት - እምፍሬ ሥርናይ ወወይን ወቅብዕ በዝኃ መዝ 4፡7
ተዳሜ ሕይወቱ ለሰብእ እክል ወግይ ወይን ወሥርናይ ሲራ 29:28
ለዘኢይሰቲ ወይነ ምንት ውእቱ ሕይወቱ ሲራ 34 ፡ 26 ተብሉ ተነግሯል።

ምሳሌ፡- እምሳሊሁ ለወልደ እግዚአብሔር የተባለ መልክ ጼዴቅ በስንዲ በወይን ያሰታቱት ነበረ። ዘፍ ዕብ
የጌታም መቀበሉ እንደ ባለመኃኒት ለማስደፈር እንድም አርአያ ለመሆን ነው። እርሱ ሳይቀበል ደቀመዛሙርቱን ብቻ አቀብሏቸው ቢሆን ናሮ ዛሬም ከሀናት ምዕመናንን አቀብለው እነርሱ ሳይቀበሉ ይሄዱ ነበርና ተቀብላችሁ አቀብሏቸው ሲል ጥሚሞ አጣዕሞሙ ይላል ተቀብሉ አቀብሏቸዋል።

ምን ደግና ርኅሩኅ ሊጋስም ቢሆን
ብሉ ብሉ ሚሰጥ ግነው ሥጋውን?
ካንተ በቀር ጌታ የዓለም መድኀን
ደምህን አፍስሰህ ጠጡ ማለትህ
አልነበረም እንዲ ፍቅር አኅብሮህ?
ታዲያ እኛን ዛሬ ምንድር ይሆን ያልከን
በእንደዘስጦችን ልጆችህ ነን እያልን

ነገር ግን ከፈትህ በልባችን ርቱን
ከዙር ስመታህን መቀበል ሲያቅተን
ከዳተኞች ናችሁ አላልከንም ይሆን?
አሁንም አባከህ ቸር አምላካችን
ዛሬ ነገ ሰንል ሞት እንዳይወስደን
አብቃን ለመቀበል ሥጋ ደምህን
አይቻልምና ያለርሱ መዳን

መጋቢት 27 - ሰቅለት

ሥጋውን በኅብስት ደሙን በወይን አስታኩቶ ተቀብሉ ሲያቀብላቸው አከሮስና (የስምዖን ዘለምጽ ሚስት) ዶሮ አሰናድታ አቀረበችለት። የተናገረው ሊፈጸም ግድ ነውና ኅብስቱን ቆርሶ ከወጡ ጠቅሶ ለይሁዳ ሰጠው። ሰይጣን ከኅብስቱ ጋር ተዋሀደው ልቡ በቅናት ነደደ። ሥጋው ደሙ ሰይጣን ያርቃል እንጂ አያሲዝም ነበር። ዳሩ ግን ዕዳ ፍዳ የሚቀበልበት ነውና ሳይበቁ የሚቀበሉ ዕዳ እንደሚሆንባቸው ለማጠየቅ ነው።

> /2/ ወደእዜኒ ዘበልዖ ለዝንቱ ኅብስት መዘስትዮ ለዝንቱ ጽዋዕ እንዘ ኢይደልዎ ደይና ወመትሙፍቶ በልዐ ለርእሱ 1 ቆሮ 11:27

ሂድ ያሰብከውን ፈጽም አለው። ወጥቶ ሄደ።ይሁዳ እንደወጣ ጌታ ዶሮውን በቃሉ ተናግሮ በእጁ ዳሶ ሕያው ከአደረገው በጓላ ይሁዳን ተከትለህ የሚያደርገውን አይተህ የሚናገረውን ሰምተህ ለደቀመዛሙርቱ ንገራቸው አለው። እየበረረ ወጥቶ ተከተለው። ከቤቱ ገብቶ ከሚሰቱ ተኝቶ በዋጋ አሳልፎ ሊሰጠው መከረ። ሄዶም አይሁድን አሳልፌ ብሰጣችሁ ምን ትሰጡኛላችሁ? አላቸው። ሰሞ ሊያሳያቸው ተሰግሞተው ሠላሳ ብር ሰጡት። የተነገረበት ትንቢት ተፈጸመ። ምን ተብሉ ተነግሯል ቢሉ ነቢዩ ዕንባቆም ለማስተማር ሲሄድ የይሁዳ አባት ከባልንጀሮቹ ጋር ከደንጊያ ላይ ተቀምጦ ባልንጀሮቹ ሲነሱለት እርሱ ተቀምጦ አሳለፈው። ሲያስተምር ውሉ ሲመለስ ከዚያው ተቀምጦ አገኘው። እንዳይነሳ ኮርቶ እንዳይቀመጥ ፈርቶ ተሸፋፍኖ አሳለፈው። "ዕብን ዲበ ዕብን ነቢሮ ደንጊያ በደንጊያ ላይ ተቀምጧል፤ ከዚህም ሰው የሚወለደው ዘእቡሁ እልገቱ ዘእሙ ብእሲቱ ወዘእግዚኡ ሜጡ - አባቱን የሚሰልብ እናቱን የሚያገባ መምህሩን የሚሸጥ ይሆናል ብሉ ትንቢት ተናግሮበታል። ከቤቱ ገብቶ ለሚሰቱ በግድ ካልተነሳህልኝ ብሉ እንዲህ አለኝ ብሉ ነገራት እሷም ደግ ያደረግህ መሰልህ? ታላቅ ሰው ሲመጣ ተቀምጠ ማየት ይገባልን? ብላ
ገሠጽችው። ከዚህ በጓላ መገናኘቱን እንተው ብለው መከረው ሲናሩ አንድ ቀን ፈቃደ ሥጋ አቸንፎት ተገናኛት። ይሁዳ ተጸነሰ። በተወለደ ጊዜ በሳጥን አድርገው ከባሕር ጣሉት። ስምዖን አሰቆርቃዊ አግኝቶ አሳደገው።

ካደገ በኋላ ያለበት ሀገር ሰዎች በአባት እናቱ ሀገር ላይ ሊዘምቱ እርሱም አብሮ ዘምቶ ነቢርና አባቱን ከሰልፍ አግኝቶ ገድሉ ሰለበው፤ እናቱንም ከሰፈር ማረካት በግብርም አወቃት። አባቱን ይገድላል እናቱን ያገባል ያለው ተፈጸመ። አንድ ቀን ሲጨዋወቱ የዚህ ሀገር ሰዎች ዘመድ ዘመድ አይሁም? አለችው። ከባሕር ተገኘህ ይሉኛል አላት። አንተ ጉደኛው ነህን? ያ ገድለህ የሰለብሽው አባትህ ነው እኔም እናትህ ነኝ አለችው።

ከዚህ በኋላ ኃጢአታችንን ያስተሰርይልናል ብለው ከጌታ ዘንድ ሄዱ። ኃጢአታቸውን ይቅር ብሎ እርሱን ከ12ቱ ሐዋርያት እርሷን ከ36ቱ ቅዱሳት አንስት ቆጠራቸው። ዳሩ ግን ትንቢት እንደተነገረበት በፍቅረ ነዋይ ተሰቦ በ30 ብር ሸጠው፤ ዘእግዚኡ ሜጡ ያለው ተፈጸመ።

ያም ዶሮ ተመልሶ መጥቶ ያለቅስ ጀመር። ያየኸውን የሰማኸውን ንገረን አለው። አላልፎ ሊሰጥህ ከአይሁድ ሠላሳ ብር ተቀብሏል፤ እነሱም ሾተል ገመድ ይዘው እየመጡ ነው ብሎ ያየውን የሰማውን ሁሉ ነገራቸው። በከንፍህ በረሀ ሰማየ ሰማያት ገብተህ እልፍ ዘመን ኑር አለው፤ በሮ በሮ ገብቷል።

ከዚህ በኋላ ወደ ደብረዘይት ወሰዳቸው። በዚህች ሌሊት ሁላችሁ ትክዱኛላችሁ "እቀትሉ ለናላዊ ወይዘረው አባግኤሁ (ዘካ 13፣7) ተብሎ ተነግሯልና፤ ከተነሣሁ በኋላ ወደ ገሊላ እቀድማችኋለሁ አላቸው። ጴጥሮስ ሁሉም ቢክዱህ እኔ አልክድህም አለ። እግዣ እብለከ ክመ በዛቲ ሌሊት ሥልሰ ትክህደኒ ዘእንበለ ይንቁ ዶርሆ- ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ብሎታል።

ወደጌቴሰማኒ(ን) ገብቶ ጴሮስን፤ ያዕቆብንና ዮሐንስን ጥቂት እልፍ አድርጎ ሰምንቱን ራቅ አድርጎ ይጸልይ ጀመር። ሲጸልይም አ አቡየ እመሰ ይትከህል ይኅልፍ እምኔየ ዝንቱ ጽዋዕ - ቢቻልስ ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ ነገር ግን ፈቃደ ዚአከ ይኩን ወአኮ ፈቃደ ዚአየ ያንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ የእኔ አያሁን አለ። ደካማ ሥጋን እንደተዋህደ ለማጠየቅ ነው። ወደደቀመዛሙርቱ ቢመለስ ተኝተው አገኛቸው። አንድ ሰዓት እንኳ መትጋት ተሳናችሁን? ትግሡ ወጸልዩ ከመኢትግሉ ውስተ መንሱት - ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ አላቸው። ሁለተኛም ቢመለስ ተኝተው አገኛቸው።

በሦስተኛው ጉሙ እንከ ወአእርፉ እንግዲህስ ዕረፉ አላቸው። ተንሥኡ ንሑር ናሁ በጽሐ ዘያገብእኒ የሚያሲዘኝ ይሁዳ መጥቷል ተነሡ እንሂድ አላቸው። ይህንንም ሲናገር ይሁዳ ሾተልና ጎመድ ከያዙ አራት ቤት ጭፍራ ጋር ደረሰ። መነ ተኀሥሡ ማንን ትፈልጋላችሁ? አላቸው። ኢየሱስሃ ናዝራዊ አሉት አነ ውእቱ እኔ ነኝ አላቸው ገብኡ ድኅሬሆሙ ወወድቁ ዲበ ምድር ይላል - የኋሊት ወደቁ። ሁለተኛም እንዲሁ ሆነ በሦስተኛ የምትፈልጉት እኔን ከሆነ እኒህን ተውአቸው አላቸው። ይሁዳ ቀርቦ በሰከ ረቢ .. መምህር ሆይ ሰላም ላንተ ይሁን ብሎ ሳመው። አ ይሁዳ በስሜኮኑ ታገብእ ለወልደ እጓለ እመሕያው የሰውን ልጅ በመሳም አሳልፈህ ትሰጠዋለህን? አለው። ሊይዙት ተረባረቡ ወበ መጥሳሕት ለስምዖን ጴጥሮስ ይላል ጴጥሮስ ሰይፉን መዘዘ የግልኮስን ቀኝ ጆሮ ቆረጠው ዋይ አለ፤ ጌታ አግብኣ ለመጥህትከ ውስተ ቤታ አለው። ያንንም በእጁ ዳሰ ፈውሶታል።

ከዚህ በኋላ አስረው እየደፉ እያዳፉ ወደ ሐና ወሰዱት። ጳውሎስ የተባለው ሳውል በዚህ ጊዜ ጌታን ከሚያሰቃዩት አንዱ ነበር። ልቡን በጭግ ረገጠው። እንደጠፋ ከእጅህ ገብቼ ሳለ ለምን ይህን ያህል ከፉ ታደርግብኛለህ? ኋላ ግን ከክፉትህ ትፀፀታለህ፤ የበተንከው መንጋዬንም ትሰበስባለህ አለው።

ሐና ምን እያልህ ታስተምራለህ? አለው። በውኑ በሰውር የተናገርሁት አለን? የሰሙኝን ጠይቅ አለው። አንዱ ጭፍራ "ከመዝኑ ትትዋሥኦ ለሊቀካህናት" ብሎ ፊቱን ፀፋው። ክፉ ከተናገርሁ መስክርብኝ በጎ ስለተናገርሁ ግን ስለምን ትመታኛለህ? አለው። ከዚህ በኋላ ወደ ቀያፋ ወሰዱት።

ጴጥሮስ ከሩቅ እየተከተለ መጥቶ ከሊቀካህናቱ ግቢ ተቀምጦ ነበር። ሳጃፍ ጠባቂዋ በለሲዳ "አ አረጋዊ ብእሲ አንተሁ እምገሊላዊ ብእሲ ከደቀመዛሙርቱ አንዱ አይደለህምን? አለችው። ደንግጦ ኢየአምሮ ለውእቱ ብእሲ - አላውቀውም አለ። ሁለተኛ የግልኮስ ወንድም ኮልሰብ - "ከርሱ ጋር በእትከልቱ ቦታ አላየሁህምን?" አለው አላየኽኝም ብሎ ካደ። ሦስተኛ አንዲቷ መጥታ "አንተኑ ረድኡ ለገሊላዊ ኢየሱስ ታልከ የዐውቀከ - የኢየሱስ ደቀመዝሙር ለመሆንህ ንግግርህ ያስታውቃል" አለችው፤ አላውቀውም እያለ

ይምል ይገዘት ጀመር። ወዲያው ዶሮ ጮኸ "ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ" ያለውን አስታውሶ አምሮ አለቀሰ።

ጌታም ሌሊቱን ሲደበድቡት አድረው መከራ ሲያጸኑበት ሌሊት ተሠወራቸው። ከሕዋረ ሰሎሞን ሲደርስ የይሁዳን ዘመድ ልጇን ታቅፋ አግኝቷት "አይሁድ እኔን ሊፈልጉ መጥተው ቢጠይቁሽ ከርሱ ምን አላችሁ? በያቸው" ብሏት ከዓምዱ ስር አረፍ አለ። አይሁድ ተከታትለው መጥተው "አላየሽውምን? አሏት። በእጇ አመለከተቻቸው። ይዘው እያዳፉ አመጡት። "አንቺ ሴት አትንገሪ ብልሽ ጥቂት ራሴን እስካሳርፍ መታገሥ አቃተሽን? በዳግም ምጽአቴ አሥነስቼ እስክፈርድብሽ ደንጊያ ሁኚ" አላት፣ ደንጊያ ሆና ቀርታለች።

በነግህ አሰፈርደው ሊሰቅሉት ወደ ጲላጦስ ወሰዱት። ይሁዳ እሱ በተአምራት ይድናል እኔም ብሬን እንደያዝኩ እቀራለሁ ብሎ ሽጠት ነበርና ይህን ሲያይ አረት "ኢትቅትል ብእሴ ጻድቀ" ያለችውን ተላልፈ ንጹህ ያም አላልፈ በመስጠቱ መልካም አላደረግሁም፣ ብራችሁን እንኩና ፍቱት አላቸው። እኛማ የፈለግኸውን ሰጥተንሃል የፈለግነውን አግኝተናል አሉት። ከእግራቸው በትናት ሄዶ ከዛፍ ተሰቀለ። ወደኋላ ሸሸችው። ከሌላ ዛፍ ሄደ። ገመድ አስሮ ሊታነቅ ሲንጠላጠል በቃል ሰብአዊ" ግረኝ ብትለው ይምርህ የለምን? ኑሕ ከመእጉከ ጴጥሮስ - እንደ ጴጥሮስ ንስሓ ግባ" አለችው። እርሷን ትቶ ከሌላ ዛፍ ሄዶ ተሰቀለ፣ ገመዱ ተበጥሶ ከመሬት ወደቀ። ሰውነቱ ቆስሎ በአርባ ቀኑ ሞቷል።

አይሁድም ጌታን ይዘው ከጲላጦስ ሲገቡ ከሀውደ ምኩናን ስድስት አርማህ (ጠረኞች) ቆመው ነበር። መለስ ብሎ ሲያያቸው እንደግንድ ተረብርበው ሰገደሉት። ከኢየሱስ ወዳጆች ተመሳጥረው ነው። በአሥር በአሥር ኃያላን ይያዙ አሉ ተያዙ። ሲያያቸው አሁንም እነርሱን አቸንፈው ሰገዱለት። በአስራ አምስት በአስራ አምስት አሲያዟቸው። ዘጠናው ስድስቱን ማቆም ተሰኟቸው ተንተው ወድቀዋል።

ጲላጦስ ፍርሀት ፍርሀት አለው። "ካውኑ የአይሁድ ንጉሥ ነህን?" አለው። "አንተ ትቤ - አንተ አልህ" አለ። አይሁድ "ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ ያደረገ፣ ሙሴንና አራትን ያቀለለ፣ ሰንበትን የሻረ፣ ለቄሣር አትገብሩ ያለ ሀሳዊ እንጂ ንጉሥ አይደለም" አሉ።

"ይህን ያህል ሲከሱህ አትሰማምን? "አለው፣ ዝም አለ። "ብየ ሥልጣን እትትልከ ወአሕጸከሂ ልገድልህ ወይም ላድንህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን? አለው። "እምአይቴ ለከ ሥልጣን ትትትለኒ ወታሕይወኒ እምኢተውህበ ለከ እምሰማይ ከሰማይ ካልተሰጠህ በቀር ልትገድለኝ ወይም ልታድነኝ ሥልጣን ከወዴት አለህ?"አለው አይሁድን እኔስ አንድ ሰንኪ በደል አላገኘሁበትም። ገርፌ ልፍታው አላቸው። ከገሊላ ጀምሮ እስከዚህ ድረስ መላ አይሁድን ሲያውክ የነበረ አይሰቀልም ትላለህን? አሉት። ገሊላዊ ከሆነማ ገሊላ ግዛቱ የሄሮድስ ነውና ወደርሱ ውሰዱት አለ።

ሄሮድስም ዜናውን እየሰማ ሊያየው ይመኝ ነበርና ደስ አለው። ዳሩ ግን ቢያናግረው የማይናገር ሆነ። አስተአዘኮ ይላል አስከፍቶ "አይቻልም እንጂ ቢቻልስ ሁለት ሞት ይገባዋል" ብሎ ወደ ጲላጦስ መለሰው። ከዚያ በፊት ጲላጦስና ሄሮድስ ተጣልተው ይኖሩ ነበር፣ አሁን ግን በጌታ ምክንያት ተነጋግረዋል።

ጲላጦስ ጌታን አዝኖ ሲያየው ሄሮድስ ብዙ እንዳሰገረፈው አውቆ አዘነ። "ይህን ሰው ወደኔ ሦስት ጊዜ አመጣችሁት፣ እኔ ግን መርምሬ ስንኪ ለሞት ለማርፋት የሚያበቃ ጥፋት አላገኘሁበትም፣ አሁን ግን ለበዓል አንድ እስረኛ ልፈታላችሁ ልማድ ነውና ገርፌ እፈታዋለሁ አላቸው። "አኮ ዘንተ አላ በርባንሃ - በርባንን እንጂ ይህን አይደለም" አሉ። በዚህ ጊዜ ከሚስቱ ከአብሮቅላ "ድኅ የነበሩ ልጆችህን መካራና ዳርታን እንደበታቸውን ከፍቶላቸዋልና ክፉ እንኳ እንደተናገረው እወቅ "የሚል መልእክት ደረሰው። አይሁድ በሥራዩ ነው ሲሉ ጌታ ከርታሱን ተቀብሎ የተጻፈውን ደምስሶ "ዋጋሽን በመንግሥተ ሰማያት እከፍልሻለሁ ልጆችሽንም ከሰማዕት አቆጥርልሻለሁ" ብሎ መልሶታል።

ይህን አይቶ ጲላጦስ ሊፈታው ፈለገ። እነርሱ ግን እመአሕየውኮ ለዝንቱ ኢኮንክ ዐርኮ ለቄሣር - ይህን ከፈታህ የቄሣር ወዳጅ አይደለህም ስቅሉ ስቅሉ - ብለው ይፍጀጁ ጀመር። ውኃ በኩስኩስት አስመጥቶ ንጹህ እኔ እምደሙ ለዝ ብእሲ ጻድቅ - ብሎ እጁን ታጠበ። አይሁድ ግን ደሙ ላዕሌነ ወላዕለ ውሉድነ ደሙ በእኛና በልጆቻችን ይሁን አሉ። ይህም ሊታወቅ ዛሬ አይሁድ ሲወለዱ ደም ጨብጠው እንደሚወለዱ ይነገራል።

ከዚህ በኋላ ከሏላመስ ተቀብለው ከግንድ አስረው አራት ከአርባ አትርፈህ አትግረፍ ትላለችና ሠላሳ ዘጠኝ ገርፈው ዘንጋውን እያሉ እየተቀባበሉ አራቱ ጭፍሮች 6666 ጊዜ ገርፈውታል፤ ሥጋው አልቆ አጥንቱ እስኪቆጠር።

የሾህ አክሊል ጎንጉነው ከራሱ ደፍተው በመቃ ቢመቱት ራሱ ሰባ ሶስት ጊዜ ተበሳስቷል። መስቀሉንም ሦስቱን እንጨቶች ዕፀ አውልዕ ፣ ዕፀ ወይን፣ ዕፀ ዘይትን እና አራቱ ዕፀወ በለስን አንድ ወገን አድርገው ቁመቱ ሰባት ክንድ ከስንዝር፤ ወርዱ ሦስት ክንድ ከስንዝር አድርገው ሠሩ። ዕፀ በለሱ ሰሎሞን ንስር አልገዛለት ብሎት ግልገሉን ከግንብ ውሥጥ ዘግቶበት ሳለ ንስር ከጎጎት አምጥቶ ግንቡ ላይ ጥሎት ግንቡን ሰብሮ ግልገሉን ከወሰደ ፀኋላ በአትክልት መካከል ተተክሎ ቆይቶ ቤተመቅደስ ሲሰራ እንደባርያ የሚገዙለት 700 አጋንንት ሊቆርጡት ሲሉ እንደእሳት ፈጅቷቸው አርሱም ለመቃንም፤ ለመድረክም አልሆን ብሎት ሳይቆርጠው ትቶት ከደጃፍ ወድቆ የነበረና የሀገራችን ንግሥት ማክዳ ጥበቡን ልታይ ወደርሱ በሄደች ጊዜ ዘንዶ ስታስገድል ደሙ ቢነጥብባት እንደ ፍየል ሰኮና ሆኖ የነበረውን ቀርፎ የጣለላት በዚህም ምክንያት ሰሎሞንና እርሷ በአንድ በአንድ ብር ለብጠው ከቤተ መዛግብት ያስቀመጡት ከርሱም በኋላ የተነሡ 28 ነገሥታት ተለምር እያደረገላቸው በአንድ በአንድ ብር እየለበጡት የቆየ ነው:: ሠላሳውን ብር ለይሁዳ ሰጥተው ግንዱን ለመስቀል አድርገውታል።

በስድስት ሰዓት ቀደ ግምጃ አልብሰው ግራ ቀኝ ፈት ኋላ ሆነው እየዘፉ እያፍሩ ወሰደው በማዕከለ ምድር በቀራንዮ ሰቀሉት። በቀራንዮ መስቀሉም ትንቢቱ ምሳሌው ይፈጸም ዘንድ ነው። ትንቢት "ወገብረ መድኃኒተ በማዕከለ ምድር" ተብሎ ተነግሯል። መዝ 73:12

ምሳሌ:- እስራኤል መና ከደመና እያወረደ ውኃ ከጭንጫ እያፈላቀ ይህንን እየመገበ ደጋ ደጋውን ሲወስዳቸው "ሐመይዎ ለእግዚአብሔር ወይ ቤሉ ይክልኑ እግዚአብሔር ሠረፀ-ማዕድ በገዳም ይዝብጥ ኩኩሐ ወያው ጎዝ ማየ" መዝ 77:19 እንዲል-ቆላተ ዮሳፍጥ ከሚባል በረሀ አውርደ መናውንም ውኃውንም ከወትሮው አብልጦ ሰጣቸው። ፋሩ ግን እባብ ጎናቸውን እየቀደደ ይፈጃቸው ጀመር። ሙሴ ወደጌታ ሲያመለክት አርዌ ብርት ሠርተህ ተራዳ ላይ ሰቅለህ አይተው ይዳኑ አለው። እንዳለው ሆኗል። ተራራው የቀራንዮ ተራዳው የመስቀል ብርት የጌታ እባብ የዲያብሎስ ቁስሉ የኃጢአት በረሀ የሲኦል፤ አይተው አምነው የዳኑ የሐዋርያት የምእመናን፤ አይተው ያልዳኑ የአይሁድ የመናፍቃን ምሳሌ።

ሊሰቅሉትም መጎናፀፊያውን፤ኩፋሩን፤ ጠፈሩንና መነሳነሱን ለአራት ተከፋፍለውታል። ቀሚሱን ግን ሰብአ ሰገል የገበሩለት ስፌት የሌለው ሥረጽ ሲያድግ የሚያድግ ገባሬ ተአምር ነውና ኢንሰጥዋ ወኢንግምድ እላ ንትፋሰስ ላዕሌሁ ለዘረከቦ ይርከቦ ብለው ዕጣ ተጣጥለውበታል።

ሰቀሉ ምስሌሁ ክልዔተ ፈያተ አሐደ እምለፌ ወአሐደ እምለፌ ይላል ጥሶን በቀኙ ዳክርሰን በግራው ሰቀሉ። "ተኖለቈ ምስለ ጊጉያን" /ኢሳ 53:12/ ተብሎ ትንቢት ተነግሯልና። ኢላመስም ከራሱ በላይ በቀረው ስንዝር ያህል "ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሠ አይሁድ" ብሎ በዕብራይስጥ በጽርዕ በሮማይስጥ ጻፈበት።

በተሰቀለም ጊዜ ሦስት በሰማይ (ጠፍር) አራት በምድር ሰባት ተአምራት ታይተዋል። በላይ የፈጣሪያችንን ዕርቃን አናሳይም ብለው ፀሐይ ጨልሟል፤ ጨረቃ ደም ሆኗል፤ ከዋክብትም ረግፈዋል። በምድርም አዕባን ተፈትተዋል፤ መቃብራት ተከፍተዋል፤ ከ500-1000 የሚሆኑ ሙታን ተነሥተዋል፤ የቤተመቅደስ መጋረጃ ከሁለት ተከፍሏል። መከራው እጅግ ጽኑ ነው፤ ሕማማቱንም ሊቃውንት በቁጥር 13 ብለው አስቀምጠዋቸዋል።

እነርሱም 1. ተአስሮ ድኅሪት
2. ተስሕቦ በሀብል
3. ወዲቅ ውስተምድር
4. ተከይዶ በእግረ አይሁድ
5. ተገፍዖ ማዕከለ ዓምድ
6. ተጸፍዖ መልታህት
7 ተወከፎ ምራቀ ርኩሳን
8. ተኮርዖተ ርከሰ
9. አክሊለ ሦክ
10. ፀሮረ መስቀል
11. ተቀንዎ በቅንዋት
12. ተሰቅሎ በዕፅ እና
13. ሰሪበ ሐሞት ናቸው።

እነሆን ትኩሳቱን አብርዱልኝ ከመከራው አስታግሱኝ ላይል በትሕትና በትዕግሥት ተቀብሏል። "አ ትዕግሥት ዘኢከሠተ አፋሁ በሕግሙ በቅድመ እለይረግዝም" እንዲል ቅዳ. ግር ቁጥ 126 ይህማ አንዲት ቃል ሰንኳ አልተናገረም ማለት አይደለምን? ቢሉ

የትዕቢት የፍርሃት ቃል አልተናገረም እንጂ አሠሩን ለሚከተሉ አብነት ሊሆን ሰባቱን አጽራሐ መስቀል ተናግሯል።

እነርሱም

1. አምላኪየ አምላላየ ነጽረኒ ወለምንት ኀደገኒ
2. አባ ሥረይ ሉሙ ኃጢአቶሙ አስመበዘኢየአምሩ ይገብሩ ሉቃ23-33 በመላእክት ያመጣዋል። አካሉ ደም ለብሶ እርቃኑን ተሰቅሎ አይተውት ደንግጠው እንዲሸሽ ተነጸፉ። ቅዱስ ሚካኤል ዝም አለ፤ ቅዱስ ገብርኤል ግን ተቆጥቶ ሊያጠፋቸው ሰይፉን መዘዘ። ባያውቁ ነው ሰ ይፍህን መልስ አለው። "ሚካኤል አርመመ ወገብርኤል ተደመ" እንዳለ ቅዱስ ያሬድ ቸርነቱን እያደነቀ ቢለቀው የቤተመቅደስን መጋረጃ ከሁለት ከፍሎ ምድርን ሰንጥቆ ገባ እስከ ምጽአት ሲወርድ ይኖራል። ሶቤ ከልዐቶ ምሕረቱ ለአብ ወጊሩቱ ለወልድ ወትዕግሥቱ ለመንፈስ ቅዱስ ዘበጠ ለመንጠላዕተ ምኩራብ ወረሰዮ ክልዔ ከፍለ "እንዲል ሃይ አበ ዘአትና ክፍል 9
3. ነዋ ወልድኪ ወነያ እምከ ዮሐ 19፡26 ጊታ በተሰቀለ ጊዜ እመቢታችን ዮሐንስ ነግሯት እየወደቀች እየተነሳች መጥታ ከእግረመስቀሉ ሆና ስታለቅስ ገናማ ሐሞት ሲያጠጡኝ በሰር ሲወጉኝ ብታይ በኃዘን ትሞት የለምን? ብሎ እናቱ ሆይ ልጅሽ እነሆ አላት፤ ዮሐንስንም እነኋት እናትህ ልጅ ሁናት ብሎ አደራ አቀባበለ። ይህም ለጊዜው ለዮሐንስ ቢሆን ፍጻሜው ለሁላችን ነው።
4. ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ ማቴ 27፡46 አይሁድ ኤልማስ ሲል ኤልያስ ያለ መስሏቸው ኤልያስ መጥቶ ሳያድነው ይሙት ብለው ሆሞተ ነጊ አጠጥተውታል። ጲላጦስም እምላኪ ካለማ ፅሩቅ ብእሲ ነው ብሎ ነፍሱን ከሥጋው ሊለይ በድፍረት ቀረበ። ጊታ ባአውታረ ነፋስ ወጥሮ መኑ አንተ መኑ ዝንቱ እያለ አስቀባጥሮታል።
5. ዮም ትሄሉ ምስሌየ ውስተገነት ሉቃ 23፡43 በቀኙ የተሰቀለው ጥሶ ሰባቱን ተአምራት አይቶ እምላክነቱን ተረድቶ ተዘከረኒ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ ተዘከረኒ አመላንም ምጽአትከ እያለ ሲማፀነው ፋክርስ ለራሱ ጻዕረ ሞት ይዞት ያስጨንቀዋል አድነን ትለዋለህን? አለው። እርሱም እኛ ብንሰቀል በኃጢአታችን ነው እርሱ ግን ለቢዛ ዓለም ብሎ ቢሰቀል አምላክን አትፈራውምን ብሎ ገሠጸው። ጌታም ራሱን ወደ ጥሶ ዘንበል አድርጎ ወደ ገብጽ ሰንወርድ የነገርከህ ሁሉ ተፈጽሟል ፤ ከሞት በቀር የቀረ የለምና ሂድ ነነት ግባ ብሎ በደሙ አትሞ ላከው።ወለግታ ለሰራዊ ዘየዐቅብ ፍኖዕፀ ሕይወት ወአለተተ እምእዴሁ ኩናተ እሳት ይላል ጠባቂዋ ሱራፌ ፈርቶ እየጀሸ አንተ ማነህ? ወዴት ትሄዳለህ?

አለው። አምላክ ሰው ሆኖ ተሰቅሎ በሞቱ ዓለምን አዳነ ለእኔም ደመግኅተሙን ሠጥቶ ላከኝ አለው። አዳም ነህን አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብ ነህን? አለው። አይደለሁም እጁን በሰው ደም ነክሬ የናርሁ ሽፍታ ነኝ። ሰባቱን ተአምራት አይቼ አምላክነቱን ተረድቼ ብማፀነው ለዚህ ክብር አበቃኝ ብሎ 5493 ዘመን ተዘግታ የነበረች ገነትን በደመ ማኅተሙ ከፍቶ ገብቷል።



6. አባ አመሐጽን ነፍስየ ውስተእዴከ ሉቃ 23፡46
7. ተፈጸመ ኩሉ ዮሐ 19፡30 በነቢያት የተነገረው በመጽሐፍ የተጻፈው ሁሉ ደረሰ ተፈጸመ ሲል ነው። እኒህን ተናግሮ ራሱን ወደቀኝ ዘንበል አድርጎ ቅድስት ነፍሱን በሥልጣኑ ከክብርት ሥጋው ለየ።

በሲኦል የነበሩ ነፍሳት በአካለ ነፍስ ወርዶ የተወጋ ጎኑን ቀኝ ክንዱን አሳይቷቸው ይሽው ጥምቀት ቁርቧን ሆናቸው ዲያብሎስ በዕ ብነ ሩካም ጽፎ ያኖረውን የዕዳ ደብዳቤ አጥፍቶላቸው ስብሐት ለእግዚአብሔር ዘአውረሰን መንግስቶ ሰማያዊተ እያሉ እያመሰገኑ ወጥተው ገነት ገብተዋል። “”ወጎደገ ሥጋሁ ሰቁለ ዲበዕፀ መስቀል ወነፍሱሰ ወረደት ውስተሲኦል ወፈወሰት ነፍሳተ እለሀለው ህየ ወጌወጠት ሲኦለ ወአግዐዘት ኩሉ ፍጥረታተ “እንዳለ አትናቴዎስ በሃይ.አበ.

ነፍሱ ከሥጋው ከተለየ በኋላ ለንጊኖስ የሚባል ሐራዊ ቀኝ ጎኑን በጦር ወጋው። ውኃና ትኩስ ደም መንታ ሆኖ ፈሰሰ። ደሙን መላእክት በጽዋዐ ብርሃን ተቀብለው በዓለሙ ሁሉ ረጭተውታል። ለንጊኖስ አንድ ዓይና ነበር፣ ደሙ ቢነተብበት ብርቶለታል። ኋላም ትንሣኤውን አይቶ መስክሮ በሰማዕትነት አርፏል። ወዘርዕየ ስምዐ ኮነ ወጽድቅ ውእቱ ስምው እንዲል ዮሐ 19፡35

ወነሥኡ ሥጋሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ወገነዝም በመዋጥሕ ዘሰንዱናት ይላል በ11፡00 ሰዓት ዮሴፍ ዘአርማትያስና ኒቆዲሞስ ከጲላጦስ አስፈቅደው ሥጋውን ከመስቀል አውርደው ሽቱ እየረበረቡ በሐዲስ በፍታ ገነዙት። ሲገንዙትም ወአንበአበሰ አፅይንቲሁ ይላል ዓናቹን ግልጽልጽ አድርጎ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት እያላችሁ ገንዙኝ ብሏቸው እንዲሁ እያሉ ገንዘውታል። አክብራችሁ ስማችሁ እንደገነዛችሁኝ እኔም አክብሬ ዘሰማያዊ ዕንቁ መንበር እናራችኋለሁ ብሎም ተስፋቸውን ነግሯቸዋል።

ከዚህ በኋላ በሦስተኛ ቀን የሚነሣ ነውና የኤልሳዕ አጽም ሙት እንዳነሳ ከነቢያቱ የአንዱ አጽም አነሣው እንዳይሉ ዮሴፍ ለራሱ ባሠራው ሰው ባልተቀበረበት አዲስ መቃብር ቀብረውታል። ዮሐ. 19፡ 41

ምላክ እንደእንግዳ ወደዓለም ቢመጣ በልጅሽ መሰቀል መከራሽ ቢበዛ
ይንና ወተቱ ብርዙ ሳይታጣ እንባሽ ጎርፍ ሆኖ ሲወርድ እንደዋዛ
ስታሞች አይሁድ አሉት ሐሞት ጠጣ። ውበት ደምግባትሽ ሲረግፍ እንደጤዛ
ዝና እንዳትቀር በገሃነም ነፍስ ማነው እይዞሽ ያለሽ የቱ ልብ የገዛ
ላም በበደለ ሞተ ክርስቶስ። አንቺው ቻልሽው እንጂ ልብሽ በጎዘን ፈዛ።
መስቀል ተሰቅሎ ያልእንዳች ጥፋት ጻድቅ ተከንና ኃጥኡ ሲጸድቅ
ሕያዋን አምላክ እንደምን ይሙት? ሐቀኛ አልቅሶ ውሸታም ሲስቅ
ሚሰግዱለትን ፈርተው መላእክት ቀማኛው ሲደሰት ለጋስ ሲሳቀቅ
አይሁድ በእንጨት ሰቅለው በጦር ሲወጉት ምን አልሽ ይሆን ዓለ ም ምንተናግረሽ ሐቅ?
በቸንካር ቸንክረው ደሙን ሲያፈሱት ምድራቱ ዝም እትበይ መስከሪ ሀቁን
ሬታ ደም ብትሆን ፀሐይም ጽልመት ጎባጣውን ማቅናት ማንሣት ምውቱን
ከዋከብት ቢረግፉ ብትርድ መሬት ያሸልግል እንጂ ያሰቅላልን?
አይበዛም ቢያንስ እንጂ እሪ ቢል ፍጥረት። ምስጋና ይድረሰው ክብር ይግባው አሜን
ች ክፋ መቃብር ምሕረት የሌላት በሞቱ ገድለው ጨካኙ ሞትን።
ንቱን ጻድቅ ውጣ አልበቃሽ ያላት ሲአል ጦም አደረች አጋንንት አፈሩ
ጣላት ጌታዋ ዛሬስ ይውጣላት ምርኳቸው ተነጥቆ ባዷቸውን ቀሩ።
አንቺ ተንከራታች ድንግል የኔ ቤዛ

ኢሳ 25:8 ፤ ቆሮ 15:54 ፤ ጴጥ 3:18

ለ- ዕረፍቱ ለአባ መቃርስ ዘየዐቢ

መቃርስ (መቃርዮስ) ማለት ቅዱሱ ለእግዚአብሔር ማለት ነው። ሀገራቸው ሳሱዊር ነው። አባታቸው አብርሃም እናታቸው ሣራ ይባላሉ። አባታቸው ካህን ነበር። የተወለዱት በብስራተ ኪሩብ ነው።

አካለ መጠን ሲያደርሱ ግድ ብለው ይህ ቀረሽ የማትባል ቆንጆ አጭተው አጋቧቸው። በድንግልና ለመኖር ይሹ ነበርና አመመኝ ብለው ከቤተ እግዚአብሔር ገብተው ከዚያ ሰነበቱ። ሲመለሱ ሙሽራት ሞታ አገኙ። እርሷን በድንግልና ሳለች የወሰዳት እኔም ከእዚሁ እንድኖር ፈቅዶ ነው ብለው ደስ አላቸው።

አባት እናታቸውም ብዙ አልቆዩም ተከታትለው አረፉ። ንዝናቸውን ከዜሩ በኋላ ያለውን ሀበት ንብረት ሁሉ ሰጥተው መጽውተው ማዕ ፈግቶና ተቀብለው ከቤተእግዚአብሔር በዓት ሠርተው ተቀመጡ። ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ግብራቸውን ጠልቶ ሞታቸውን ሽቶ ላቸ አነሳባቸው። ለሀገሩ ባላባት አንዲት የደረሰች ልጅ ነበረችው

በዝሙት ጸነሰች። ልጇ ምነው እንዲህ አደረግሽ ብሎ አዘነ። ሰይጣን ለጸሀፉ ምክንያት አድርጎ መርሚታልና ቤተእግዚአብሔር እጅ ልነሳ ብሂድ አባ መቃርስ እንዲህ አደረገኝ አለች። ተቆጥቶ ሂዶ እጅ እግራቸውን አስሮ ይገርፋቸው ጀመር። ይህን ያህል የምትገርፈኝ ምን በደልሁህ? አሉት። በደልህንማ አንተው ታውቃለህ ብሎ ሥጋቸው እስኪተፈተፍ ድረስ አብዝቶ ገረፋቸው።

ይህም አልበቃ ብሎት በሰንሰለት አስሮ እየጎተተ ሲወስዳቸው ሁለቱ መላእክት በአምላለ ወራዙት ቀርበው ምን አጥፍተ ነው። አሉት። ልጇን አስነውሮ እኔን አሳፍሮ ነው አላቸው። ይህንንስ እንደማያደርግ እናውቃለን፤ ባይሆን እስክትወልድ ድረስ ልብሷን ቀለቧን ይሰጣል በዋስ አሰናብተው አሉት። ማን ይዋሰዋል? አለ። ሕማማቸውን አይቶ ያዘነ አንድ መንገደኛ እኔ እዋሳለሁ ብሎ አስለቀቃቸው።

ከቁስላቸው ሲድኑ መልአኩ መጥቶ ለዚያች ሴት ቀለቧን ልብሷን አትሰጥምን? አላቸው። ቅርጫት እየሰሩ ሸጠው ሲሰጧት ቆዩ። የመውለጃ ጊዜዋ ሲደርስ ምጥ ፀንቶባት አራት ቀን ተጨነቀች። እናቷ ልጇ ጌታን ያስቀየምሽው ነገር እንዳለ አለቻት። የአባቴን ቁጣ ፈርቼ እንጂ የጸነስኩት ከአባ አይደለም አለች። ያን ካህን በከንቱ አስቀይመነዋል አሁንም ሳትሞት እንማጸነው ብለው ሲሄዱ በመንፈስ ቅዱስ ተገልጠላቸው ይህማ ውዳሴ ከንቱ ሊሆንብኝ ነው ብለው ከበዓታቸው ወጥተው ሲሸሹ መልአኩ በክንፉ ነዋቆ ገደመ አስቂጥስ አድርሷቸው ይህ ቦታ የአንተና ልጆችህ ነው። እንዲህ አድርግ እንዲህ አታድርግ ብሎ ሥርዓት ሠርቶባቸዋል።

አጋንንት እየተፈታተኑ ቢያስቸግራቸው መልአኩ መርቶ ከአባ እንጠንስ አገናኛቸው ሥርዓተ ምንኩስና ተምረው ተመለሱ ኋላም አባ እንጠንስን ገንዘው ቀብረዋል። ከዚህ በኋላ ግን መከራውን በትሰ ግሥት ሰይጣንን በጸሎት ድል ነሥተውታል። አንድ ቀን አጋንንት ከበዓቱ ደጃፍ አሳት አንድደው ፍህሙን እየታፈኑ ይጥሉባቸው ጀመር። ስመ እግዚአብሔር ጠርተው ቢያማትቡባቸው እንደ ጢስተነው እንደ ትቢያ በነው ጠፍተዋል። ኋላም ጌታ ስነገድላቸው እንዲገለጽ ብዙ ደቀመዛሙርትን አመጣላቸው፤ ሥርዓተ ምንኩስና አስተምረዋቸዋል።

በዘመናቸው በሀገረ አውሲም ትንሣኤ ሙታን የሚል መናፍቅ ባሕታዊ ተነሥቶ ምእመናንን ሲያስተምር ሄደው ወንድሜ የዘሩት ሲበቅል የተከሉት ሲጸድቅ አላየህምን ብለው በምሳሌ አስተምረው አንድ ሙትም አሥነስተው አሳይተው አሳምነውታል። በመጨረሻም በስማቸው የተማጸነ ከዕዳ ከፍዳ እንደሚድን ተስፋቸውን ተቀብለው በተወለዱ በ97 ዓመታቸው በዚህ ዕለት አርፈዋል።

- የነበሩት በ4ኛው ም.ዓ. ድ-ል-ክ ነው።

ቅዱስ መቃርዮስ የመንፈስ አርበኛ
በጸሎት ድል ነሣው የሰውን ደመኛ።
የዓለም ብልጽግና ማለፉን አስቦ
በትኅርምት ኖረ በአራዊት ተከቦ።
የጠላት ፈተና መሆኑን ተረድቶ
ሲገርፉት ዝም አለ በትዕግሥት ፀንቶ።
በአምላክ ዘንድ ከፍ ቢል ክብርና ሞገሱ
የሚያኰገረው መልአክ ነበር ለርሱ።
ያለኃጢአቱ ሰውን ማስቀየም
የኋላ የኋላ ያመጣል መረገም።
በመልካም እንድትኖር ሳያገኝህ ፍላ
ፈጽሞ አታስብ ማንንም ልትጎዳ።

ኢሳ1፡16 1 ተሰ 5፡15 2 ቆሮ 13፡7

መጋቢት 28 ሀ. ቀዳም ስዑር

ዐባይ ሰንበት፣ ቀዳም ስዑር ትባላለች። ዐባይ ሰንበት መባሏ ጌታ በጥንተ ፍጥረት ከእሑድ እስከ ዓርብ ሲድስቱን ቀናት ሲፈጥር ሰንብቶ በሰባተኛዋ በቀዳሚት አልፈጠረም። ዕረፍባት ሲል ሥራውን ፈጽሞ አርፎባታል። ወእእረፈ እግዚእነ እምኩሉ ዘአኀዘ ይግበር እንዲል ዘጸ 20፡11

5500 ዘመን ሲፈጸምም ከሰማያት ወርዶ ከድንግል ተወልዶ ሰው ሰውኛውን ኖሮ የማዳኑን ሥራ ዐርብ በመልዕልተ መስቀል ፈጽሞ በአዲስ መቃብር አርፎ ውሉባታልና ስለዚህ ነው።

ስዑር መባሏም ደቀመዛሙርቱ ዓርብ ሕማሙን ሞቱን አይተው እሞታለሁ ብሎን ሕማሙን ሞቱን አየን፤ እነሳለሁ እንዳለንስ ትንሣኤውን ሳናይ እንቀራለን ብለው ከምግብ ተከልክለው ሲያዝኑ ውለዋል። ስዑር መባሏ ብትሻር አይደለምን ብለው ሲሰሩባት ተድላ ደስታ ሲያደርጉባት የሚውሉ ቢኖሩም እውነታው ግን እንዳልነው ሕማሙን ሞቱን እያሰብን የምንጸምባት የምናዝንባት ስለሆነ ነው። በነግህ ካህናት የነግህ ተግባራቸውን አድርሰው ገብረ ሰላመ በመስቀሉ

እያሉ በዘመነ ናህ ርግብ "ሐጸ ማየ አይኅ" "ነትነ ማየ ድምሳሴ" ስትል ቄጠማ የወይራ ቅጠል ይዛ እንደተገኘች "ሐጸ ማየ ኃጢአት" "ነትነ ማየመርገም" ሲሉ ቄጠማ ለምእመናን ያድላሉ።

ለ. ዕተፍቱ ለቈስጠንጢኖስ ጻድቅ (272 - 337 ዓ.ም)

ሀገሩ በራንጥያ (ቁስጥንጥንያ) ነው። አባቱ ቁንስጣ ይባላል። የበራንጥያ ንጉሥ ነበረ። መንግሥት ለማዳረስ ወደ ሰርቪያኒስ ሔደ። ዕሌኒን ከባህር ተጥላ አግኝቷት ሚስቱ አደረጋት። አረሚ ቢሆንም ቅሉ ክፋት የለውም ነበር። ዕሌኒ ግን አረሚ በመሆኑና ልጇን ልታስጠምቅ ባለመቻሏ ታዝን ነበር። ዳሩ ግን ጌታ ዓምደ ቤተክርስቲያን እንዲሆን መርጦታልና ከእናቱ ትምህርተ ክርስትና እየተማረ ከክርስቲያን ጋር እየተባበረ መንፈሳዊ ሆኖ አደገ።

አካለ መጠን ሲያደርስ አባቱ ሥርዓተ መንግሥት አውጥቶለት ዘውድ ደፍቶለት በሁለት ዓመቱ አረፈ። በብራንጥያ ሰባት ዓመት ከነገሠ በኋላ ሮማውያን ንጉሥ መክስምያኖስ አገዛዝ አጽንቶብናልና መጥተህ አድነን ብለው ላኩበት። ሲያስበው ውሉ ሌሊት በሕልሙ "በዝ ትእምርተ መስቀል ትመውየ ለጸርከ - ጠላትህን በዚህ ትእምርተ መስቀል ታሸንፈዋለህ" የሚል ጽሑፍ የተቀረጸበት የብርሃን መስቀል አየ። ምን ይሆን እያለ ሲያወጣ ሲያወርድ የታዘዘ መልአክ መጥቶ እንዳየኸው አድርገህ አሠርተህ ያዝ ታሸንፈዋለህ አለው። ከዘውዱ ጀምሮ እስከ ተራ የጦር ዕቃ ድረስ በሁሉ ላይ መስቀል አስቀርጾ ገጥሞ ድል አድርጎታል።

ከዚህ በኋላ ሮምን ጠቅልሎ መግዛት ጀመረ። በዓመቱ "አብያተ ጣዖታት ይትዐፀዋ ወአብያተክርስቲያናት ይትራኀዋ" ብሎ አውጆ በመክስምያኖስና ዲዮቅልጥያኖስ ዘመን የፈረሱ የተተኮሱ አብያተ ክርስቲያናትን አሠራ፤ የተዘረፉ ንዋያተ ቅድሳትን መለሰ፤ አብያተ ጣዖታትን አፈረሰ፤ ርስት ጉልታቸውን ለቤተክርስቲያን ሠጠ። ይህም በቤተክርስቲያን ታሪክ ለክርስትና እምነት መስፋፋት ከተደረጉ አስተዋጽኦዎች አንዱና ታላቁ ነው።

በኮረ ሰይጣን አርዮስ የተወገዘበት፤ አምስቱ አዕማደ ምስጢር፤ ጸሎተ ሃይማኖት፤ የተረቀቀበት ሌሎችም ድርሳናት የተጻፉበት የመጀመሪያው የሊቃውንት ስብሰባ (ጉባኤ) በኒቅያ የተደረገው በርሱ ዘመነ መንግሥት በርሱ ፈቃድና ጥረት ነው። ሙሉ ታሪኩ በክፍል 1. ገጽ 63

በመጨረሻ ዕለ በዓል ለማየት ኒቆምድያ ደርሶ ሲመለስ ታመመ በሊቀጳጳሳቱ በአባ ሶል ጴጥሮስ ተጠምቆ በተወለደ በ65 ዓመቱ በዚህ ዕለት ዐርፏል። ቈስጠንጢኖስ ጥምቀት ነጭ ልብስ ናት። ደኃ ብበድል ፍርድ ባጓድል አሳድፋታለሁ እያለ ያስብ ነበር። በፍጻሜ ዘመኑም መጠመቁ ስለዚህ ነው። ይልቁንም አብያተ ክርስቲያናትን ከማሠራት ክርስቲያንን ከጥፋት ከመታደግ የበለጠ አለን? ደኃ ብበድል ፍርድ ባጓድል ላልከው ግን ፈቃደ እግዚአብሔር ጠይቀን ሕግ እንሠራልሀለን ብለው ፍትሐ ነገሥትን፤ ግሩም ቅዳሴንና ሕንፃ መነኮሳትን ጽፈው ቢሰጡት እንጂ ሠለስቱ ምዕትን ድኃ ብበድል ፍርድ ባጓድል እናንተ መከራ ተቀብላችሁ የምትገቡባትን መንግሥተ ሰማያትን ልወርስ እችላለሁን መንግሥቴን ትቼ ገዳም ገብቼ እንድኖር አሰናብቱኝ እናንተ የወደዳችሁትን አንግሣችሁ ኑሩ ብሎ ሕልቀተ ወርቁን፤ ሕለተ ወርቁንና አክሊለ ወርቁን ሰጥቷቸው ነበር። ክብሩንም አባ ብሶይ አይተው መስክረዋል። በዓታቸውን ዘግተው ሲጸልዩ ቈስጠንጢኖስ በአካለ ነፍስ መጥቶ ሰላም ለክሙ አ ብውዓን መነኮሳት አላቸው፤ አንተም እንጂ በዘመንህ ቀርነ ሃይማኖት ቆሟልና ብፁዕ ነህ አሉት። ከሄደ በኋላ ለደቀመዛሙርቱ ነግረዋቸዋል።

ዜና አበው

ደግ እናት ዕሌኒ በእምነቷ ጸንታ
ደግ ልጅ አስገኝቶ የሚሆን አለኝታ
ሰላም ለጠገው ሕዝብ ለሚሻ ጸጥታ
ታላቅ ሰው እንዲሆን አምላኩ መርጦት
ለቤተክርስቲያን ሙሶሶ ሆናት።

አልቀረም በክንቱ ቈስጠንጢኖስ ነግሦ
አይተን ደስ ተሰኝን ጠላት ተደምስሶ
መንግሥት የእግዚአብሔር እውቆ መሆኑን
አገለገለበት ፈጣሪ እምላኩን።
ሰዎች እንታበይ በሹመታችን
በሀብት እንመካ አይጠፋ መስሉን
በጎ ልንሠራበት ነው የተሰጠን።

መጋቢት 29 - ብስራት (በዓለ ትስብእት)

ታሪኩ በክፍል 1 መጽሐፍ ገጽ 110 ተጽፏል

ሰ. ትንሣኤ

"ሞተ በፈቃዱ ወተቀብረ በሥምረቱ" ሃይ. አበ. ዘአትና. እንዲል፡፡ በፈቃዱ ሞቶ በውዱ ተቀብሮ ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ከፈቱልኝ ሳይል በገዛ ሥልጣኑ በዘመነ ማርቆስ እሑድ በመንፈቀ ሌሊት ተነስቷል፡፡ "ወተንሣእኩ በሥልጣነ - ባሕቲትየ" እንዳለ ቅ-ቄርሎስ

የተቀበረ ዓርብ በሠርክ የተነሣ እሁድ በመንፈቀ ሌሊተ ከሆነማ 3 ቀን 3 ሌሊት በመቃብር ቆየ መባሉ እንደምን ነው? ቢሉ ዕለተ ዓርብ ከሦስት ታከፍሏል፡፡ ከነግህ እስከ ቀትር ሰዓቱ አራት ነው፡፡ ብርሃን ሆኗል፤ ቀትር ኮነ ሌሊተ ወጸልመ ኵሉ ዓለም እንዲ ሉቃ 23 ፡ 44 አንድ ሌሊት፡፡ ከዘጠኝ እስከ ሠርክ ሰዓቱ አራት ነው ብርሃን ሆኗል፡፡ ሁለተኛ ቀን፤ ሌሊቱ ሁለተኛ ሌሊት፤ ቅዳሜ ቀኑ ሦስተኛ ቀን ሌሊቱ እስከ መንፈቀ ሌሊት ሦስተኛ ሌሊት ነው፡፡ ያውስ ቢሆን የተቀበረ በሠርክ ነው፡፡ እስከዚያ ያለው ስለምን ተቆጠረ ትለኝ እንደሆነ ሕማሙ ሞቱ ቁጥሩ ከዚያው ነውና፡፡

ትንሣኤውን በሦስት ቀን ያደረገው በ2 ወይም በ4 ያላደረገው ስለምንድር ነው? ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ይፈጸም ዘንድ ነው፡፡ ትንቢት - እርሱ ባለቤቱ "እስመ በከመ ነበረ ዮናስ ውስተ ከርሠ አንበሪ ሠሉስ መዋዕለ ወሠሉስ ለያልየ ከማሁ ይነብር ወልደ እጓለ እመሕያው ውስተ ልበ ምድር ሠሉስ መዋዕለ ወሠሉስ ለያልየ" ብሎ ተናግሯል፡፡ ማቴ 12፡40

ምሳሌም ዮናስ ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት በከርሠ አንበሪ አድሮ ወጥቷል፡፡ ከርሠ አንበሪ የመቃብር ዮናስ የጌታ ምሳሌ ነው፡፡ ትንቢቱን ባወቀ ተናገረ ምሳለውንም ባወቀ አስመሰለ ፍጻሜው ግን ኃጢአትን በምድር፤ መርገምን በመስቀል፤ ሞትን በሲኦል፤ ጥፋትን በመቃብር ማጥፋቱን ለማጠየቅ ነው፡፡ "አስተጋፈረ ኃጢአተ በዲበምድር መሠዐረ መርገመ በዲበ ዕፀ መስቀል ወአብጠለ ሞተ በውስተ ሲኦል ወነሠተ ሙስና በውስተ መቃብር" እንዲል፡፡ ሃይ. አበመቃብሩን ሲጠብቁ የነብሩ አራት ሞኖች መግነዝ ፍቱልኝ

መቃብር ከፈቱልኝ ሳይል በአካለ ብርሃን ሲነሣ፤ መላእክት ከእግሩ እንደሻሸ ተነጽፈው ሲያመሰግኑት ደንግጠው ሲቻኮሉ ወደ አይሁድ ሄደው ተነሣ አሏቸው፡፡ ቢሄዱ መቃብሩን ተከፍቶ አገኙት፡፡ ልብሳቸውን እየቀደዱ ይጮኹ ጀመር፡፡ 400 ወቂት እንስጣችሁ ተኝተን ሳለ ደቀመዛሙርቱ ሰረቁት በሉ አሏቸው፡፡

ደቀመዛሙርቱ አይሁድን ፈርተው ተሸሽገው ነበር፡፡ ማርያም መግደላዊት ግን ሽቱ ይዛ እንዘ ዓዲሁ ጽልመት ይላል ኀሀ ሳይቀድ ሄደች፡፡ ሌሎችም ተከታትለው ከመቃብሩ ደረሱ፡፡ ጌታችንን ወስደውታል እያሉ ሲያለቅሱ መልአኩ ለምንት ተኃሥሣሁ ለሕያው ምስለምውታን ተንሥአ ኢሀሎ ዝየሰ ስለምን ሕያውን ከሙታን መካከል ትፈልጉታላችሁ? ተነሥቷል ከዚህ የለም፤ ይልቁንስ ተነሥቷል ገሊላ እቀድማችኋለሁ ያላችሁን አስቡ ብላችሁ ለደቀመዛሙርቱ ንገሯቸው አላቸው፡፡ ሄደው ተናገሩ፡፡ ጴጥሮስና ዮሐንስ እየሮጡ ሄዱ፡፡ በደሮ ለጴጥሮስ ይላል ዮሐንስ ቀድሞ ደረሰ፡፡ ነገር ግን ርዕሰ ነውና ከውሎ ሆኖ ጠብቆ ከጴጥሮስ በኋላ ገባ፤ መግነዙን እንጂ እርእሱን አላገኙም፤ በእውነት ተነሥቷል እያሉ ተመለሱ፡፡

ማርያም መግደላዊት ግን የደረሰበትን ሳላውቅ አልሄድም ብላ ቆማ ታለቅስ ነበር፡፡ ጌታ ከወደኋላዋ መጥቶ ምን ሆነሽ ታለቅሺአለሽ? አላት፡፡ ጠባቂ መስሏት ጌታዬ አንተ ወስደኸው ከሆነ ሽቱ እንድቀባው ያደረግህበትን አሳየኝ አለችው፡፡ ማርያም ብሎ ስሟን ሲጠራት ጌታ መሆኑን ተረድታ መምህር ሆይ ብላ እጅ ልትነሳው ቀረበች፡፡ ኢትልከፍኒ እስመ ዓዲ ኢዐረጉ ኀበ አቡየ ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ አላት፡፡ ይህ ሴቶች ሥጋ ደሙን መቀበል እንጂ ማቀበል አለመቻላቸውን ያጠይቃል፡፡ ኋላ ቶማስን ጎኑን ያሰዳሰሰዋልና፡፡ ዮሐ 20፡27 ሄደሽ ለደቀመዛሙርቴ ተነሣ ብለሽ ንገሪያቸው አላት፤ ሄዳ አብስራቸዋለች፡፡ ዮሐ 20፡11-17

በእመቤታችንም ያመጣዋል፡- በነግህ ብትሄድ ደንጊያው ተገልብጦ መግነዙ ተቀምጦ አገኘች፡፡ ምርር ብላ ስታለቅስ ጌታ ሰማያዊ ግምጃ ተጎናጽፎ አካሉ እንደ ፀሐይ አብርቶ መጥቶ ብታለቅሺ ብታለቅሺ አትደክሚምን? አላት፡፡ አይሁድ መስቀል መግደል እንዳይበቃቸው ሥጋውን ወስደው ጎዘን ጨመሩብኝ አማኝቼው ቢሆን ብተጽናናው ነበር አለች፡፡ በውኑ በመር የተወጋ ጎኑን፤ በችንካር

ግሮቹን፣ በአካሊለ ሦክ የተቆራረሰ ራሱን ስታዪ
ስ አይሁድ በልጅሽ ተግምለውበታል፣ አንቺ
ተሸ ወደ ቤትሽ ሂጂ አላት። ነገሩን የምታውቅ
ያለበትን አሳየኝ አለችው። ፍጹም ጎዘኗን
ሉት አንቺም የምታለቅሺለት አንድ ልጅሽ እኔ
ት እናቴ ሆይ አይሁድ መነሣቱን ሊያስተባብሉ
ካንያት አገኘን እንዳይሉ ወደ ደቀመዛሙርቴ

ፃ፡10



ጲላጦስ ጌታ በመስቀል ሆኖ የተደረጉትን ሰባት ተአምራት አይቶ ደግ ሰው አስትያለሁ ብሉ አዝኖ ሳለ ጌታ በሕልሙ ሞቺ የቀረሁ መሰለህን? ግረኝ ብትለኝ እምርህ የለምን ሲለው አየ። በነግህ አይሁድ መጥተው ሥጋው ተሰርቋልና ጠባቂዎችን አስጠርተህ መርምርልን አሉት። ሲመረምራቸው አንዱ ጴጥሮስና ዮሐንስ ሠረቁት፣ ሁለተኛው አሥራ አንዱ ሁሉ ሠረቁት፣ በሦስተኛው ዮሲፍና ኒቆዲሞስ ወሰዱት አሉ። አራተኛውን እውነቱን ንገረኝ ብሉ ቢገሥፀው ከእንቅልፍ ስንነቃ ከውኃ ጎድጓድ ተጥሉ አገኘነው ፤ ይህንንም ያደረጉ ደቀመዛሙርቱ ይሆናሉ ብለን እንጂ ሲወሰዱትስ አላየንም አለ። አራቱንም ከግዞት ቤት አስገብቶ የመቶ አለቃውን ከነጭፍሮቹ አስከትሉ ከመቃብሩ ሄደ። መግነዙን አይቶ ደቀመዛሙርቱ ወስደውትስ ቢሆን ይህንንም ባልተውት ነበር ብሉ መግነዙን ይዞ ያለትስ ጀመር። እኔስ ጌታ እንደተነሳ ይህም መግነዝ ዕውር እንደሚያበራ አምናለሁ ብሉ መቶ አለቃውን ቢዳስሰው የጠፋች አንድ ዓይኑ በርታለታለች። ወዲያውም ዮሴፍ ኒቆዲሞስን ጠርቶ አስመሰከራቸው። አይሁድ እነርሱ ከኛ እድል ፈንታ ጽዋ ተርታ የላቸውም፣ አንተ ተነሣ የምትለው ግን ያውልህ ከጉድጓድ ወድቆልህል አሉት። ከመቶ አለቃው ጋር ተሸክሞ አምጥቶ ከመቃብሩ አግብቶ ደንጊያውን ገጥሞ ጌታዬ ሆይ የአንተ ክብርህ የኢይሁድ ሐሰታቸው በዚህ ሙት ይገለጥ ዘንድ እለምንህለሁ ብሉ ለመነ። ሙቱ ተነሥቶ በጌታ ቀኝ የተሰቀለ ጥሪስ መሆኑን የጌታንም ክብር መስክሯል። አይሁድ ፈርተው እየተጯጯሁ ይሸሹ ጀመር ያሏቸው አትልቀቁአቸው ብሉ ሥጋቸው እስኪተፈተፍ ድረስ በጎመድ አስገርፏቸዋል።

ወዲያውም ተነሣ ብሉ ከሄሮድስ ላከበት። እሱም መግነዙን፣ ዓይኑ የበራለትንና ከሞት የተነሣውን አያቸው ዘንድ ላክልኝ ብሉ ላከበት። እውነት መሰሉት ላከለት። ሰዎቹን በሰይፍ አስመትቷቸው በሰማዕትነት አርፈዋል። እርሱንም በሐሰት ከቂሳር አጣልቶ ከሚስቱና ከሁለት ልጆቹ ጋር በሰይፍ አስመትቶት በሰማዕትነት አርፏል። ግብ. ሕግ

ከዚህ በኋላ ከደቀመዛሙርቱ ሁለቱ ቀለዮጳና ኒቆዲሞስ ከኢየሩሳሌም 60 ምዕራፍ ወደምትርቅ ወደ ኤማሁስ የርሱን ነገር እየተጨዋወቱ ሲሄዱ ከወደኋላቸው ተከትሉ ይህ የምትሉት ነገር ምንድነው? አላቸው። ቀለዮጳ አንተ ለኢየሩሳሌም እንግዳ ነህን? ናዝራዊው

ኢየሱስን አይሁድ ጸልተው ተመቅኝተው እንደሰቀሉት አልሰማህምን? እኛማ ወልደ አምላክነቱን አምነን ተከትለነው ነበር፤ ዛሬም በነግህ ሴቶች ወደ መቃብሩ ሄደው ሥጋውን አላገኙም፣ ተመልሰው መጥተው ተነሥቷል አሉን። ይህንንም ጴጥሮስና ዮሐንስ ሄደው አይተዋል አሉት። እናንተ ዝንጉአን ብትሆኑ እንጂ አሱማ እንዲሞት እንዲነሣ ነቢያት ትንቢት ተናግረውለት የለምን እያለ መጻሕፍትን ይተረጉምላቸው ጀመር።

ከሚሄዱበት ሲደርሱ መሸቷል ከእኛ ጋር አደር ብለው ግድ አሉት። ማዕድ ሲቀርብ ኅብስቱን አንስቶ ባርኮ ሰጥቶ ተሰወራቸው። ወተከሥታ አእይንቲሆሙ ይላል ጌታ መሆኑን አውቀው ወደኢየሩሳሌም ተመልሰው ለሐዋርያት ነገሩ። ወዲያውም ጌታ ከዝግ ቤት እንዳሉ በማይመረመር ጥበቡ ከመካከላቸው ቆሞ ሰላም ለክሙ አላቸው። ምትሀት መስሏቸው ታወኩ። በጦር የተወጋ ጎኑን በችንካር የተቸነከሩ እጆቹን እግሮቹን አሳይቷቸዋል። በዚያውም ላይ ንሥኡ መንፈሰ ቅዱሰ ለእለ ኀደግሙ ኃጢአት ይትኀደግ ሎሙ ወለእለ ኢኀደግሙ ኢይትኀደግ ሎሙ ብሉ በምድር ያሠሩት በሰማይ የታሠረ በምድር የፈቱት በሰማይም የተፈታ ይሆን ዘንድ ሀብተ ክህነት ሠጥቷቸዋል። ሉቃ 24፡ 1-43

በመቃብር አድሮ ሦስት ሌሊት ሦስት ቀን
ሳይል መግነዝ ፍቱ አንሡ ደንጊያውን
ብርሃን ተነናጽፎ ሲነሣ መድኀን
ሊያስቀረው አልቻለም ሞት ይዞ እርሱን።
አይሁድ እርሱን ሰቅለው ደሰ ሲላቸው
ከሙታን ቢነሣ ፍርሀት ዋጣቸው።
በብርሃን ሲተካ የሌቱ ጽልመት
መላእክት ከበው ሲያመሰግኑት
ሙታን ናቸውና የአይሁድ ሠራዊት
ያንኮራፋ ነበር ተኝተው መሬት።
ግና ወላጆቹ ዋሉ ተደሰተው
በገዛ ሥልጣኑ ጌታ አምላካቸው
ከሙታን ተነሥቶ አይተውት በዓይናቸው
እምነቱ በአምላኬ ታላት ነው የጸና
ሞቼ ብቀበርም እነሣለሁና።
አማፀንሃለሁ ጌታ ፈጣሪዬ
ኋላ እንድታነሣኝ በጎ ግብር አዝዬ
አንተኑ ጌታዬን አባቴን መስዬ።

መጋቢት 30 - ዕረፍቱ ለሶምሶን መስፍን

ሶምሶን ማለት ሐዲሱ ለእግዚአብሔር ማለት ነው። ትውልዱ ከነገደ ዳን ነው። አባቱ ማኑሄ እናቱ እንትኩይ ይባላሉ። እንትኩይ ዕፀተ ማህፀን ሁና ስታዝን ትኖር ነበር። አንድ ቀን እንጪት ሰትሊታቅም የታዘዘ መልአክ መጥቶ ደግ ልጅ ትወልጃለሽ፣ የወይን ጠጅ

ከመጠጣት ርኩስም ነገር ከመብላት ተጠበቂ፤ ለባልሽም ንገሪው፤ ሕፃኑ ለእግዚአብሔር የተለየ ነውና በራሱ ላይ ምላጭ አያርፍበትም አላት። ለባሏ ነገረችው። ሁለተኛ ሲገለጥልሽ ንገሪኝ አላት። ሁለተኛ ተገልጾ ደግ ልጅ ትወልጂያለሽ አላት። ቆየኝ ባሌን ልጥራ ብላ ጠርታ አመጣችው። ለርሷ የነገራትን ሁሉ ነገረው። የፍየል ጠቦት አርዶ ሥጋውን አወራርዶ መሥዋዕት አቀረበ። መልአኩ በዘንጉ ቢነካው ተቃጥሉለታልል፤ አሱም በጢሱ ዐርጓል። መልአክ አይተው አያውቁም ነበርና ወዮልን እንሞታለን አላት። እኛ ከሞትንማ ልጁን ማን ይወልደዋል? አንሞትም አለችው። ወዲያውም ሶምሶን ተፀነሰ።

ተወልዶ ባደገ ጊዜ ኃያል ሆነ። በአሥራ አምስት ዓመቱ ከአባቱ ጋር ወደ ኢሉፍሊ ሄደ። በመንገድ ተለይቶ ዱር ቢገባ ግሩም አንበሳ አገኘው። በጡጫ መትቶ ገድሉታል። ሲመለስም አስታውሶ ቢያየው አንህብት በአፉ ውስጥ ማር ሰርተው አገኘ። ማሩን ቆርጦ ከአባት ከእናቱ ጋር ተመግቦታል።

በኢሉፍሊ ያያት ቆንጆ ነበረች። አባቱን አጋባኝ አለው። ተስፋ ከተነገረላቸው ከእስራኤል ሴቶች እንጂ ከአሕዛብ ሴቶች አታገባም ብሎ ከለከለው። እርሱ ግን ወድኛታለሁና አጋባኝ ብሎ ግድ አለ። አጭቶ አጋባው። ሠላሳ ያህል ሚዜዎች ተመርጠው ሲያጨዋውቱት ካገኛችሁት ሠላሳ መጎናፀፊያ ሠላሳ ቀሚስ እሰጣችኋለሁ። ካላገኛችሁት ግን እናንተ ትሰጡኛላችሁ ብሎ "እምአፈበላዒ ተረክበ መብልዕ ወእምአፈ ሕሡም ተረክበ ጥዑም ከበላተኛ አፍ መብል ከከሱም አፍ ጣፋጭ ተገኘ" የሚል ምሳሌ ነገራቸው። ሦስት ቀን ሲያሰቡ ቆይተው የማይሆንላቸው ቢሆን ሚስቱን ጠይቀሽ ንገሪን ብለው አስጨነቋት። ጠይቃ ነገረቻቸው። በቀጠሮ ቀርበው ምሳሌህን እንንገርህ አሉት። እሺ አለ። "ከአንበሳ የተፈራ ከማር የጣፈጠ ምን አለ? ከአንበሳ አፍ ማር አግኝተህ በልተህል" አሉት። "እምኢያሥራህምዋ ለዕንልትየ እምኢረከብከዋ ለምሳሌየ - ሚስቴን ባታስጨንቋት ኖሮ ምሳሌየን ባላገኛችኋት ነበር" ብሎ ተናዶ ወደ ሜዳ ወጣ። ሠላሳ ያህል ነጋድያን ሲያልፉ አግኝቶ ጭንጭናቸውን ሰብሮ መጎናጸፊያና ቀሚሳቸውን ገፎ አምጥቶ ሠጣቸው። በዚህም አዝኖ ወደ ሀገሩ ተመለሰ።

ከሦስት ወር በኋላ የበግ ሙክት ይዞ ቢመጣ አግቱ ሚስትህንግ ቀረህ ብለን ለሚዜህ ዳርናት። ከወደድህ ታናሿን አግባ አለው። ወደኋላ ተመልሶ 300 ቀበሮ ያዘ፣ 150 ጭራሮ አዘጋጅቶ አንዱን በሁለቱ ቀበሮዎች ጅራት እያሰረ በእሳት እያቀጣጠለ ለቀቃቸው። ቀበሮዎቹ ደንግጠው ሜዳ ለሜዳ ሲሮጡ የኢሉፍላውያንን አዝመራ አቃጥለውት ዋሉ።

የሀገሩ ሰው ሶምሶን ያደረገው መሆኑን ሲያወቁ በአግቱ ፈርደው አግቱን ከሀብት ከንብረቱ ጋር ቤት ዘግተው አቃጥለውታል። ሶምሶን ይህን ባታደርጉ ኖሮ ጠቢ ከእናንተ ነበር አላቸው። አርባ ሆነው ገጠሙት። ጭንጭናቸውን ሰብሮ በዓተ ኤጣም ገብቷል። ጌደው አሰራኤልን ሶምሶንን ይዛችሁ ስጡን አሏቸው። ነገሩት እጅ እግሬን አሰራችሁ ከሜዳ ጣሉኝ አላቸው። ጣሉት። ሲይዙት ሲጠጉ የታሰረበትን በጣጥሶ ተነሳ። የአህያ መንጋጋ አግኝቶ ቢወረውር ባንድ ጊዜ 1000 ሰው ፈጅቷል። ወዲያው ውኃ ጥም ተሰማው። ወደጌታ ቢያመለክት ከአህያው መንጋጋ አፍልቆ አጠጥቶታል። በጋዛም ሳለ ካደረበት ቤት ሸምቀው ሲጠብቁት መኖራቸውን አውቆ ወጸረ ራግዛተ ጋዛ በመትከሱ ይላል ከነደርቡ ተሸክሞ ወሰዶ ገደል ከቷቸዋል።

ከዚህ በኋላ በሴራቅ ደሊላ የምትባል ሴት ለመደ። ኢፍላውያን ወርቅ ብር እንሰጥሻለን ኃይሉ የሚደክምበትን ጠይቀሽ ንገሪን አሏት። ጠየቀችው በሰባት አውታር ብታሠር እደክማለሁ አላት። አሥራ ሶምሶን ኢሉፍላወያን መጡብህ አለችው። በጣጥሶት ተነሣ። አታለልከኝ እውነቱን ንገረኝ አለችው። በሰባት ምራን ብታሠር እደክማለሁ አላት። አሥራ ሶምሶን ኢሉፍላውያን መጡብህ አለችው። ጎማዶት ተነሣ። አሁንም ዋሸሽኝ ንገረኝ እንጂ አለችው። ሰባቱ ቁንዳላዎቼን ከምድር በካስማ መትተው ቢያሲዟቸው እደክማለሁ አላት። እንዲሁ አድርጋ መጡብህ አለችው። ነቃቅሎት ተነሣ። ከኃይሉም ጽናት የተነሣ ካስማዎቹ የደረሰበት አልታወቀም።

በመጨረሻ እወድሻለሁ ትለኛለህ እንጂ አትወደኝም ብላ ወተህወከት ነፍሱ እስከ ለሞት ይላል ነፍሱ እስክትታወክ ድረስ አስጨነቀችው። ኃይሌ በጸጉሬ ነው፣ እስመ ናዝራዊ ሐዲሱ ለእግዚአብሔር የተባልሁ እኔ ነኝ ከተወለድሁ ጀምሮ አልተላጨሁትም አላት። በወይን ጠጅ

አስከራ አስተኝታ ጸጉሩን ቆርጣ ቆርጣ ከጣለችው በኋላ ሶምሶን ኢሉፍላውያን መጡብህ አለችው። ኃይል ተነስቶት መነሳት አቃተው። በዚህ ጊዜ ኢሉፍላውያን ይዘው ሁለት ዓይኑን አጥፍተው እየጎተቱ ወሰዱት። ባቄላ ሲያስፈጩት ኖረዋል።

ጸጉሩ እያደገ ኃይሉ እየተመለሰ ሄደ። አንድ ቀን በዓል አድርገው ሳለ ያን ዕውር አምጡት ያጨውተን አሉ። አንድ ብላቴና እየመራ አምጥቶ ከመካከል አቆመው። ሁለቱን ሙሰሶች በቀኝ በግራ እጁ ይዞ አ እግዚአ እስእለከ አሐተ ስእለተ ህየንተ ክልዔሆን አዕይንተየ ትፃእ ነፍስየ ምስለ ኢሉፍላውያን ስለሁለቱ ዓይኖቼ ነፍሴ ከኢሉፍላወያን ጋር ትወጣ ዘንድ እለምንህለሁ ብሎ አንዱን ሙሰሶ በቀኝ እጁ ሁለተኛውን ሙሰሶ በግራ እጁ ቢመታው ከፎቅ የነበሩትም ከምድር ያሉትም ሁሉም አንድ ሆነው ጠፍተዋል። በሕይወተ ሥጋም ሳለ ካጠፋቸው ጠላቶቹ ያን ጊዜ በሞቱ ያጠፋቸው ይበዛሉ።

መጽ. መሳፍንት ከምዕራፍ 13 - 16 በሙሉ።

• <u>የነበረው በ1300 ዓ.ም ገደማ</u> ነው።

_____ //_____

ምዕራፍ 2

ሚያዚያ 1 - ዕረፍቱ ለአሮን ካህን

አሮን ማለት ደብረ እግዚአብሔር ማለት ነው። የሊቀ ነቢያት

ሙሴ ታላቅ ወንድም ነው። ሲራ 45:6 ትውልዱ ከነገደሌዊ ነው። አባቱ ጌታ እስራኤልን ከምድረ ግብጽ ሲያወጣ ሙሴን መስፍን አሮንን ካህን አድርጎ አስነስቷቸዋል።

ኤርትራን ከተሻገሩ በኋላ እስራኤል ሲበድሉ ጌታ በቸነፈር ገሠጻቸው። ሙሴ ወደጌታ ቢያመለክቱ ወንድምህ አሮን ልብሰ ተክህኖ ለብሶ ማዕጠንተ ወርቅ ይዞ የታመሙትን ባንድ ወገን ያልታመሙትን ባንድ ወገን አድርጎ ይጠንላቸው አለው። ወነሥአ ኤፋደ ቅኔሁ ዘጸሉት ከተረ መዓተ ወአጎሥዐ መቅሰፍተ ይላል እንዳለው አድርጎ ቢያጥንላቸው የታመሙት ድነዋል ያልታመሙት ተጠብቀዋል።

ልጆቹ ናዳብ፣ አብዩድና አልዓዛርም እንደርሱ በክህነት ጌታቸውን ያገለግሉ ነበርና ደቀቀ ቀዓት እስከ መቼ ክህነትን ከነልጆቹ ይዞ ሲገዛን ይኖራል? ብለው ተመቀኙት። ሙሴን እኛም ከሌዊ ወገን ተወልደናልና ሹመን አሉት። አሮን የተሾመ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። እናንተም ከእግዚአብሔር አግኝታችሁ ተሾሙ እንጂ እኔ አይቻለኝም አላቸው። ይህማ ለወንድሙ ማድላቱ ነው። ብለው ከሁለት መቶ የሚበልጡት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ማዕጠንተ ብርት ይዘው ሊያጥኑ ገቡ። ጢሱ ሲያርፍባቸው ልብሳቸው ምንም ሳይሆን እነርሱ እሳት እንደለበለበው ግንድ ሆነው ሙሴ አሮን አውጥተው ጥለዋቸዋል። በሙሴም ተነሰተው የነበሩ ዳታንና አቤሮን ከነሀብት ንብርታቸው መሬት ውጣቸዋለች። ምክር ሊያጸና ወዲያ ወዲህ ይል የነበረ ቆሬም የደረሰበት አልታወቀም ጠፍቷል።

እስራኤል ኃጢአታችንን እያሳሰቡ ይህን ሁሉ መከራ የሚያመጡብን ሙሴ አሮን ናቸው ብለው ሊወግሯቸው ደንጊያ ይዘው መጡባቸው። ከደብተራ አሪት ገቡ። ወድያውም የብርሃን ዓምድ ከምድር እስከ ሰማይ ተተከለ። በዚህ ፈርተው ተመልሰዋል።

ከዚህ በኋላ ጌታ ክህነት ከቤትህ እንዳይወጣ ምልክት አሳይልህለሁና ወንድምህ ሙሴ የ12ቱን ነገድ በትራቸውን ሰብስቦ በምሽት ከደብተራ አሪት አግብቶ በነግህ ያውጣው አለው። ሙሴ እንደታዘዘው ሰበሰበ። አሮንም የአባቱን የሌዊን በትር አምጥቷል። 12ቱንም በምሽት አግብቶ በነግህ ቢያወጣው የእርሱ ለምልማ አብባ አፍርታ ተገኝታለች። ዘኁ 16:17 እና 18 (ምሳሌነት አለው። በክፍል 1 ገጽ 95 ተመልከት።)

እንዲህ እያሉ ሐቅለቃዲስ ሲደርሱ እስራኤል ዋዕየ ፀሐይ ተሰምቷቸው ውኃ ውኃ ብለው ሙሴና አሮንን አስጨነቁአቸው። ደንጊያውን በበትር ሲመቱት ውኃ ፈለቀ። ለወትሮው ንሴብሐን ደግመው ንሥኡ ዘወሀበክሙ እግዚአብሔር ኪያሁ ሰብሑ - የሰጣችሁ እግዚአብሔርን አመስግኑ ብለው ይሰሟቸው ነበር። አሁን ግን ተናደዋልና ይህን ሳያደርጉ ሳያመሰግኑ ሰሟቸው፤ እስራኤልም ሳያመሰግኑ ጠጡት። በዚህ ጌታ አዘነ። ታመሰግኑኝ ዘንድ አላመናችሁብኝምና ምድረ ርስት አትገቡም አላቸው። ይኸውም አልቀረ ሙሴ በሞአብ አሮንም በደብረ ሐር ዐርፈዋል። ዘኁ20: 1-29

ሚያዚያ 5 - ዕረፍቱ ለሕዝቅኤል ነቢይ

- የነበረው በ1500 ዓ.ም አካባቢ ነው።

ሕዝቅኤል ማለት ጽኑዕ ጽኑዐ እግዚአብሔር ማለት ነው። ትውልዱ ከነገደ ሌዊ ነው። አባቱ ቡዝ ይባላል፤ ካህን ነበር። ቁጥሩ ከአራቱ ፀበይት ነቢያት ነው።

እስራኤል ተማርከው ፋርስ ባቢሎን በወረዱ በ30 ዓመት ሀብተ ቅንቢት ተሰጥቶታል። ሕዝ 1:1-3 ከዚህ በኋላ ክህነትን ከትንቢት

አንድ አድርጎ ይዞ ሃያ ዓመት አስተምሯል። የጌታን ከእመቤታችን መወለድና እመቤታችንም ቅድመ ጸኒስ፣ ድኅረ ጽንስ፣ ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ወለድ ድንግል መሆኗን በራዕይ አይታል።። ሕዝ 44: ከምርኮ ከተመለሱ በኋላ አስራኤል አምላካቸውን ዘንግተው በቃላቸው አዘው በእጃቸው ሠርተው ላቆሙት ምስል የሚሰግዱ የሚሠው ቢሆን ገሠጻቸው። በዚህ ምክንያት ጸልተው ተመቅኝተው በደንጊያ ወግረው ሮኀሳት ተኩሰው ገድለውታል።

➢ መዋዕለ ትንቢቱ ከ 592 – 570 ዓ.ዓ ነው:.

ሚያዚያ 6 - የአዳምና ሔዋን መታሰቢያ

ወይቤ እግዚአብሔር ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ ዘፍ 1:26 ይላል ጌታ ከአሑድ ዓርብ ነግህ 21 ዱን አስራወፍጥረታት ከፈጠረ በኋላ አዳምን ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ (ከነፋስ፣ እሳት፣ ውኃና መሬት) ከሦስቱ ግብራተ ነፍስ (ለባዊነት ነባቢነት እና ሕያውነት) የ30 ዓመት ጎልማሳ አድርጎ በማዕከለ ምድር በቀራንዮ ፈጠረው፤ ባሕርዩ ባሕርየ መልአክ ወሰብእ ነውና ማዕከላዊ ነህ ሲል ነው።

ሰውም ግለት ሰባት ባሕርያት ያሉት ፍጹም ፍጡር ግለት ነው። ሰባት ቁጥር በዕብራውያን ፍጹም ነውና። እስመጕልቊ ሳብዕ በኀበ ዕብራውያን ፍጹም ወእቱ እንዲል ሃይ. አበ ፍጹምነቱም በአርአያ እግዚአብሔር በመፈጠሩ ነው። በፍጥረት ላይ የሰለጠነ ሆኖ መፈጠሩም ፍጹም ያሠኘዋል። "ወሤሞ ንጉሠ ካህነ ወነቢየ ወመጋቤ፤ ላዕለ ኩሉ ዘፈጠረ እንዲል ሰንክሳር ይህም ሊታወቅ መላእክት ከእግዚአብሔር ታዘው በየብስም በባሕርም ያሉትን እንሰሳት አራዊት ወደርሱ አያመጡ እሱ ስም አውጥቶላቸዋል። ኩፋ. 4፡ 1-3

ከዚህ በኋላ ወይቤ እግዚአብሔር ኢኮነ ሠናየ ለእጓለእመሕያው ይንበር ባሕቲቶ አላ ንግበር ሎቱ ቢጸ ዘትረድኦ ይላል። የሰው ልጅ ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም። ረዳት እንፍጠርለት ብሎ እንቅልፍ አመጣበትና ፍጹም ሳይተኛ ፍጹምም ሳይነቃ ከጎኑ

አንድ አጥንት ወሰዶ በሥጋ መልቶ የ15 ዓመት ቆንጆ አርጎ ሴትን ፈጠረ። ወአምጽአ እግዚአብሔር ድቃሰ ላዕለ አዳም ወኖመ ወነሥአ አሐደ አጽሙ እምዝኩ ወለእንተ ነሥአ አጽም ረሰያ ብእሲተ ወአምጽአ ኀበ አዳም አዳምም ዛቲ አጽም እምአጽምየ ወሥጋ እምሥጋየ ይህች አጥንት ከአጥንቴ ሥጋም ከሥጋዬ ናት ብሎ ሚስት አደረጋት፤ ሰሚንም ሔዋን አላት። ሔዋን ማለት እመ ሕያዋን ማለት ነው። ዘፍ 3፡20

ይህም የሆነ በሳምንቱ ዓርብ በሦስት ሰዓት ነው። አስኪጎርስ አዳም በተፈጠረ በ40 ቀኑ ሔዋንም በተፈጠረች በ80 ቀኗ ገነት ገቡ። በዘመነ አራት ወንድ በአርባ ቀኑ ሴት በሰማንያ ቀኗ ዕጉለ ርገብ ዘውገ ግዕዝት ይዘው ቤተመቅደስ መግባታቸው፤ ዛሬም እንዲሁ በአርባ በሰማንያ ቀናቸው ለጥምቀተ ክርስትና ቤተክርስቲያን መግባታቸው ስለዚህ ነው። ኩፋ 4፡9-10

በነነትም የታዘዘላቸውን ፍሬ እየተመገቡ 7 ዓመት ከ1 ወር ከ17 ቀን ተቀመጡ። ኩፋ4፡16 በዚህ ጊዜም እንሰሳት አርደህ ብላን አልበህ ጠማን ሲሉ አራዊትም እጅ ሊነሡ ከአዳም ዘንድ ሄዱ። እርሱም ሁሉን መርቆ ሰደዳቸው። እየተደሰቱ ሲመለሱ ዲያብሎስ ከነዳና ቆይቶ ይህ ሁሉ ደስታ ምን ተገኝቷል? አላቸው። አርደህ ብላን አልበህ ጠማን ብንለው መርቆ ሰደደን አሉት። ጌታችሁ አዳም ምን ይመስላል አላቸው? ከፀሐይ ሰባት እጅ ያበራል አሉት። ያችን ዕፅ ቆርጠ ማን ከአፉ ባደረገልኝ ብሎ አሰበ።

በሌላ ቀን እጅ ሊነሱ ሲሄዱ አግኝቷቸው አስከትሉኝ አላቸው። አይሆንም ብለው ትተውት ሄዱ። አብርል አዝርል የተባሉ ድምፀ መልካም አዕዋፍም ጌታችን አዳም መልከመልካም ነው አንተ ግን መልከ ጥፉ ነህ ብለውት አለፉ። በመጨረሻም የግመል ወሃብራ ታህል የነበረችው እባብ መጣች። አስከትዪኝ አላት። መልከ ጥፉ ነህ አይሆንም አለችው። መልከ ክፉ ካልኖረ መልከ መልካም በምን ይታወቃል፤ በዚያውስ ላይ ካንቺ ከመልከመልካሟ ጋር ሆኜ መልከ ከፉነቴ አይታወቅም አላት። በውዳሴ ከንቱ ተጠልፋ እሺ ብላ አስከተለችው።

ከዳገት ሲደርሱ ይህ መንገድ ካላወቁበት ያደክማል፤ እንተዛዘል አላት። እሺ አለች። አዘላት። ጥቂት እልፍ አድርጎ በጽሐ ፍዳ

ተባርዮ ዘጸርኩኪ ጽርኒ ተራሽ ደረሰ እዘዚኝ አላት። አዘለችው። ከአካሏ ተዋሕዶ እያከለፈለፈ ወሰዳት።

አዳም መላእክት አሌፋት አስተምረውት ነበርና ሲጸልይ አገኘው። ቀርበ በሐከ አ አዳም ንጉሠ ሰማያት ወምድር - የሰማያትና የምድር ንጉሥ ሰላም ላንተ ይሁን ብሎ ሰላምታ አቀረበ። እርሱ ግን ፍልጥ አርዌምድር የምድር እንጂ የሰማይ ንጉሥ አይደለሁም ወግድ አለ። ወደ ሔዋን ቢሄድ ሥራ ፈትታ እግሯን ዘርግታ አገኛት። ድል እንደሚነሳት አወቀ። ቀርቦም በሐኪ አ ሔዋን ንግሥተ ሰማያት ወምድር አላት። ለካስ የሰማያትም ንግሥት ነኝ ብላ ደሰ አላት። በእንተ ምንት ይቤለክሙ እግዚአብሔር ኢትብልዑ እምኵሉ ዕፀው ዘውስተግነት በግነት ካሉ እንጨቶች ሁሉ እንዳትበሉ እግዚአብሔር ያዘዛችሁ ለምንድር ነው? አላት ያዘነ የተቆረቆረ መስሎ ኧረ ዕፀበለስንም አትበሉ ያለን ሞትን እንዳንሞት ነው አለች። ለእመ በላዕከሙ እኝትኩ በለሰ ሞተ ትመውቱ እንዲል ዘፍ 3:3 አኮ ሞተ ዘትመውቱ አላ አምላክ ትከውኑ - አምላክ ትሆናላችሁ እንጂ አትሞቱም ወባሕቱ የአምር እግዚአብሔር ከመ ሶበበላዕከሙ እምኔሃ ይትከሠታ አዕይንቲክሙ ወትከውኑ ከመአምላክ ዳሩ ግን ከርሷ በበላችሁ ጊዜ አይኖቻችሁ እንዲገለጹ እንደ አምላክም እንድትሆኑ እግዚአብሔር ያውቃል ለዚህ ነው አላት። ወአፍተዋ ከመትብላዕ እምውእቱ ዕፅ ይላል አስጎመጃት። በልታ አዳምን አበላቸው። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ልብሰ ብርሃን ተጐናጽፈው ሳይተፋፈሩ ይኖሩ ነበረ። በዚህ ጊዜ ግን ጸጋቸውን ተገፋፋ፣ ተፋፍረው በበለስ ቅጠል ሥጋቸውን ይሸፍኑ ጀመር። እባብ ከአራዊት ሁሉ የተረገመ በሆዱ የሚሳብ አፈር የሚመገብ የሰው ልጅ ራስ ራሱን የሚቀጠቅጠው እንዲሆን ፈረደበት። አዳምና ሔዋንንም በሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ በርደተ መቃብር ርደተ ገሃነም ፈርዶ ከገነት አስወጥቶ በደብር ቅዱስ አኖራቸው። ተመልሰውም እንዳይገቡ "ወአዘዘሙ ለኪሩቤል ወሱራፈል ዘውስተ እዳሞሙ ሰይፈ እሳት እንተ ትተመያየጥ ከመይዕቀቡ ፍናተ ዕፀ ሕይወት"(ዘፍ 3:24) ይላል። ሰይፈ እሳት የያዙ ኪሩቤል እንዲጠብቋት አድርጓል።

ከዕለታት አንድ ቀን አዳም እግዚአብሔርን ያህል ጌታ ገነትን ታህል ቦታ ባንቺ ምክንያት አጣሁ ብሎ ሔዋንን ፊት ነሳት፤ ደንግጣ ሸሸች። ቅዱስ ገብርኤል መጥቶለምን አበረርኻት? በርሷ ምክንያት እግዚአብሔር ጌታዬን ገነት ቦታዬን አጣሁ አለ። በርሷ ምክንያት

ብታጣም መታረቂያህ እርሷ ናትና ታረቃት አለው። እርሱ ግን ኢትከወነኒ ናዛዚተ - በፍፁም መታረቂያዬ አትሆንኝም ብሎ ሳይታረቃት ቀረ። ከዚህ በኋላ በጸሉት ጊዜ ሲጸልይ መልአኩ አዳም ዋቄመኖን ጸሉት እግዚአብሔር አይሰግም ምን ያረግልሀል አለው። ሄዶ ታርቆ አምጥቷታል።

ሔዋን ከጌታ መታረቅ ሽታ አዳም እግዚአብሔር ግረን ብንለው ይምረናልና ሱባኤ ይዘን እንለምነው አለች። እርሱም አንቺ እያልሽ በምን ይሆናል አለ። ከእንግዲህ ከፈታድህ አልወጣም አለች። ከዚህ በኋላ "ምትዋሞን (ምጽላዮን) ለአንስት ለባሕቲቶን" የምትል ሕግ እንድትሠራ አውቀው እጅግም ሳይራራቁ እጅግም ሳይቀራረቡ ለየብቻቸው ሆነው ከባሕር ገብተው ይጸልዩ ጀመሩ። በሰላሳ አምሰተኛ ቀን ዲያብሉስ እንግዲህማ ሊታረቁብኝ አይደለምን ብሎ መልአከ ብርሃናዊ መስሎ አዳም ጌታ ምሬሀለሁና ውጣ ብሎሀል አለው። አንተ ማነህ? አለው መልአከ ብርሃን ገብርኤል ነኝ አለው እርሱም ከዚህ በፊት የፍጡር ቃል ሰምቼ ተጐድቻለሁና አልወጣም አለ። ወደ ሔዋን ሄዶ አንቺ ሔዋን ባልሽ አዳም ቀድሞ አትብላ ያለውን በልቶ ከፈጣሪው ተጣላ አሁን ደግሞ ታርቄሀለሁ ውጣ ቢለው አልወጣም አለ እኔ ምን ገደኝ ለራሱ ይባሰው እንጂ አላት። አንተ ማነህ? አለችው። መልአከ ብርሃን ገብርኤል ነኝ አላት ወጥታ ሄዳ አዳም ጌታ እንኳ በ35 ቀን በ1 ቀንስ ይምር የለምን ውጡ ካለንማ እንውጣ እንጂ አለችው። እርሱ ግን አይሆንም የፍጡር ቃል ሰምቼ አልወጣም አለ። እኔስ እሄዳለሁ ብላ ወጥታ ሄደች። መልአኩ አትለያት ብሎት ነበርና እርሱም ወጥቶ ተከተላት ከእግረ ገነት ሲደርሱ ሰይጣን እኔ ግንኙ አውቃችሁኝ? አላቸው መልአከ ብርሃን ገብርኤል ነኝ አላልሀምን? አሉት። ምን ገብርኤል ነኝ ባላጋራችሁ ነኝ እንጂ ብሎ ጐሡም ግዙን ቢያሳያቸው ደንግጠው ወደቁ። በሦስተኛው ቀን ቅዱስ ገብርኤል ወስዶ በደብር ቅዱስ አስቀመጣቸው ሲሄድም ምግቡን እንዲወስዱለት በገነት ያሉ አዕዋፍን አዞለት ሄዷል።

አዕዋፍም በአፋቸው በእግራቸው አንድ አንድ ሁለት ሁለት ዘላላ እየወሰዱ 12 ዎሻ ሞሉለት። ከአዕዋፍም አብርል አዝርል የሚባሉ አዳም በገነት ሳለ ቋንቋቸውን ለምዶ ነበርና እንሂድ ሲባባሉ ሰምቶ ከመጡለት ፍሬ ስንቁን ይዞ እየሮጠ ተከትሏቸው እኩል ከእግረ ገነት ደረሰ። ዳሩ ግን ገነት በአሳት ተቀጽራ ነበርና እነሱ ላይ ላዩን ሲሸሹ ሲገቡ እርሱ መግቢያ አጥቶ ከዚያው ቆሞ ቀረ። ዲያብሉስ

አይቶት ደግሞ እዚህ ምን አመጣው? እንደውም ካልገደልኩት አላርፍም ብሎ ቤት የሚያህል ደንጊያ አንስቶ ጫነበት። ወተደብተረት ይእቲ ዕብን ላዕለ ርዕሰ አኖም ሠሉሰ መዋዕለ ወሠሉሰ ለያልየ -ይላል ደንጊያው እንደ ድንኳን ሆናለት ሦስት ቀን ሦስት ሌት ቆይቶባታል። በሦስተኛው ቀን ቅዱስ ገብርኤል አንሥቶለት የያዘውን ፍሬ በደሙ ለውሶ መሥዋዕት አቀረበ። ጊታም በገሙስ ዕለት ወበ መንፈታ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ወእድጎከ ውስተ መርሀብከ ወእትቤዘወከ በደሙ መስቀልየ ወበሞትየ ብሎ 5500 ዘመን ሲፈጸም የልጅ ልጁ ከምትሆን ከእመቤታችን ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ በዘበረ ደሙ ፈሳሽነት እንደሚያድነው ተስፋ ሰጥቶታል። ... ተሌምንመስ

አኖም ይህን ተስፋ ካገኘ በኋላ እያረሰ በምድረ ኢልዳ ተቀመጠ። ኩፋ 5:6 ሚስቱ ሔዋንን በንብር አወታት፣ ታኢልን ወለደችለት፣ በሁለተኛ ሩካቤ አቤልን ወለደችለት። መገደል በታኢል መሞት በአቤል ተጀምሯል። በዘፍል 1 ገጽ 130 ተመልክት። አኖም በአቤል ሞት ምክንያት 4 ሱባዔ ዘመን አዝኗል። ኩፋ 5:12 ከዚህ በኋላ መልአኩ መጥቶ ናሁ ወልድከ አቤል ተገልመ ዕፀሚገ ልንት አለው፤ ከገዘሱ ተጽናና ወንድ ልጅም ተወለደለት ስሙን ሴት አለው። ምትክ ማለት ነው። በዚህ ጊዜ አኖም የ230 ሔዋን የ215 ዓመት ዕድሜ ሰዎች ነበሩ። ከሌትም በኋላ ብዙ ወንዶችንና ሴቶችን ወልደዋል።

ጊዜ ዕረፍቱ ሲደረስ አኖም ልጁ ሴትን ላልሞት እንድባርካቸው ልጆችህን አምጣ አለው። አምጥቶ በፊቱ አቆማቸው። ዓይን ዓይናቸውን እያየ ያለትስ ጀመር። እነርሱም አባታችን ከእኛ እንዲት ትለያለህ እንዲትስ ከአፈር ትጣለህ? እያሉ አለቀሱ። እግዚአብሔር ይባርካቸሁ ብሎ ባረካቸው መረቃቸው። ሴትንም ልጇ ፈጣሪህን እንዳታስቀይም እወት ታኢል በእግዚአብሔር ዘንድ የተናቀ ነውና አንተ ከርሱ ልጆችህም ከልጆቹ እንዳትተባበሩ ተጠንቀቅ ኋላ ግን ምድር በንፍር ውኃ ትጠፋ ዘንድ አሳትና ሥጋዩን ብቤተመዛግብት አስቀምጠው ብሎት በ930 ዓመቱ ዓርብ በዘጠኝ ሰዓት ዐረፈ። ዘፍ5:5

ሥጋውንም መላእክት እያሳዩአቸው ሽቶ ቀብተው ገንዘው ዕጣን ወርቅ ከርቤውን አድርገው በቤተመዛግብት አኑረውታል። በጥፋት

ውኃ ጊዜም ናኅ ከመርከብ ይወጣ ገቢኣል። ሲመጣም ይዞት ወጥቶ ለሴም ሰጠው። ሴምም ከዚም ወገን የተወለደ መልከጼዴቅን ከመናፍቁ አሰናብቶ በግዕዝ ምድር ቀራንዮ አስጠብቆታል። ጌታም በተራንዮ መስቀሉ ቅሉ ሰለዚህ ነው።

• የአኖም መዋዕለ ሕይወቱ ከ5500 - 4570 ዓ.ም ነው።

ሰላም ላንተ አኖም ሠላረ ፍጥረታት
ለአምላክ ልጁ ነህ ለሰዎች አባት።
ከሥሉ አለቃ አምላክ ዘወደህ
ወአርአያ ወአምሳሉ ዘልጁ አዘዘህ
የኋይወት እስትንፋስ እፍ ብሎብህ
ወፍተረት ውስ ላይ አመላለሰ።
ልትወድሰው እንኳ አለመቻልህ ከቶ
ፅንሠህን አይተሰህ ሉሩህን ሰውተ
ወደ ኋይወት መራህ እርሱ ዋነን ዋቱ።
እናታችን ሌዋን ይድረስሽ ወሰላታ
የሰው ውስ እናት ነሽና አዘኝታ።
ፀጋህን ወትላሊ ወወት ናረሽ
እነሆ ድንገልን ወመወደድ ከርሽ።

የድኅነታችን ምንጭ ናትና ልጅሽ
ምክንያተ ሰዲት መሳለ ተረልሽ።
ሞትና መተፍር ሰለመ የመጭ
አኖምና ሌዋን ወለሰ ወለተመ ነው
ልንለ አደግም ከእንግዲህ አንተው።
አነርሱግ አለትሰው ንስሓ ገቡተው።
ደኼሙ ወከር አለ ወአምላክ ደምደነው።
ወኖሰ ያመሳጠን ዋትና መትሰርትን
የኖሙ ግጣጣም ነው ወለለ ኃጢአትን
ለለዘህ ተምረን ከሌዋን ከአኖም
ወሕይወት ሰጥር ወግያልፍ ንስም
ንጹህ እንግዛ አንቺደል ቀማ።

ግቱ 3:2 ሉቃ 13:10 ፣ 15: 11

ሰ- ዳንግይ ትንግኤ (ሬጸምን)

ወንል ትንግኤ የወንሳት ውስ ርዕስ፤ ቁንም ነው። ስለሆነም ዲተከርስቲያን እለክ ወንል ሕርገት ድረስ ያለውን ጊዜ ዘመነ ትንግኤ ብለ የሰሙችው ሲሆን በተለይ ከትንግኤ ጀምር እለክ ሰምንተኛው ቀን እሑድ ድረስ ያሉትን ዕለታት ለዩ ሰያሜ ሰተታ እንደ አንድ ወንል ታክብራቸዋልች።

የዕለታቱም ሰያሜ እንደግእተሌው ነው
ሰኖ - አዉርሃም
ግእስኖ - አልግዛር
ኀሙስ - አኖም
ዓርብ -
ቅዳሜ - አንስት
እሑድ - ሬጸምን (ዳንግይ ትንግኤ)

በዚህ ዕለት የሚደረሰው ምስጋና ከዕለተ ትንሣኤ ምስጋና ጋር አንድ ዓይነት ነው። ታሪኩም - ጌታ የተነሣ ዕለት ደቀመዛሙርቱን ከዝግ ቤት ገብቶ ሰላም ለክሙ ባፅቸው ጊዜ ከአስራ አንዱ ሐዋርያት አንዱ ቶማስ የተባለው ዲዲሞስ ከነርሱ ጋር አልነበረም። ሲመጣ ርኢናሁ ለእግዚእነ ጌታን አየነው አሉት። ሑሩ ወመሀሩ እንደሚላቸው ያውቃልና እነሱ አየን ብለው ሲያስተምሩ እኔ ሰማሁ ልል ነውን ብሎ እመኢርኢኩ እደዊሁ ወአገሪሁ ኅበ ቀኑውዖ በችንካር የተቸነከሩ እጆቹን እግሮቹን ካላየሁ - ወእመ ኢወዲይኩ አጽባእትየ ውስተ ቅንዒቲሁ ወእመ ኢያባእኩ እደየ ውስተገቦሁ ወኢገሠሥኩ በችንካር የተቸነከሩ እጆቹን እግሮቹን በጦር የተወጋ ጎኑን ካልዳሰስኩ አላምንም አለ።

ወእምድኅረ ሰሙን መዋዕል ይላል በስምንተኛው ቀን ቶማስ ባለበት በዝግ ቤት ገብቶ ሰላም ለክሙ አላቸው። ቶማስ ጎኑን ካልዳሰስኩ ብሎ ነበርና ሀብ እዴከ ወአብእ ውስተ ገቦየ ወግሥሥ እጅህን አምጣና ወደጎኔ አግብተህ ዳሰኝ ወኢትኩን ናፋቂ አላ አመን አመን እንጂ አትጠራጠር አለው። ቢዳስሰው ከእሳት እንደገባ ጅማት ኩምትርትር አለ። አግዚእየ ወአምላኪየ ጌታዬ አምላኬ ሆይ አለ። አሰመ ርኢከኒሁ አመንከኒ ብታየኝ አመንክ ብፁዓንሰ እለእንዘ ኢይሬእዩኒ የአምኑኒ - ንዑዳን ክቡራንስ ሳያዩኝ የሚያምኑብኝ ናቸው። ብሎ ፈወሶታል። ይህች ጎኑን የዳሰሰች እጁ ዛሬም ሕያዊት ሁና በሕንድ አገር ከታቦቱ ጋራ ትኖራለች። በዓመት በእመቤታችን በዓል (በአስተርእዮ) ሊያጥኑ ሲገቡ ቀድሳ ታቆርባለች፤ የሚሸመውን ወጥታ ቀኝ እጁን ትይዘዋለች። እንዲህ እያለች እስከምጽአት ድረስ ትኖራለች። ትር፡ ወን

ለ. ማርያም ግብጻዊት

ሀገሯ እስክንድርያ ነው። አባት እናቷ ሲያርፉ በደግነታቸው ይቀና የነበረ ሰይጣን እርሷን ፍትረ ዝሙት አሳደረባት። 27 ዓመት በሴት አዳሪነት ኖረች። ጌታ ሊያድናት ቢወድ ግስተዋልን ሰጣት። አንድ ቀን ቅዱሳን መካናትን እጅ ሊነሱ የሚሄዱ መንገደኞች አግኝታ ተከተለቻቸው። መርከብ ሲሳፈሩ እርሷ ገንዘብ አልነበራትምና ሥጋዋን ፈቅዳለት ተሳፍራ ተሻገረች።

ጎልጎታ ከመቃብር እግዚእ ምእመናን ሲገቡ እርሷ መግባት ተሳናት። ከስዕለ ማርያም ሥር ወድቃ ስታለቅስ ቆይታ እመቤታችን ዋስ ሆናት ገብታ ተሳለመች። ደስ ብሏት እመቤቴ በሥጋ እንደተዋስሽኝ በነፍሴም ዋስ ሁኚኝ እድን ዘንድ የግደርገውን አስታውቂኝ ብላ ተግፅኆ እመቤታችንም በሰዕሏ አድራ ከሰው ተለይተሽ ገዳመ ዮርዳኖስ ንብተሽ ኑሪ አለቻት።

ከመንገድ ወጥታ ስመ እግዚአብሔር ጠርታ ጥቂት ሣንቲም አገኘች። ሁለት ጎብስት ገዝታ ያን ይዛ ዮርዳኖስን ተሻግራ የሰው ድምፅ ከማይሰማበት በረሀ ገብታ 47 ዓመት ኖረች። የያዘችው ሁለት ጎብስት ምን በልታ ትኖር ነበር? ቢሉ በበረሀ ምን ይገኛል እንደበግ ሣር ነጭታ ውኃ ተጎንጭታ ትኖር ነበር።

ከዚህ በኋላ ዞሲማስ የተባለ መነኮስ እመቤታችን አነሳስታ ልካው ቢሄድ ከሩቅ አያት። ዕርቃኗን ነበረችና ተነሥታ ሮጠች። እሱም በረከት ቀረብኝ ብሎ ተከትሏት ሮጠ። ጥቂት ከተራራው በኋላ መለሰ ብላ አ ዞሲማስ ለእመፈቀድከ ከመ ትትናገር ምስሌየ ውግር ሊተ ጸርቀ ዘእትከደን ቦቱ እስመ አነ ዕርቅት - ከኔ ጋር ልትነጋገር ከወደድህ ዕርቃኔን ነኝና የምለብሰው ጨርቅ ጣልልኝ አለችው። መደረቢያውን ጣለላት። ያን ለብሳ መጥታ እጅ ተነሳሱ። ከዚህ በኋላ ታሪኳን ነግራ ለዓመቱ ሥጋውን ደሙን አምጥቶ እንዲያቀብላት ተማጽና ተሰናበተችው።

በዓመቱም ሥጋውን ደሙን አምጥቶ አቀበላት። የዛሬ ዓመት በዚህ ጊዜ መጥተህ ጠይቀኝ አለችው። ቢሄድ ዐርፋ ሥጋዋን ግሩም አንበሳ ሲጠብቀው በራሷም አ ዘሲማስ ቅበራ ለማርያም - ቅበራት የሚል ተጽፎ አገኘ። እሱ ሥጋዋን ሱገንዝ አንበሳ መቃብሯን ቆፍሮለት ቀብሯ ተመልሷል። <u>"እባዕኩ ለኪ ሰብሐተ ተአምር ዘይሤለስ በበጎምሳ፤ ሀየንተ ጽጌያት ጎምሳ ሰበዕልኪ አክሊለ ርዕሳ፤ ተወኪፈኪ ግርያም አንጽሕኒ እምአበሳ፤ ከመ አንጸሕኪያ ለግብጻዊት እምርኩሳ፤ እስከመቃብራ ከሪየ ዘይጥህር አንበሳ።"</u> እንዳለ ደራሲ

* የነበረችው በ5ኛው ም.ዓ ድ፡ል፡ክ ነው የቤ/ክ መዝ. ቃ አማርኛ፣

ግብጻዊት ማርያም ባሕታዊት እናት
የድንግል ማርያም ወዳጅ ነሽ በእውነት
መንደላቱት ሳለ በዓለም ተደሰቱ
በበረሀ መኖር ከሰው ተለይቱ
ለአላም ልጅ በምድር ይቻል ይሆን ከቱ?
በእምላክ ቸርነት ግን ላንቺ ተችሏል
እርባ ስምንት ዓመት በበረሀ ኖረሽ
መሪር የንስሐ ዕንባ እያነባሽ።

ጠላት ዲያብሎስን ከናግከራው
በንስሐ ጦርሽ አንበረከከሽው
የዓለም ሀሳብንም እንኮታኮትሺው
የሰው አዋራሹ ነውና ጣዪው
የቀድሞ በደልሽ በዕንባሽ ተደምሰሳ
መታብር ቆፈረ ግሩሙ አንበሳ
የኛም ኃጢአታችን ይፋቅልን ዘንድ
በንስሓ እንቅረብ ወደ ወልድ ዋሕድ።

* "ንስሓሰ ትሬስዮ ለዘአበሰ ከመ ዘኢአበሰ። ወለዘማኒ ከመ ድንግል"
"ንስሐ የበደለውን ያልበደለ። እመንዝራውንም እንደ ድንግል ታደርጋለች"
አረጋዊ መንፈሳዊ ድር 26 እና 29

ሚያዚያ 7 - ዕረፍቱ ለኢያቄም ጻድቅ

ዮናኪር፣ ሳዶቅ ተብሎም ይጠራል።

ትውልዱ ከነገደ ይሁዳ ከቤተ ዳዊት ነው። አባቱ ቅስራ ይባላል። ከነገደሌዊ ወገን የሆነች ሐናን አግብቶ በይሁዳ ከተማ ይኖር ነበር። ነገር ግን ሐና ዕፁተ ማኅፀን ሁና ልጅ አጥቶ ብዙ ዘመን ሲያዝን ኖሯል። ኋላ ግን ጌታ ኀዘኑን አይቶ ጸሎቱን ሰምቶ ልዮላሚ መቀት ከተለየው በኋላ በብስራተ መልአክ እመቤታችንን ሰጥቶታል። እመቤታችንም በተወለደች ጊዜ ታድሶ እንደ መላእ ዓመት ጎልማሳ ሆኖ ሕማም ድካም ሳይሰማው ኖሮ በዚህ ዕለት ዐርፏል። ያረፈውም እመቤታችን ገና በቤተመቅደስ ሳለች ነው። ነገ ማር

ኢያቄም ይድረስህ የጸጋ ምስጋና
የጽድት የትሩፋት አበጋዝ ነህና።
ፍቅርና የሞሃት ትዕግስት ጓደኞችህ
ኀዘንህን ሁሉ አስወገዱልህ።
ጸልየህ ተስፅህ ባይሰግህ ለጊዜው
ከተ አልሞከርከም አምላክን ልትከሳው
በትዕግስት ናርክ እንጂ እየተግጻንከው
ጌታም ጽናትህን ትዕግሥትህን አይቶ
አስደሰተህ ላንተ የልጅ እናት ሰጥቶ።
የአምላክን እናት ለመውለድ የክታህ
ኢያቄም ሆይ እንተክብ የጻድቃን ራስ ነው።
ልክ እንደኢያቄም እንደደጉ አባት
ጸንተው ደጅ ቢጠኑት ያስመታቸት
ፈጣሪ አይነሳም የሹትን ባጸውነት።

ሉቃ 18፡7 ሉቃ 21:36

ሚያዚያ 15 ፀዓተ ነፍሱ ለዮሐንስ መጥምቅ

ዚና ዕረፍቱ በክፍል 1 ገጽ 15 እንደተገለፀው ንጉሥ ሄሮድስ ኢይከውነክ ታውሰብ ብእሲተ እኁከ ፊልጶስ ብሎ ቢገሥፀው ወሰድፍ አስመትቶታል አንገቱም ከንፍ አብቅላ አ ሄሮድስ አይከውነክ ታውሰብ ብእሲተ እኁከ ፊልጶስ ብሎው በራ ሂዳልች። በዚህ ጊዜ ጌታ ከደቀመዛሙርቱ ጋር በደብረዘይት ነበርና ቀርባ ስትጸልት ባለሽበት ፀንተሽ አስተምሪ አላት። 15 ዓመት አስተምራ በዚህ ዕለት ዐርፋለች። * ያረፈችው ዓ45 ዓ.ም ነው።

ሚያዚያ 23 - ዕረፍቱ ለቅዱስ ማር ጊዮርጊስ ሊቀ ሰማዕታት

ጊዮርጊስ ግለት ኮከብ ብሩህ፣ ሐረገወይን፣ ፀሐይ ግለት ነው። ቁጣኩስ በልዳ እንዲለው ሀገሩ ልዳ ነው። አባቱ ጰርጉቶስ (አንስጣስዮስ) ይባላል። በልዳ መስፍንነት ተሹሞ ይኖር ነበር። እናቱም ቲዎብስታ (አትልሰያ) ትባላለች። ማርታ ደስያ የሚባሉ እኅቶች ነበሩት።

አሥር ዓመት ሲሆነው አባቱ ሞተ ሲላ መስፍን ተሾመ ደን ክርስቲያናዊ ዘርና ከቤቱ ወሰዶ እያስተማረ አሳደገው። እርሱም ፈረስ መጋለብ ተዘት መወርወር ለመደ። ሙር ሚዳ ወጥቶ ከጠላቶቹ መሀል ገብቶ እኔ የክርስቶስ ወታደር ጊዮርጊስ መሳሪያችሁ ሲሉኞው ደንግጠው ይሸሹ ነበር።

እንዲህ እያለ አድጎ ሃያ ዓመት ሲመላው መስፍኑ የ15 ዓመት ቆንጆ ልጅ ዘረችውና እርሷን አግብቶ ሀብቷን መርሶ ይኑር ብሎ ደግስ ሲያበደግስ ላለ ሊያስተል ጊታ ቅዱስ ጊዮርጊስን ለዚህ አላመመውምና የመስፍኑን ነፍስ ወሰደ። እርሱም ጎዘኑን ዘረሶ ወደ ቂሩት ሂደ። ደጀች ቂሩት ለኢያሱ ፍርጅ ያለች ቅድሩ ሴሬ አምላኮ ጽኑ የሆነች ሀገር ናት። ሴምጂ ግን አገዚአብሔርን የማያውቁ ደራጎንን የሚያመልኩ ነበሩ። ደራጎን እንደገመር ሁለት ክንፍ እንደ ፍጥል ጀሀም እንደ አንበሳ ፈርሞግ ክንድና እግር እንደዘንዶም ጅራት ያለው አንተቱ አንደ ሰኖ የሰፋ ጥርሱ እንደአዞ ጥርስ የረዘመ ታላቅና አስፈሪ እርኖ ነው። ሲርመው ዊአር መሰኖ ያሉ እንስሳትን ጸአየር ያሉ አእዋፍን ጸዳር ያሉ እንስሳቱን አራዊቱን ፀትንፋሹ እያነደደ ይጠላ ነበር። ጠዚህም ምክንያት አገሩ ሲት ሲት ልጆቻቸውን እያጋሩለት ይኖሩ ነበር። ልጆቻቸውን ሰተተው ሲመገርሱ ሹሙን ልጆቻችንን ሰተተን መረዘን ሚስቶቻችንን እንዳንሰተ ያስነርሱ መናር አደቻለንም ካልሰጠነው ደግሞ ይፈጀናል። ስለዚህ ወደጸላ ሀገር እንሂዳለን አሉት። እኔም ልጅን አሞጣው ፀነራችሁን ትታችሁ እተሂዱ አላቸው።

ሂዱው ሲደርስ የሹሙን ልጅ ወስደው ከግንድ አሰሩለት። ቅዱስ ጊዮርጊስ ጠዚያ ሲያልፍ የልትሰዋን ድምጽ ሰማ። ምን ሆነሻል? አላት። ልእምላኮችን ልደራጎን ተሰተቼ ነው አልችው። አምላኮችው ወደት አለ? አላት። ምክንያ ሊፈልግ ጊያል፣ ከሥላ ይተናኮለሀልና ፈጥነህ ሂድ አልችው። እኔግ ምን ነየል አለች? ከኒ ጋር ያለው ግን እርሱ ያቸንፈዋል አላት። ይህን ሲእጋዙ ደራጎን ምድሪቱን እያነዋወጸ መጣ። ሊበላው ሲቀርብ ፀሎ እግዚአብሔር መርቶ ዚያማትብበት ጠዛዩ ያደረ ሰይጣን እንደ ጉም ተኖ እንደትዚያ ወኖ ጠፋ። ኃይሉ ያዝሎ። እንተቱን ዚታሰረችበት ጉመድ አሥር እሳ እጥተተች እሉ ጠደረበት ሆኖ ከተማ ደረስ ሕዝቡ ሲያስደጅን ነው ብለው ደጀሹ ጀመር። እጅናንቱ መሰላቸው። አምላኮችንን ስምን አመጣህብን አሉት ደዘ ራሱን እንቂ ጣዛን አልተቻለውም እንደምን አምላኮው ይሆናል? አላቸው። አምላኮችንን አንተውም አሉ። እንዚህ ካሳችሁማ ልትቂ እስፈጀችኋለሁ

አላቸው፡፡ ይህስ አይሁን ባይሆን ከገደልከው በአምላክህ እናምናለን አሉ፡፡ ከከተማ አውጥቶ በጦር ወግቶ ገደለው፡፡ ይህን እይተው በእግዚአብሔር ስም አምነው ተጠምቀዋል፤ አውሬውን ከገደለበትና ከመሀል ከተማ ሁለት አብያተክርስቲያን ሠርተዋል፡፡

በዚህ ጊዜ የፋርሱ ንጉሥ ዱድያኖስ ሰባ ነገሥታት ሰብስቦ ሰባ ጣያታት አቁሞ ይሰግድ ያሰግድ ነበረ፡፡ የአባቴን ምስፍና ተቀብዬ ልምጣ ብሎ እጅ መንሻ ይዞ ብላቴናቹ አስከትሎ ቢሄድ ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣያት ስገዱ ብሎ አውጆ ሕዝቡም ለጣያት ሲሰግዱ አገኘ፡፡

ለአምልኮተ እግዚአብሔር ቀናዒ ነውና እዘነ፡፡ ወርቅ ብሩን ለነዳያን መጽውቶ ብላቴናቹን አሰናብቶ ነገሥታቱ ከተሰበሰቡበት ገብቶ እነ ውእቱ ከርስቲያናዊ ወአአምን በእግዚአየ ኢየሱስ ክርስቶስ አለ፡፡ ዱድያኖስ ሦስት ዓመት ሙሉ ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣእት ስገዱ ዕል እንዲህ ያለኝ እንድ እንኳ የለም፡፡ ለመሆኑ የማን ልጅ ነህ? ሀገርህስ ዴት ነው? አለው፡፡ ከኒ ጋር ምን ጎብረት አለህና አባቴን ሀገሬን ትጠይቀኛለህ? አለው፡፡ ሌሎች ያወቁት ነበርና የዞሮንቶስ መስፍን ልዳ ልጅ ነው አሉት፡፡ አንተግ የእኛ ነህ በ10 አህጉር ላይ እሾምሃለሁ የኔን አምላክ አጽሁንን አምልክ አለው፡፡ ሹመት ሽልማትህ ላንተ ይሁን እኔ አምላኪ ኢየሱስ ክርስቶስን አልክድም አለ፡፡ ተቆጥቶ በእንጨት አሰቅሎ ሥጋውን በመቃጥን አስተፈተፈው፡፡ ረጃጅም ችንካሮች ያሉበት የብረት ጫግ አጫምቶ ሂድ አለው፡፡ ችንካሮቹ እግሮቹን በሳስተው ወጡ ደሙ እንደ ውኃ ፈሰሰ፤ አጥንቱ ደቀቀ፡፡ መሄድ አቅቶት አጎንብሶ ሄዷል፡፡ <u>"ሰላም ለመከየድከ በእግዐነ ሐጺን ዘተጽዕረ፤ እስከነሐርከ ድቡተ ሶበ ሰእንከ ሰጊረ"</u> እንዲል፡፡ መከራው ቢፀናበት ኦ እግዚአየ ኢትግድፉ ለነፍስየ እስከ አስተጎፍር ለዝንቱ ዕልው ይህን ከሠዲ እስካሰፍረው ድረስ ነፍሴን አትውሰድ ብሎ ወደጌታ አመለከተ፡፡ ቅዱስ ሚካኤልን ልከ ፈወሶታል፡፡ ሄዶ ጎፈር ኦ ዕልሙ አለው፡፡ በሰባ ችንካር አስቸንክር በእሳት አስተኩሶ አናቱን በመዶሻ አስቀጥቅጦ በሆዱ ላይ የደንጊያ ምሰሶ አሳስር እንዲያንከባልሉት አደረገ፡፡ የማይሞት ሆነ ሥጋውን በመጋዝ አስተልትሉ ጨው ነሰነሰበት፤ ሥጋው ተቆራርጦ ወደቀ፡፡ ከዝግ ቤት ትተውት ሄዱ፡፡ በመንፈቀ ሌሊት ጌታ በእጁ ዳሰ አስነስቶ ገና ስድስት ዓመት ስለ ሰሜ ትጋደላለህ ሦስት ጊዜ ትሞታለህ፡፡ በአራተኛው ታርፋለህ አለው፡፡

ሲነጋ ከንጉሥ ሄዶ አንተ ከሠዲ እፈር አምላኪ አዳነኝ አለው፡፡ በሥራይ የሚያቸንፍልኝ ባገኝ ቤቱን በወርቅ እመላለታለሁ አለ፡፡ አትናስዮስ የተባለ መሠርይ መጥቶ ንጉሥ ሺህ ዓመት ንገሥ ጠላትህ ይደምስስ አለው፡፡ በምን እውቀዋለሁ አለው፡፡ ላም አስመጥቶ በጆሮዋ ቢያንሾካሽከባት ከሁለት ሰንጥቃለች፡፡ ለጊዜው እርሱንም እንዲህ የሚያደርግለት መስሉት ደስ

አለው፡፡ ሆድ በጥብጦ አንጀት ቆራርጦ የሚገድል መርዝ ቀምሞ አስማተ ሰይጣን ደግሞ ሰጠው፡፡ ስመእግዚአብሔር ጠርቶ ቢጠጣው እንደጨረቃ ደምቆ እንደአበባ አሸብርቆ ተገኘቷል፡፡ ጠንቋዩ ማረኝ ብሎ ከእግሩ ወደቀ፡፡ መመለሱን አይቶ የቆመባትን መሬት በእግሩ ረግጦ ውኃ አፍልቆ ወደጌታ ቢያመለክት ሐዋርያው ቶማስ በአካለ ነፍስ መጥቶ አጥምቆት ጥር 23 ቀን አንገቱን ለሰይፍ ሰጥቶ በሰማዕትነት ዐርፏል፡፡

እሱን ግን በመንኮራኩር አስፈጭቶ ከጥልቅ ጉድጓድ ጥሎት ደንጊያ አትሞበት ተመለሰ፡፡ ጌታ የተፈጨ ሥጋውን በእጁ ዳሰ መንፈሱን መልሶ እንሥቶታል፡፡ እግረ መንግዱን አሕዛብን እያስተማረ ከንጉሥ ቀረበ፡፡ አንተ መስሀት እፈር አምላኪ ከሞት አነሳኝ አለው፡፡ ተበሳጭቶ በብረት አልጋ አስቸንክሮ ከበታቹ እሳት አንድዶበታል፡፡ እሳቱም ደሙ ቢነጥብበት እልም ድርግም ብሎ ጠፍቷል፡፡

ከዚህ በኋላ ከርስቶስ አምላክ ነው ትላለህ ምን እድርገህ ታሳየናለህ? አሉት የለመለሙትን ዕፀው አድርቆ የደረቁትን አለምልሞ፤ ከሞቱ 430 ዘመን የሆናቸው ሙታንን አሥነስቶ አሳይቷቸዋል፡፡ በረሀብ በጽም ይሙት ብሎ የሚላስ የሚቋመስ ከሌላት ደኃ መበለት ቤት እንዲታሰር አዘዘ፡፡ ከምሶው ጋር አሠሩት፡፡ ራበኝ አብዬኝ አላት፡፡ የምትሰጠው ብታጣ ወደደጅ ወጣች፡፡ ስትመለስ የታሰረበት ሙሰሰ ለምልሞ 15 ክንድ ያህል ከማራው አልፎ፤ ካጠገቡ እንጀራ የተመላ መሶብ ተቀምጦ አጎሉ ዘይቱ በየዕቃው መልቶ አገኘች፡፡ ናሁ አምላክ ገሊላውያን ተመሊሉ ሰብአ ወረደ እምሰማይ ወበአ ውስተ ቤትየ የገሊላውያን አምላክ ሰው መስሉ ከሰማይ ወርዶ ከቤቴ ገብቷል፡፡ አለች፡፡ አገልጋዩ እንጂ እርሱን አይደለሁም አላት፡፡ ጆሮው የማይሰማ ዓይኑ የማያይ አፉ የማይናገር ሐንካሰ ልጅ ነበራት፡፡ ሰው እንዳያየው ሸሽጋ ታኖረው ነበር፡፡ አምጥታ ሞኑን ብታሰነካው ዓይኑ ሸርቶለታል፡፡ ጌታዬ ጆሮውንም አፉንም እግሩንም ፈውሰው አለችው፡፡ ይህ ጊዜው ገና ነው አላት፡፡ እርሱንም ቅዱስ ሚካኤል ከእስር ፈቶት መበለቲቱን ከነልጇ አጥምቆ እያስተማረ ወደንጉሥ ተመለሰ፡፡

ንጉሥ ዱድያኖስ የሚያደርገው ጠፋው፡፡ በመንኮራኩር ፈጭታችሁ ደብረ ይድራስ ወሰዳችሁ ንዙት አለ፡፡ ፈጭተው ወሰደው ቢነዙት ሥጋው ያረፈበት ሣር ቅጠሉ ደንጊያው እንጨቱ ሁሉ ጊዮርጊስ ቅዱሱ ለእግዚአብሔር ጊዮርጊስ ሰማዕቱ ለእግዚአብሔር እያሉ አመስግነዋል። ጌታም ሦስተኛ ከሞት እንሥቶታል ቁፍርቹን ተከትሉ አምላኪ ከሞት አዳነኝ አላቸው፤ ደንግጠው ከእግሩ ሥር ወደቁ፡፡መሬቱን ከእግሩ መትቶ ውኃ አመንጭቶ ቅዱስ ዮሐንስ አጥምቋቸዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ንጉሥ ልሹመህ ልሸልመህ ለአትሉን ስገድ አለው፡፡ ከሾምከኝማ ሌላ ምን አሻለሁ እሺ አሰግዳለሁ አለ፡፡ እንኪያስ እስከዛሬ ባስከፋሁህ ይቅር

በልኝ ብሎ ክአልፍኝ አስተዋፅ ወጣ። ንግሥቲቱ አለአስክንድርያ ትባላለች። ስሙ አማሊሳዊልር ወርቀ ሲያመሰግን ሰምታ ምን ማለት ነው። ይህን ምክንያት አድርጎ አስተምሮ አሳምኗታል።

ዲኦን ጊዮርጊስ ለአድሱን ሊሰግድ ነውና ከአደባባይ ተሰብስቡ ብሎ አዋጅ አስነገረ። ሃች መብለት ልጇን አትፋ ሀብት ይውን ጊዮርጊስ ለአድሱን አይሰግድም እያለች ታልትስ ነበር። ልጅዝን ከዚህ አትሪው አላት። እናረችው።ተነሥተህ መልእክቴን አድርስ አለው። ተነሥቶ ቆመ። ከዚተ ጣኦት ጉብተህ አድሱንን የክርስቶስ አገልጋይ ጊዮርጊስ ይመራዋል በለው አለው። ጊዶ ዚመራው ወዚያ ያደረ ሰይጣን አል ሊተ ወደ ሊተ እያለ እያምሽ ሕሱን ተክትሉ መጥቶ ከፈቱ ቆመ። ሕሱ ወዚህ አጋማሚ እግሩን ጀርውን አቶን ተፈውሷል። ወውጉ አንተ እምላክ ነህን አለው ዚመውልኝ ይሰግዱልኝ እንጂ አምላክ አይደለሁም አለ። እንዚያስ ዳታንንና አዚርንን የዋሙች ምድር ትዋተህ አለው። ምድር አፏን ከፍታ ውጣዋልች።

ንጉሥ እንዲያደንቁልት የሰበሰባቸው ሁሉ የሚያደንቁበት ዚሆን ልብሱን ተደ እንደ እብድ እያስፈለፈ ከአልፍኑ ገባ። ንግሥቲቱ ምን ሆነ! አልችው። እንዚህ አደረገብኝ አላት። እኒግ እንጂ ነገሬህ አልነዚረምን ጊዮርጊስን አስከሬ ያመታቸው አደዚታህም ትምህርቱን ሰምተህ ተአምራቱን አይተህ ከክርስቶስ አትመለስም? አልችው ፀጉሯን ይዞ እያንተተ መሬት ከነሥቱ ፈት አዘኖ ፍረዱኝ አላቸው። ትተግ አሉት። ሰርቃኒን አሰቅሉ ብለዮ አስቆቷት ደግ ጥምት ሆኗ በስግብትነት ወርፋልች። "ብአሲተ ንጉሥ ከሠዚት እንተ ትኩንን አእዘ፤ በአረ መጥቀት ከላዩ ተደመተክ መዚሠ" እንዚል አስተማሪዋን ተድግ አርፋልች።

ትምህርቱን ሰምተው ተአምራቱን አይተው ያመኑ በሺህ የሚቆጠሩ ነበሩ። እነሱንም በለይፍ አስመታቸው። አሱንም በለይፍ ሲቀጠት ደጨመት ሲጀጹ መከራዉን ሥቃዩን ተቀብለህ ከሆነ በአለያስ ታል ከሰማይ ወርዳ ሠላቶቹን የሚጥች እላት እኒህን ሠላውያን ትዘጥተው ብሎ ወደጊታ አመለከተ። ወዚያውም ንጉሥ ግብር እንብቶ ከአሥራሽ ተገኝቶ ሲዘዳ ሲጠግ እላት ከሰማይ ወርዳ ገዘላብሚቸዋለች። ሁሉቸ ጊድሏን የጸደ ያጸደ። መታዘዚያቱን ያደረገ። በሰሚ ዚተከርከቲያን ያነጽ። ቁመከራ ሆኖ በሰሚ የተማከለ ሁሉ ዚሥጋው ረድኤትን በነፍሱ ምሕረትን የሚያገኝ ይውን ብሉ ሰመከ። ወዚህ ጊዜ ሐግያት ተከፈቱ ምድር ተናወጠች። ጊታ መላእክቱን ዝዚያትን ሐዋርያትን እስከትው መጥቶ ሐሳም ዕክ እ ጥራደኛ ጊዮርጊስ ሐሳም ላንቱ ይውን የክመከው ሁሉ ይሁንለህ እንተም እንጂ ሰባት ዓመት ሐዘን ነገሥትን ታገለህልና ዘክመራጽሳኩ ዘአዘ ኢተንሥእ እምተወልደ አንስት ዘሆነው ሰምሐንስ መጥምቅ ፈቶች ከወሰፏቸው ዮሐንስን የሚበልጥ እስተነሳም //ማቴ 11፡11// ያልኩትን እንደፈጸምክ ከገዛህዚ እብክክ ሐልሶ ዘደመከክ እምክሱሙ ማንበረ ሰማዕት አለ እምትድጊክ መልምድጊረክ

እንዲሁ ከማንበረ ሰማዕት የሚመለስህ የሚስተካከልህ የለም" ብሎ ተሰፋውን ነገርታል። ቁፍርቹ ግን ይህን ሊያዩ ሊሰሙ አልታደሉምና ከወደቁበት ተኝተው ያንከራቱ ነበር! ተስትሶ የታዘዝችሁትን ፈጽሙ አላቸው። በሰይፍ መትተውታል። በመቱትም ጊዜ ደም! ውኃና ወተት ከአንገቱ ፈሷል። ጊዜው ዘጠኝ ሰዓት ነበረ። ዕድሜውም 27 ዓመት ነበር።

ጊታም ስለ ሰባት ዓመት ተጋድሉው ሰባት አክሊላት አቀዳጅቶታል። በሰማይም ኩላ ነፍስ ማዕምንት ለእሙ ወጽአት እምሥጋ ትሰግድ ቅድመ ለሥሉስ ቅዱስ መካዕበ ለትድስት ድንግል ወላዲትየ ወእምዝ ይለድዋ ጎበፍቱርየ ጊዮርጊስ ከሙ ትሰግድ ሉቱ ብሉ ኩብሩን ነግርለት ነፍስ ሁሉ እጅ ትነሳዋለች።



ገድል ያለመለመው የወንጌል ተከል
የጊዮርጊስ ስሙ ጥዑም እምአስካል
አይደርት አይጠወልግ ሁሌም ያብባል።
ሹመት ሽልማቱን ክብሩን ሁሉን ትቶ
ታስር ተገረፈ ለአምላኩ ክብር ተንተ።
ኧረ እንደምን ቻለው ያን ሁሉ መከራ
ተቆልቶ ተፈጭቶ እንደእኅል ሲዘራ።

እኔስ ይጨንቀኛል ገድሉን ሳስበው
ሰባት ዓመት በገድል ይኖራል ወይ ሰው?
ዛሬስ እንዳንዱ ሰው እጅግ ያሳዝናል
ገና ምንም ሳይሆን ክሩን ይበጥሳል
ሰው ጊታውን ሲከድ ለሥጋ እያዘነ
ጊዮርጊስ ለአምላኩ እስከሞት ታመነ
አክሊልን የሚያሰጥ ይኼው ለሰሙን

ማቴ 10 : 39 ራእ 2 : 10

ሚያዚያ - 27 ዕረፍቱ ለፈቅጠር ሰማዕት

ሀገሩ አንጾኪያ ነው። አባቱ ጎርግናስ እናቱ ማርታ ይባላሉ። የቅዱስ ፋሲለደስ የእህት ልጅ ነው። ንጉሡ ኑማርያናስ ተንባላትን ሊወጋ ሲዘምት እርሱም አብሮ ዘምቷል። በጦርነቱ ንጉሥ ሞተ። ፈቅጠር በተሰለፈበት ጠላት ድል ነሥቶ ድንበር አስፍቶ ወደከተማ ቢመለስ የንጉሡ ፈረስ አቅራቢ የነበረ አግሪጳዳ (ዲዮቅልጥያናስ) የንጉሥን ሴት ልጅ አግብቶ መንግሥት ወርሶ አገኘ። በዚህ አዝኖ ከፋም በጎም ሳይናገር ብዙ ጊዜ ተቀመጠ። ኋላ ግን ዲዮቅልያናስ አብያተ ጣዖታት ይትራኑዋ ወአብያተ ክርስቲያናት ይትዐጸዋ ብሎ ሃይማኖት ሲያስከድ ለጣዖት ሲያሰግድ የወንድሞቹን መንግሥት መንጠቁ አንሶት ደግሞ እንዲህ ይለናልን ብሎ ሊጣላው ሰይፍ መዞ ቢሄድበት ሸሽቶ ወደግጀት ገባ። እርሱንም ቅዱስ ፋሲለደስ ስለ ክርስቶስ ልንሞት እንጂ ልንገድል አይገባም ተው አለው። ንጉሡም በአግላጅ በአጓዳጅ ታረቀው።

እሱም እጹ ከምጽዋት አንደበቱ ከጸሉት ሳይለይ ሲኖር ቴዎድያዳ ከሁለት ልጆቿ ጋር ክርስቶስን አልክድም ለጣዖትም አልሰግድም ብላ በሰማዕትነት ሞተች። ንጉሥ ቀብር ከልክሉባት ሥጋዋ ከአደባባይ ወድቆ ዋለ አደረ ይህ ፈቅጠር ከወደቁበት አንሥቶ ቀበራቸው። መሳፍንቱ በዚህ ምክንያት ከንጉሥ አጣሉት። ጠርቶ ምነው እንዲህ አደረግህ አለው የወደቀን ማንሳት የሞተን መቅበር ምን ጥፋት አለው ይልቁንስ አንተ እስክመጽ እንዲህ ስትል ትኖራለህ? አለው። ወገኖቹን ፈርቆ በድብቅ አፉን እንደፈረስ አስለጉሞ ወደ እስክንድርያ አጋዘው። ሹሙ ሀርሜኔዎስ ራሱን እሰኪስት ድረስ አስገረፈው። ሥቃዩ ቢጸናበት ወደጌታ አመለከተ። የታዘዘ መልአክ በአካለ ነፍስ ወስዶ ጌታ ያዘጋጀለትን መካነ ዕረፍት አሳየው። ጌታ እንጂ ሑጥቂት ሀሣር ብዙ ከቡር በእንድ ሞት የዘለዓለም ሕይወት ይሰጣልና ብሎ በጥብዓት የሚጋደል ሆነ። ያም በደንጊያ አሰወግር በእሳት አስተኩሶ የማይሞትለት ኪሆን ወደ እንዲናው ላከው። ቢያሥሩት ተፈትቶ ቢገድሉት ተነሥቶ ያገኙታል። በችንካር ቸንክረው ሰትለው ተዉት። ይህን ታይ የነበረች የ15 ዓመት ብላቴና እሰይ እሰይ እልል እልል አለች። ምነው ለሞተ ሰው ዋይ ዋይ ይባልለታል እንጂ እልል ይባላልን አሏት። መላእክት ሰማያዊ አክሊል ሲያቀዳጁት አየሁ አለች። እንግዲህማ ብዙዎችን ሊያምንብን አይደለምን ብለው በሰይፍ መትተውታል።

• በ4ኛም. ዓድ፡ል፡ክ መጀመሪያ ላይ ነው

ፈቅጠር ምዕመኑ ለአምላክ ክርስቶስ
ተወካሌ ሕማም አርከ ጊዮርጊስ
ከኃጥአን ጋራ ከሚኖር ተዋዶ
መሞትን መረጠ ስለጽድቅ ተሰዶ።
እንደፈረሰ በሐብል ቢለጎም አፉን
በእምነቱ ጽናት መሰከረልን
የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነቱን።

አመጾችቶ ሰጥቶ ለችንካር እጆቹን
አሰቦ አለቀሰ የጌታ ሥቃዩን
ስለሰው ልጅ ብሎ የተቀበለውን።
ሞቱ ለጻድቅ ሰው ነውና ሕይወቱ
መላእክት ዘመሩ ጻድቃን ተደሰቱ
አልል አልል አለች ሕፃኗም ከፈቱ

መዝ 115፡

ሚያዚያ 30 - ዕረፍቱ ለማርቆስ ወንጌላዊ

ማርቆስ ማለት ንህብ፣ አንበሳ፣ ካህን ማለት ነው። ንህብ የተባለ ንህብ ሁሉን እንድተቀስም እርሱም አስቀድሞ ከጌታ ኋላም ከሐዋርያት ስለተማረ ነው። አንበሳም የተባለ አንበሳ ላህምን እንደሚሰብር እርሱም በአምላስ ላህም በአምላለ ጣያዋ ተሠርተው ሲመለኩ ነበሩ የግብጽን ጣያታት አጥፍቷልና ነው። ካህን የተባለም ወአምጽኡ ማሬ ዘድዮስ ባለው ሄዶ ነው። ሐዋ 14፡13 ቀዳሚ ስሙ ዮሐንስ ነው። ሐዋ 12፡12 ቁጥሩም ከ72ቱ አርድዕት ነው። አባቱ አርስጠቦሉስ እናቱ ማርያም ይባላሉ። ይህች ማርያም ሐጌታ ያመነች ወንጌልን የተቀበለች ጌታም ካረገ በኋላ ቤቷን ለሐዋርያት ቤተጸሉት አድርጋ የሰጠች አነርሱንም በተልዕኮ ያገለገለች ከ36ቱ ቅዱሳት አንስት አንዷ ናት። ሐዋ 12፡12

ጌታ ካረገ በኋላ ሐዋርያትን እየተከተለ ይማር ያገለግል ነበር። በርናባስንና ሳውሎስን ተከትሎ አንጾኪያ ወርዶ አስተምሯል። ሐዋ 12፡25

ከዚያ በኋላ ቅዱስ ጴጥሮስን ተከትሎ ሮም ወረደ። ቅዱስ ጴጥሮስም ከፍጹምነት መድረሱን አውቆ ጵጵስና ሾሞ ከሀገረ ስብከቱ ግብጽን ከፍሎ አስተምር ብሎ ሠጠው። እሱም ወደ ግብጽ ሲሄድ ከከተማው በር ሲደርስ የጫማው ጠፈር ተበጠሰበት። አንያኖስ የሚባል ጫማ ሰፊ አግኝቶ ስፋልኝ ብሎ ሠጠው። ሲሰፋ እጹን ወግቶት ኢስ ታአስ ብሎ ጮኸ አሐዱ እግዚአብሔር ማለት ነው። የጠራኸውን ታውቀዋለህን አለው። ሲሉ ሰምቼ እንጂ ያስተማረኝ የለም አለው። ፈቃዱን አይቶ አስተማረው። ከነቤተሰቦቹ ከነንረቤቶቹ አምኖ ተጠምቋል።

"የሀገሩን ሰርዶ በሀገሩ በሬ" እንዲሉ አንያኖስን ጸያሔ ፍኖት አድርጎ ያስተምር ጀመር። ሕዝቡም ትምህርቱን ሰምተው ተአምራቱን አይተው አመኑ ተጠመቁ። ካመኑም ዘንድ ጣያታቱን አፈራርሰው አብያተ ክርስትያናት ሠርተዋል።

ገነውተ ጣያቱ በጠላትነት ተነሱበት። ምዕመናን አባታችን ልናጣህ አንሻምና ቁጣቸው እስኪበርድ ወደሌላ ሄደህ ቆይ አሉት። እረኛ የሌለው መንጋ እንዳይሆኑ አንያኖስን ኢኢስቆጰስ ልጆቹን ቁስ ዲያቆን አድርጎ ሹሞላቸው በባርቃና በአቅራብያዋ ባሉ 5 አህጉር እየሰበከ ቅዱስ ጴጥሮስን ለመጠየቅ ወደሮም ሄደ። ከዚያ ሆኖ ወንጌሉን በልሳነ ሮማይስጥ ጽፎታል። ዘመኑም በአብነት መጻሕፍቶቻችን ጌታ ካረገ 11ኛ ሲፈጸም 12ኛ ሲጀመር ቀላውዴዎስ ቂሳር በነገሠ በ4ኛ ዓመት (ዓ.ም 45-46) ነው።

በመዝገበ ቃላት ግን በ60 ዓ.ም ተብሎ ተጽፏል።

የቂት ጭንቃትን ቆይቶ ቢመለስ ምእመናን በዝተው እግሩ ደስ አለው ገበረ የበራው በትሉ የተከለው ጀድቶ ቢያይ ደስ እንደሚለው በግለ ትንሣኤን ከክርሱ ጋር ሊያከብር እኒያ ዓለውያን መመለሱን ሰምተው ሊሚሉት መጡ ምእመናንም አዛታችን ሽሽ አሉት ናላዊስ ጌር ይሚሉ ነፍሶ በእንተ አባግኢሁ ዮሐ 10:11 እንዲል መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበጉቹ ይሰጥ የለምን አይሆንም አልሸሸም አለ። እንደ ሳም በእንጉቱ ጉድ አስረው በረሀ ለበረሀ ሲጉትቱት ዋሉ። ሥጋው ቢእሾህ ቢጋራጣ ተበሳ። ወደ ጌታ ቢያመለክት ለርሱ ተገልጾ ሥቃይህን አይቼ ልመናህን ሰምቼ ሳላርፍህ መጣሁ። ስለ ተቀበልከው መከራ ክብርህን ከ12ቱ ደቀመዛሙርቱ አንድ አድርጌሃለሁ። በስምህ የተማጸንኝን እምርልሃለሁ። ብሉ ቅድስት ነፍሱን ከሥጋው ለይቶ ቢቃሉ አትርጉት በስብሐት መላእክት አሳርጓታል። በዚህ ጊዜ የሰባ ዓመት አረጋዊ ነበር። ዘመኑ እንደአብነት መጽሐፍቶቻችን ተፋውዲያስ ቄሣር በነገሠ በ11ኛ ዓመት እንደ መዝ ቃላ ግን በ67 ዓም ነው።

እኒያም ሥጋውን እናቃተላለን ብለው እንጪት ሲረበርቡ ሄፍት ሲያርከፈክፉ ቃላት ነጉድጋድ ሆነ ምድር ተናወጸች ፀሐይም ብርሃኗን ከለከለች ዎን መጣብን ብለው ሸሽተዋል ኋላ ግን ምእመናን ብርሃነ መብራት ተክቦ እግኙተው ተብረውታል። ዕለም ለግርቆስ ለግርያም እኃ፣ ዘከሀዲዎ በዘዳል/ ውስተ አዕደዊሁ ከመጸበላ፣ እመ አውጽኦ ፈቀዱ ለእሳት በከበሳባላ ሄናም ወአለሐትያ አጥፍኔ ግዘሳ፣ ወመብረት ለሥጋሁ ከለላ እንዲል አርክ፡



ምዕራፍ 3

ግንቦት 1 ልደታ ለማርያም እግዝእትን

እመቤታችን በፈቃደ አምላክ በብስራተ መልአክ ነሐሴ 7 ቀን ተጸነሳለች። በማኅፀንም ሆና ብዙ ተአምራት አድርጋለች። ሁለቱን ለአብነት ያህል እናያለን።

1 ሐና በርሴባ የምትባል አንድ ዓይና አክስት ነበረቻት ልትጠ ይቃት መጥታ ሳለ እግዚአብሔር በቸርነት ጉብኘሽ ብላ ማኅፀናን በዳሰሰችበት እጇ የጠፋ ዓይናን ብታሸው ዘርጉላታል። ሌሎችም እንዲሁ ሆዷን እየዳሰሱ ድነዋል

2 ሐና የምትወደው ሳምናስ የሚባል የአጐቷ ልጅ ሞቶ በዚተሰብ ልግድ የአልጋውን ሽንኮር ይዛ ስታለቅስ ጥላዋ ቢያርፍብት ሙቱ አፈፍ ብሎ ተነስቶ ሰላም ለኪ ኦ እምሔሙቱ ለዘገብረ ሰማየ ውምድረ ሰማይና ምድርን የፈጠረ የአምላክ አያቱ ሐና ሰላም ላንቺ ይሁን ብሎ መስክሮ ተመልሶ አርጅል።

ከዚህ በኋላ አይሁድ ለምቀኝነት አያርፉምና ቀድሞ ከእኒህ ወገን የሆኑ

ዳዊትና ሰሎሞን አርባ አርባ ዘመን ገዙን አሁን ደግሞ እነዚህ የወለዱት ሊገዛን ነውን ብሎ በጠላትነት ተነሡ ቅዱስ ገብርኤል አያቄምን ሐቅለ ሊባናስ ይዘሀት ሂድ አለው ይዟት ሄደ። ጊዜዋ ደርሶ ዝርና በዚህ ዕለት ኦቢያት ትንቢት የተናገሩላት ምሳሌ የመሰሉላት አያቶጅ ቴክታ በጥሪቃ በጨሪቃ አምሳል ኢያቄምና ሐናም በርግብ አምሳል ያዩአት እመቤታችን ተወለደች። በሊባናስ መወለጃም ሰሎሞን ንጂ እምሊባናስ መርዓት ንጂ እምሊባናስ መኃ 4:9 ያለው ይፈጸም ዘንድ ነው።

የተወለደችው በ 16 ዓ.ዓ ነው።

ሙዝዘ ርኀራኄ ድንግል ማርያም
ወልዳ የሠጠን የዓለምን ሰላም
ለመላእክት አጎት እናት ናት ሴም።
ክብርት ናትና አምላል የሌላት
ድንግል ተመለደች በመልአክ ብሰራት።
ድንግል ስትመለድ በአምላክ ቃልኪዳን
የሊባናስ ጋራ ተመላች በብርሃን
ሐሤት አደረገን በፍጹም ደስታ
ምስጋናም አቀረብን ለአምላክ በፅልታ

የድንግል መወለድ ከእያቄም ኪሐና
ሰጋጠብተው የኖርን ተስፋችን ነውና።
ዘመድም ባታጣ ወዳጅ ቢኖራት
ሐና ምትወልድበት አልተገኘም ቤት።
እንኳን ቤት በረቱን አይሁድ ኑፍጥት
በደብር ተወለደች የአምላክ እናት
አባቷ ሰሎሞን ቢቃለ ትንቢት
ንጂ እምሊባናስ አንተየ መርዓት
ብሎ እንደዘመረ እንዳወደሳት።

መ ኃ 4:9

ግንቦት 5 እረፍቱ ለኤርምያስ ነቢይ ከ626 - 515 ዓ.ዓ

ኤርምያስ ማለት እግዚአብሔር የሚያውቀው ጎሩይ እምከርሠ እሙ ማለት ነው። ቁጥሩ ከአራቱ ሀበይት ነቢያት ነው አባቱ ኬልቅያስ ይባላል በዓናቶት የሚኖር ካህን ነበር። ከኢዩአስ ዘመን መንግሥት እስከ ሚጠተ እስራኤል ድረስ አስተምሯል።

ንጉሡ ኢኮንያን ይባላል ሦስት ወር እንደነገሠ ናቡከደነጸር ከፋርስ መጣ እሱን አሥሮ ሕዝቡን ማርኮ ሲሄድ ወንድሙ ናታን ከመንገድ ቆይቶ እነኔ ብታነግሠኝ እስራኤልን አስገዛልህ ነበር ብሎ ሹመት ለመነ። ስሙን ባትከዳኝ ሲል ሴዴቅያስ ብሎ ከምርኮ በቀሩት ላይ ሹሞት ሄዷል። እርሱም 8 ዓመት ሲገብር ኖሮ ቅጽሩን ካሸፋ አንባውን ካዳና በኋላ አልገብርም አለ። አስቀድሞ በሞአባውያን መንፈቅ ያህል አስከበበው ኋላም እርሱ ሁለት ዓመት ከበበው። ወደ እግዚአብሄር አመልክትልኝ ብሎ ወደ ኤርምያስ ላከ ከሕዝብህ ጋር ትማረካለህ አለው አንተማ በጉ ተናግረህልኝ አታውቅም ብሎ እጅ እግሩን አሥሮ ከጥልቅ ጉድጓድ አስጣለው። ጌታ ቅዱስ ሚካኤልን ልኮ በአቤሜልክ አድሮ አውጥቶታል። ኤር 38: 7- 11 እስራኤል ረሀብ የሚጐዳቸው ቢሆን ንጉሣችንን በምክንያት እናድናለን ብለው እንደ ሞተ ሰው ገንዘው በአልጋ አድርገው ዋይ ዋይ እያሉ ይዘውት ሲወጡ ናቡከደነጸር የሰውን ብዛት አይቶ ምንድር ነው ብሎ ጠየቀ። የእስራኤል ንጉሥ ሞቶ ሊቀብሩት ይወስዱታል አሉት እሱንማ አጥቤ ገንዘ ልቀብረው ይገባኝ ነበር። ያም ባይሆን ልሳመው አምጡት አለ። አስመጥቶ መገነዙን ፈትቶ ቢያየው ቁልጭ ቁልጭ ይላል። ምነው ሳምንህ ከዳኸኝ አሁንስ እንጂ እኔን ከዚህ አስቀምጠህ ወዴት ልትሄድ ነበር አለው ዝም አለ መሳፍንቱን ፍረዱኝ አላቸው እችላለሁ ብሎ አይዋጋ ወይ አልችልም ብሎ አይገባ ሞት ይገባዋል አሉ ፍርድ አላወቃችሁም ሞቱ ለብእሲ ዕረፍቱ ሞትማ እረፍት ነው ብሎ ሰባት ልጆቹን በሰይፍ አስመትቶ እሱን ሁለት ዓይኑን አውጥቶ በፈረስ ጭራ አስሮ እያስጐተተ ባቢሎን አወረደው ጫን ባቄላ ሲፈጭ ከወፍጮ ስር ልቡ ፈርሶ ሞቷል።

ለኤርምያስ አቤሜልክና ባሮክ የሚባሉ ምድያማውያን ደቀመዛሙርት ነበሩት ከዚያ በፊት የምርኮን ነገር ሲናገር እየሰሙ

ኢታርአያን ሙሽዝ ወብድወታ ለኢየሩሳሌም የኢየሩሳሌምን ጥፋት ኢታሳዮን እያሉ ያለቅሱ ነበር። ጊዜው ሲደርስ ባሮክን መቃብረ ነገሥት አስጠበቀው አቤሜሌክንም ለድውያን የምንቀባው አጽቀ በለስ እምጣ ብሎ ላከው እርሱ ግን ከሕዝቡ ጋር ተማርኮ ፋይሰ ባቢሎን ወርዷል።

አቤሜሌክ በለሱን ቆርጦ በሙዳይ አድርጉ ሲመለስ ከጥላ ስር አረፍ አለ ወዲያውም አንቀላፍቶት ተኛ በተኛ በ66 ዓመቱ ነቅቷል ሲነሣ ጥለው ከተኛበት ጊዜ ጥቂት እልፍ ብሎ ነበርና ዘገይቻለሁ ብሎ ፈጥኖ ሊሄድ ቢሞክር መንገዱ ጠፋው። ቁሞ ሲመለከት መልኣኩ በአምሳሉ አረጋዊ ከተራራ ሲወርድ አየ። ሄዶ አይቴ ሀለው ኤርምያስ ወአኃውየ እነ ኤርምያስ ወዴት አሉ አለው። አንተኑ ነግዳ ለኢየሳሌም ለኢየሳሌም እንግዳ ነህን እነ ኤርምያስ ያሉ ባቢሎን በስደት ኢየሩሳሌምም ከጠፋች 66 ዓመት አለው አሪት ሽማግሌውን አክብር ብላኛለች እንጂ ጅጁ ጀጃዋ ብልህ በወደድሁ ነበር ለድውያን የምንቀባው በለስ አምጣ ብሎ ልኮኝ ይኸው ቅጠሏ አልጠወለገም ደሟም ይንጸፈጸፋል አለው አንተን ከመከራው ሠውሮህ ነው ብሎ በወራቱ አስረድቶ ወስዶ ክብሮክ አግናኘው አንገት ለአንገት ተቃቅፈው ተላቅሰዋል። ኋላም ቀኖና ቢገቡ እስራኤል ከምርኮ ሊመለሱ አራት ዓመት እንደቀራቸው ተገለፀላቸው ይህን ጽፈው ዐጽቀበለሱ ጋር ታቦ ቢመጣ ንስር አንገት ላይ አሥረው ላኩለት።

ኤርምያስ ሰው ሞቶበት ሊያስቀብር ሲሄድ ከፈረስ ግንብ ለጠገብ እስከሬኑ አሳርፎ ላለ ንስሩ በስሙ ጠርቶ ጣለለት ነገሩንም እንዲረዳለት ሙቱን በእግሩ ረግጦ አንስቶታል ሙቱም በወረቀቱ የተጻፈውን መስክሮ ተመልሶ አርፏል። ጽሁፉም ከምርኮ ለመመለስ አራት ዓመት ቀርቷልና ከአሕዛብ የተጋባችሁ ተፋቱ ያላገባችሁ ተጠበቁ የሚል ነበር። ብዙዎቹ እግዚአብሔር የተናገረውን አያስቀር ብለው ያገቡ ተፋቱ ያላገቡትም ተጠበቁ። የቀሩት ግን ሚስቶቻችንን አንፈታም ከሀገራችንም አንቀርም አሉ። አራት ዓመት ሲፈጸም ኤርምያስ በፈቃደ እግዚአብሔር እስራኤልን ሰብስቦ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። እኒያም ከኋላ ከኋላ ተከተሉት። ዛሬኦ አቤሜሌክ ሊቀበሏቸው ወጥተው የአሕዛብን ሴቶች አይተው ምነው እንዲህ አደረጋህ አሉት ሚስቶቻችንን ማን አፋቶን ሀገራችንንስ ማን ነሥቶን ብለው መጡ አላቸው ኃያላኑን መርጠው

አላደዋቸዋል:: ከዚያም ቢመለሱ ንቃችሁን ጠልታችሁን ሂዳችሁ የለምን ብለው አባረሯቸው:: ዮርዳኖስን ሳይሻገሩ ሀገር አቅንተው ተቀመጡ:: ምድሪቱንም ሠመርናሃ /ወደድናት/ ሲሉ ሰማርያ ብለዋታል::

ከምርኮ ከተመለሱ በኋላ ኤርምያስ የፈረሰውን ቤተመቅደስ አሠርቶ ንዋያተ ቅድሳቱን አሰናድቶ ዳግመኛ እግዚአብሔርን በድለው ይህን የመሰለ መከራ እንዳያገኛቸው ሲያስተምራቸው ቆይቶ በዚህ ዕለት ሕዝቡን ሰብስቦ የሥጋዌን ነገር ሲናገር የአምላክን ልጅ አምላክን አየሁት ይሩናልን ብለው በደንጊያ ወግረው ገድለውታል:: ተረ.ኤር 11:54 ዕብ 11 37

ግንቦት 7 ዕረፍቱ ለአትናቴዎስ ሐዋርያዊ

አትናቴዎስ ማለት ሞት ሕልፈት የሌለበት ሕይወት ማለት ነው:: ሐዋርያ የተባለው አንድ ቀን ከጴጥሮስና ከጳውሎስ መቃብር ሄዶ ሰላም ለክሙ ብጹዓን ሐዋርያት እያለ ሲጸልይ ለከሂ ይበሉከ ሐዋርያ አንተንም እንጂ ሐዋርያ ይሉሀል የሚል ጽምጽ ስለሰማና እንደሐዋርያት መከራ የተቀበለ የተሰደደ በትምህርቱ መናፍቃንን ተከራክሮ የረታ በተሠዉ በድርሰቱ ለቤተክርስቲያን ዓምድ ስለሆነ ነው::

ሀገሩ መኑፍ ነው:: አባት እናቱ አረማውያን ነበሩ የአባ አለ እስክንድሮስ ደቀመዘሙር ነው:: የአረማዊ ልጅ ከሆነማ እንደምን ደቀመዝሙሩ ሆነ ቢሉ አንድ ቀን አለእስክንድሮስ በመንገድ ሲሄድ ይህ አትናቴዎስ ከሕፃናት ጓደኞቹ ጋር እሱ እንደ ሊቀጳጳስ ሆኖ ጓደኞቹ እንደምእመናን ሆነው አጥምቀን እያሉ እያጠመቃቸው ሲጫወቱ አይቶ ቆሞ ይመለከታቸው ጀመር:: ተከታዮቹ አባታችን ከሕፃናት ምን ቁም ነገር ይገኛልና ቆመህ ታያቸዋለህ አሉት እንዲህ መሰሏቹህልን እኒህ ሕፃናት የሚሰሩት ኋላ ጌታሰአድሮ የሚሰራውን ነው ይህ ብላቴና አባቱ በሕፃንነቱ ይሞታል እናቱ አምጥታ ትሰጠኛለች እኔም ቀጥሎ የሚሾም እሱ ነው አላቸው::

ይኸውም አልቀረ አባቱ በዘመነ ረሀብ ሞተ እናቱ እንደወደደህ አድርገው ብላ አምጥታ ሰጠችው እያስተማረ አሳድጉ ከበታቹ ሾመው:: እርሱ ካለፈ በኋላ በርሱ ቃል በመንበሩ ሾመውታል 20ኛ ሊቀጳጳሳት ነው:: ተሹሞም ላለ ብዙ ተግሣጽ

ጽፋል ብዙ ድርሰት ደርሳል:: ከብዙውም አንዱ የቅዳሴ እግዚእ ለውጥ ሆኖ በሰንበት በክረምትና በደብረታቦር የሚቀደሰው ቅዳሴ ነው ብሎ ሕሙማንን ፈውሷል፣ በለበሰው ልብስም ሙት አንሥቷል:: ከትህትናውም ብዛት እንግዳ ሲመጣበት እንደ ብላቴና ዝናሩን ነጥቆ ወገቡን ታጥቆ እግር ያጥብ ነው::

ንጉሥ ቁስጠንጢኖስ ዘየዐቢ አርፎ ልጁ ቁስጠንጢኖስ ዘይንእስ ነገሠ:: የአርዮስ ወዳጅ የነበረ አውሳብዮስ ሄዶ ንጉሥ ብዙ ስለነበሩ አስወጥተውት እንጂ ይአርዮስ ሃይማኖት እውነተኛ ነበረች:: አለው እሱም ነገሩን ተቀብሎ አትናቴዎስን ከመንበሩ አስወጥቶ ሰደደው 7 ዓመት በስደት ኖሯል:: ተሰዶም በብሔረ ዐረብ ሳለ ዐረባውያን አምልኮ የሚፈጽሙበት ምኩራብ ጣዖት ነበረ:: ቆሞ ሲያየው ቆይቶ ወደ ጌታ ቢያመለክት የሰው እጅ ሳይነካው ፈርሶ የኮረት ክምር ሆነ ምን መጣብን እያሉ ሲታወኩ ነገሩ ከወደእግዚአብሔር የተደረገ መሆኑን አስረድቶ አሳምኖ አጥምቋቸዋል ቀሳውስት ዲያቆናትንም ሾሞላቸዋል:: ስንክሳር

ከሰባት ዓመት በኋላ ቢያከራክረኝ እከራከራለሁ ቢገድለኝም እሞታለሁ እንጂ እስክ መቼ በስደት እኖራለሁ ብሎ ከንጉሥ ቀረበ:: በገዛ እጁ ይሙት ብሎ አውሳብዮስን በአዲስ መርከብ የምርቶ ምግቡን ቀዛፊውን ሰጥቶ እሱን ግን ምግብ ቀዛፊ ሳይሰጠው በነቀዘ መርከብ አድርጎ ወደ እስክንድርያ ላካቸው አውሳብዮስ መርከብ ተሰብሮበት ሰጥሞ ቀርቷል:: እሱ ግን መላእክት መንፈሳዊ ምግብ እየመገቡት በአዲስ መርከብ አሳፍረው አድርሰውት ወደ መንበሩ ተመልሷል::

ከዚህ በኋላ አርዮሳዊው ቁስጠንጢኖስ ዘይንዕስ ሞቶ ዩልዮስ የተባለ ከሀዲ ነገሠ ሊገድለው ሲያስፈልገው ሸሽቶ ገዳመ አስሚም ገባ መሸሹ ግን ሞት ፈርቶ ሰማዕትነት ጠልቶ አይደለም ወሰበ ይሰድዱክሙ እምዛቲ ሀገር ጉዩ ጎበ ካልዕታ ማቴ 10:25 ያለውን አስቦ እርሱም እኔን ገድሉ በኔም ምክንያት የብዙኃን ደም ፈስሶ እዳ ፍዳ እንዳይሆንበት ብሎ ነው:: እሱም አልቆየም ሞተ ምእመናን አባታችን ጠፋብን ብለው ለአባ እንጦንስ ነገሩ ገዳመ አስሚም አለላችሁ አላቸው በአጀብ አምጥተው ወደ መንበሩ መለሱት ከዘህ በኋላ በሰላም ሲያስተምር ቆይቶ በተሾመ በ47 ዓመቱ በዚህ ዕለት አርፏል:

ዲቁ አትሩቴዎስ ደግ ሐዋርያው
ዕዜተክዘስቲያን የመ:ት ግምድ ነው
ርእሰ ደጸላት ክቡር ሰው ሲሆን
ቀርዞ አገር አጠበ የእንገዶቹን
ታዲያ ጻድት ቢሳል ያፀዘየልን
እስዚ ልብ በሉት ትሕትናውን
በመሩፍቃን ምክር ቢሰደድ ነገር:
ኦር አስተማረ ወንጌልን በሞር:
ነፍሰን በሚያረካ በተአም ትምህር:ቱ
ከአሕዛብ መንደር ጠፋተው ጣኦታቱ
በክብር ክቡ አለች የአምላክ ታቦቱ
የሸሀ ግንድ አር:ዮስ ከሠደት ፍሬውአተከ
ጻድቃንን ሲያጻግ ሥጋቸውን ቀር:ጠ
ጓላም አንዳ ያመከ ጉድው አቆጥፈጠ
በምስጢር ምሳሩ አትሩቴዎስ ልጠ
ከሰሩ ጣለው ፕዘንዝ ቆራር:ጠ
እስዚ እንደአባታችን ይኑረን ትዛትና
ራሰን ማዋረድ ክፉ ያደር:ጋልና

1ጴጥ 5 6

ግንቦት 8 ዕርገት

የተነገረው ትንቢት የተመለለው ምሳሌ ይፈጸም ዘንድ ጌታ በተቀበረ በሶስተኛው ቀን በሰንበተ ክርስቲያን ሙሃንዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳያል ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ተንሥኧል ተንሥቶም አር:ባ ቀን ለሐዋርያት መጽሐፈ ኪዳን አስተምሯል። ጉብኤ ሠር:ቶ ያስተማራቸው ሶስት ቀን ነው። በትንሣኤ በአግብኦተ ግብርና በጥብርያዶስ ወገንቱ ሣልሱ ለእግዚአነ እንዘ ያስተር:እዮሙ ለአር:ዳኢሁ እምድኅረ ተንሥአ እሙታን እንዲል ዮሐ 21: 1 በየቀኑ ግን ለአንዱ ለሁለቱም ሳይገለጽላቸው አያውልም አያድርም ነበር። በ40ኛው ቀን አንት-ሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም እስክ ትለብሱ ኃይለ እምአር:ያም ከሰማይ ኃይል እስክ:ጎኙ ድረስ በኢየሩሳሌም ቆዩ ብሏቸው እስክ ቢ:ንን አውጥቶ እስክ በትር:ያር:ክሳት ያለውን ጠሳረጣ በአንብሮተ እድ ሾሚቸው ዐር:ጋል። ሉቃ 24 50

ክአር:ባ ዝቅ ብሎ በ39 ከፍም ብሎ በ41 ያላደረገው በ40 ቀን ያደረገው አዳም በ40 ቀን አግኝቶ ያጣትን ልጅነት እንደመለሰ ለማመየቅ ነው። ማረጌም ክአመቤታችን በነሣው ሥጋ ነው። ስለምን

ቢሉ ተለየ ተለወጠ ላሉት እንዳይመ:ቸው አንድም ቅዱሳን ግረጋቸውን ሄት መንግሥት ሰማያት መሣባታቸውን ለማጠየቅ ነው ዐርገ ከመያለቡ ዕርገተ ጻድቃን ንኡሐን አንዲል መቅ ወን

ክርስቶስ ኢየሱስ የነለም መድኃኒት
ከሞት በተነሣ በአርባ ዕለት
መላእክት እጅበው እያወደሱት
በእልልታ ዐረገ በቃለ አትርንት
ከድንገል ማርያም የነሣውን ሥጋ
ልዕል ጌታ አረገ አክብር በጸጋ
በእጁ ባርኳቸው ሐዋርያትን
ጌታ ወደ ሰማይ ሲያረግ በሥልጣን

ጠብቁ አላቸው መንፈስ ቅዱስን
ቅዱሳን መላእክት ለርሱ እየዘመሩ
ጌታ በክብር ሲያርግ ቆመው የነበሩ
ያዩ ሐዋርያት ምንኛ ይከብሩ
በነብበን ሳንቀር ከሞት ተነስተን
ወደ ሰማይ መንግሥት ግረጋችንን
በርሱ የከብር ዕርገት እውቀን ተረዳን
እርሱ ዐርጎ ለኛ አብነት ሆነን

1 ተሳ 4 17

ግንቦት 9 ዕረፍታ ለቅድስት ዕሌኒ /ከ 255 328 ዓ.ም/

አየሁዳዊት የሮሓ ሴት ነች። ተርዚናስ የሚባል ባል ነበራት ነጋዲ ነበርና ለንግድ ሄዶ ሶስት አራት ዓመት ኑሮ ሲመለስ ባልንጀሮቹ ከግዕዘል ከሞገድ ድነን እንደወጣን ሚስቶቻችን ሌላ ወንድ ሳይለምዱ ብናገኛቸው መልካም ነበር አሉ። በሃይማኖት የጸናች ከገዚረ ኃጢአት የራቀች መሆኗን ያውቃልና እኔስ እንኳን ከግዕዘል ተርፍሁ እንጂ ሚስቴን በዚህ አልጠረጥራትም አላቸው ያንተ ሚስት ፍጥረቷ ከሔዋን ልጆች አይደለምን ሴት ጥንቱንም ምክንያተ ስሒት አይደለችምን አሉት በፍጹም አታደርገውም አለ አንዱ አሁን እኔ ቀድሜ ሄጀ ለምጃት ለምዳኝ ብመጣስ አለ አሱም ባይሆንልህስ ቢሆንልኝስ ጥሬቴን እሰጣለሁ ጥሬቴን እሰጣለሁ ተባብለው ተወራርደው ሄደ።

ከዚቱ አትራቢያ ደርሶ ከተርዚናስሚስት አገናኙኝ አለ። ስንኳ ሰው ፀሐይ አይቷት አያውቅም አሉት አገልጋያን አስጠርቶ እመቤት ዕሌኒን ላኑጋገራት እፈልጋለሁ ንገሪልኝ አላት ገብታ ብትነግራት ፊት ነሳቾት ተመልሳ አልሆነልህም አለችው። ገንዘብ ልስጥ ይላል ፀይልኝ አላት ነገረቾት ተቆጥታ በያዘችው መታቾት። ደሟን እያዘራች ውጥታ አይሆንም ስልህ እንዚ ብለህ አስመታኸኝ አለችው እንኪያስ ይህን ገንዘብ ላንቺ ልስጥሽ ሁለቱ የሚተዋወቁበትን ነገር አምጥተሽ ስጪኝ አላት። ይህንንስ

አደርግልሀለሁ አንተም ኑጋድያን መጡ የብስ ሬገጡ ብለህ አስወራ አለችው አስወራ ገብታ ኑጋድያን መጡ የብስ ረገጡ እየተባለ ነው ሰውነትሽን ታጠቢ ሽቱም ተቀቢ አለቻት:: ስታጥባት ከአንገቷ ያሠረላትን ዕንቁ ረስታው ገባች:: ወስዳ ሰጠችው ከመደብር ሄዶ ለምጃት ለምዳኝ መጣሁ ብሎ የያዘውን ዕንቁ አሳየው እውነት መስሎት ልመርምር ሳይል ጥሬቱን አስረክቦ ባዶ እጁን ገባ::

ዕሌኒ ግዘኑን መቆጣቱን አይታ ወንድሜ ምን ሆነህል እንደወትሮህ ደስ አላለህም አለችው ይህን ያህል ዘመን የደከምሁበት ጥሬቴን ማዕበል ሲወስድብኝ ምነው አላዝን አላት ይህማ እግዚአብሔር ያየነውን ቢነሣን ያላየነውን ይሰጠን የለምን በዚያውም ላይ ከዘመዶቻችን ተበድረን እንደወትሮህ ነግደህ እንኖራለን አለችው:: እኔስ አበድሬ በኖርኩበት ሀገር ተበድሬ አልኖርም አንቺን ግን ሁሉ ይወድሻል እንዳልሽው ሆነሽ ኑሪ ብሎ በነገሩ ይወርፋታል:: ተነሥቶ ሲወጣ እኔስ ካንተ ተለይቼ ወዴት እቀራለሁ ብላ ተከተለችው::

"ሦቦን አስጠርቦ ይዘ መርከብ ተሳፍረው ሲሄዱ እኅቴ ምነው ሳምንሽ ከዳሽኝ ሰወድሽ ጠላሽኝ አላት አንተን ጠልቼ ማንን ወድጃለሁ አንተን ከጀ ማንን ለመድሁ አለችው እንኪያስ ይህንን ለእገሌ ማን ሰጠው አላት ሠራተኛዋ መጥታ ነገረችኝ አይሆንም አልኳት ኋላ ገላዬን ስታጠብ ረስቼ ገብቼ ነበር እሷ ወስዳ ሰጥታው ይሆናል እንጂ እኔስ መልኩን እንኳ አላየሁትም አለችው አድርገሽው ከሆነ ሥራሽ ያጥፋሽ አላደረግሽውም እንደሆነ ሥራሽ ያውጣሽ ብሎ በሦቦን ከቶ ከባሕር ጣላት ማዕበል እየገፋ ወስዶ ጽንፈ በራንጥያ አደረሳት የበራንጥያ ንጉሥ ቁንስጣ ከባህር ዳርቻ ቆሞ ነበር የነጋዴዎች ወርቅ ይሆናል ብሎ አስወጥቶ ቢከፍተው ቁልሎ ቁልሎ ሰትል አገኛት ውበቷን አይቶ አላዋቂ ነውና የክርስቲያን እመቤት ማርያም አንቺ ነሽ? አላት የከፋኝ የቤት እመቤት እንጂ የርሷን የእግሯ እጣቢም አልሆንም አለችው ሥርዓተ አሕዛብ የሚያስተምሯት ሽቱ የሚዘጉላት ደንገጡሮች ሰጥቶ መንፈቅ ያህል የጠራ የለስለስ ሲመግባት ቆይቶ በመንፈቁ ተገናኛት ልጅ ወለደች:: ስሙ ቈስጠን ጢኖስ ተባለ እናቱ ከባሕር ተገኝታለችና ሐመልማል ማለት ነው::

እስከ አራት ዓመቱ ነገረ ሃይማኖት እያስተማረች አሳደገችው ጥምቀት ግን አባቱ አረማዊ ነበርና እንዳይጣላው ብላ

አሳስጠመቀችውም ወደ ሀገሯ ይዛው ከተመለሰች በኋላ አድጉ አካለ መጠን ሲያደርስ ጥበቡን ኃይሉን ሰምቶ አምቶቶ አንግሦት በሁለት ዓመት አረፈ እሱ በበራንጥያ ዲዮቅልጥያኖስ በሮም ተከታትለው ነገሡዋል:: የዲዮቅልጥያኖስ ንግሥና እንደምነው ቢሉ ቀዳሚ ስሙ ነገሬጳ ነው ሀገሩ ላዕላይ ግብጽ ነው ከሮሙ ንጉሥና ከኑግርያኖስ ቤት የፍየል እረኛ ሆኖ ሲያገለግል ይኖር ነበር:: ንጉሡ ሕንጥርብያ፣ ፍንጥርብያ፣ የሚባሉ ሴቶች ልጆች ነበሩት ታላቂቱ ሕንጥርብያ ድምፃዊ ነበርና ሲያንጐራጉር በገና ሲደረድር እየሰማች በሐጸዝሙት ተነደፈች አባቷ ጠላት ተነሥቶበት ዘምቶ በዚያው ሊሞት ስሙ መንግሥቱን ዲዮቅልጥያኖስ ብላ አግብታ አነገሠችው ከስምንት ዓመት በኋላ ታናሽቱ ፍንጥርብያም ቢትወደዱ መክስምያኖስን አግብታ በአንጾኪያ አነገሠችው::

ዲዮቅልጥያኖስ በነገሠ በ20 ቈስጠንጢኖስ በነገሠ በ19 መክስምያኖስ በነገሠ በ 8 ዓመት ዲዮቅልጥያኖስ በአባ ባጋግዮስ ምክንያት አብያተ ጣዖታት ይትራኑዋ አብያተ ክርስቲያናት ይተአጸዋ ብሎ አዋጅ ነገረ:: አብያተ ክርስቲያናት ተቃጠሉ፣ መጻሕፍት ተቆነጸሉ፣ ምእመናን በግፍ ታረዱ ተሰደዱም ኋላ ግን ዲዮቅልጥያኖስ ዓይኑን ታውሮ ተሰቃይቶ ሞቷል:: /ገድ.ጊዮ/ መክስምያኖስንም እርሱ ድል ነስቶታል:: እንደምን ቢሉ ከሞት ከሰደት የተረፉ ምእመናን መጥተህ አድነን ብለው ላኩበት:: ይህን ሲያወጣ ሲያወርድ ሌሊት በራእይ «በዝ ትእምርተ መስቀል ትሙዎ ለጸርከ» የሚል ጽሑፍ የቀረጸበት መስቀለ ብርሃን አየ ምን ይሆን እያለ ሲያሰላስል የታዘዘ መልአክ መጥቶ እንዳየኸው ምስል አሠርተህ ያዝ ታሸንፈዋለህ አለው:: ከዘውዱ ጀምሮ እስከ ተራ የጦር ዕቃ ድረስ መስቀል አስቀረጸ:: ከዘህ በኃላ መክስምያኖስ መጣብህ ብለውት ቢገጥመው አቸንፎታል:: መክስም ያናስም ሲሸሽ የቴብር ወንዝ ድልድይ ተሰብሮበት ሰጥሞ ቀርቷል:: ከዘህ በኃላ ሮምን አንጾኪያን ጠቅልሎ የሚገዛ ሆነ በዓመቱም /በ313 ዓ.ም/ አብያተ ጣዖታት ይትዐጸዋ አብያተ ክርስቲያናት ይትራኑዋ ብሎ አዋጁን በአዋጅ መልሶታል::

ዕሌኒ ቀድሞ ልጅ ላለ ደገኛ ሃይማኖተኛ ይሆንላት ዘንድ ብፅዓት ገብታ ነበርና በዘሙሉ ቀን ሃይማኖት ስለቆመ ደስ ብሏት ብጽዓቷን ለመፈጸም በ327 ዓ.ም ኢየሩሳሌም ወርዳ መስቀሉን

ከተቀበረበት አስወጥታ አብያተ ክርስቲያናት አሠርታ በዓመቱ /በ328 ዓ.ም/ በዚህ ዕለት አርፋለች::

ጴጥቅላጥያናስና መክስምያኖስ በ305 /6/ ዓ.ም መንግሥታቸውን በፈቃዳቸው ለቀው ኦክ፣ ቈስጠንጢኖስም የተዋጋው በመክስምያኖስ ተተክቶ ከነበረ ሌላ መክስምየኖስ ነው የሚል ታሪክም ይነገራል::

ግንቦት 11 ቅዱስ ያሬድ

ያሬድ ማለት ሙራድ ማለት ነው:: ብሔረ ሙላዱ አክሱም ነው ትውልዱ ከዘርዐ ሌዋውያን ነው:: አባቱ አዳም እናቱ ታውክልያ ይባላሉ:: አባቱ ካህን ነበር የተወለደው በ505 ዓ.ም ነው ለትምህርት ሲደርስ ይስሐቅ ለሚባል መምህር ሰጡት ከሱ ፊደል አጥንቶ መዝሙረ ዳዊት ሊማር ለእናቱ ወንድም ለርሱ አጐቱ ወደ ሆኑት ወደ መምህር ጌዲዎን ሄደ አንዲት ቀለም እንኳ ሳያጠና ሰባት ዓመት ተቀመጠ::

አንድ ቀን ቀለም አጥፍቶ መምህሩ ተቆጥተው በበትር ገረፉት የፀብ አይደለም «ወኢትዘብጥ አሐደኒ ዘእንበለ ሕጻን በእንተ ትምህርት ወግተሣጽ ከመ በዝንቱ ይተዐቀብ» /ፍት.ነገሥ.11ክ1/ እንዲል ለተግሣጽ ነው:: ሽሽቶ ሲሄድ መንገድ አድክሞት ዋዕየ ፀሐይ ተሰምቶት ከዛፍ ጥላ ሥር ተቀመጠ:: ትል ዛፉ ላይ ለመውጣት ሽታ ሰድስት ጊዜ እየወጣች ስትወድቅ በሰባተኛው ወጥታ ስትሄድ አየ እኔስ እስከመጨረሻ ብተጋ ትምህርቴ ይገለጽልኝ የለምን ብሎ ተመልሶ መመህሩን ይቅርታ ጠየቀ ከዚህ በኃላ ጌታ ጎሊናውን ንጹሕ ልቡናውን ብሩህ አድርጐለት ባንድ ቀን ብሉይ ሐዲስ ወሰኖ ተገኝቷል::

ከጊዜያት ባንዱ ጌታ ሶስት አዕዋፍ ከገነት ልከለት በቃል ሰብአዊ ሲያነጋግሩት ተመስጠ መጣበት ጌታ በመንበረ ጸባያት ሆኖ በቃለ አቅርንት በስብሐተ መላእክት ሲመሰገን ሰማ:: ጻጻሱ ንጉሥ ካህናቱ መሳፍንቱ ለጸሎት ተሰብስበው ሳሉ በሶስት ሰዓት ከመላእክት የሰማው ተገልጸለት ሃሌ ሉያ ለአብ ሃሌ ሉያ ለወልድ ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ ቀዳሚሃ ለጽዮን ሰማየ ሣረረ ወበጸግም አርአየ ለሙሴ ዘከመ ይገብር ግብራ ለደብተራ ብሉ

በዚግ አመስገኗል:: ከዚያ በፊት በዚግ ምስጋና የለም ኦክርና ሁሉም ተደንቀው ሲሰሙት ውለዋል:: ይህን ድርሰቱንም ከአርያም የሰማሁት ነው ሲል አርያም ብሉታል:: በሚያዜምም ጊዜ ያለፈ ያገደመው የወጣ የወረደው ሁሉ በተመስጠ ይሰማው ነበር:: አዕዋፍም ከቡር ንዑድነቱን አውቀው ማዕየ ፀሐይ እንዳይሰማው በክንፋቸው ይጋርዱት ነበር::

ንጉሥ ዐጼ ገብረ መስቀል ከፍቅር የተነሣ ከቤተመንግሥታቸው ያናሩት ነበር አንድ ቀን ከፊታቸው ቆሞ ሲያሰማቸው ተመስጠው ላይታወቃቸው በያዙት ጦር እግሩን ወጉት እሱም በተመስጠ ያደርስ ነበርና ሰጊዜው አልታወቀውም ኋላ ግን ተሰማው የደምህን ካሳ ምን ልስጥህ አሉት ወርቅ ብር አልሻም ወደ ገዳም እንድሄድ ያሰናብቱኝ አላቸው:: መለየቱን ባየውዱም ስመ እግዚአብሔር ጠርተው ምለውለት ነበርና አሰናበቱት:: ወደቤተክርስቲያን ገብቶ እጁን በታቦተ ጽዮን ላይ ዘርግቶ ቅድስት ውብዕዕት ስብሐት ወቡርክት ክብርት ወልዕልት አንቀጸ ብርሃን ማዕረገ ሕይወት የሚለውን የእመቤታችንን ምስጋና ንባቡንና ዜማውን ሰተት አድርጉ ተናግሮታል:: በዚህም ጊዜ አንድ ከንድ ያህል ከመሬት ከፍ ብሉ ታይታል:: ከዚህ በኋላ ደቀመዛሙርቱን አስከትሉ ተከዚን ተሻግሮ በጸለምት ከገዳማተ ሰሜን በአንዱ በጸም በጸሉት ተወስኖ ኑሮ በዚህ ዕለት ዘገብረ ተዘካርየ ወተዝካረ ጌዲዎን መምህርየ ወተዝካረ አዳም አቡየ ምንት እንከ አስቡ ብሉ ጌታን ጠይቆ ጌታም በተስፋህ ያመነውን በቃል ኪዳንህ የተማጸነውን እስከ 10 ትውልድ ድረስ ምሬልሀለሁ ብሉ ተስፋውን ነግሮት ተሠውሯል::

የድርሰቱንም ነገር ከዚህ ይናገሩታል:: የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች አምስት ናቸው እነርሱም ድጓ፣ ጸመ ድጓ ፣ምዕራፍ፣ ዝማሬና መዋሥዕት ናቸው::

1. ድጓ - እስትግቡዕ /የተሰበሰበ/ ማለት ነው:: ከብሉይም ከሐዲስም ከአዋልድም ይጠቅሳል፣ የጌታን የእመቤታችንን፣ የነቢያት የሐዋርያት የጻድቃን የሰማዕታትን ክብር ይናገራልና ድርሰቱን በዮሐንስ ጀምሮ በዮሐንስ ፈጽሞታል:: ዓለም በዘመነ ዮሐንስ ተፈጥራ በዘመነ ዮሐንስ ለማለፏ ምሳሌ ነው:: ዮሐንስ፣ አስተምህሮ፣ጸመድጓ፣ ፋሲካ ብሉ በአራት ዐበይት ክፍሉች ከፍሉታል:: በአራቱ ፀወርተ መንበር በአራቱ ወንጌላውያን ምሳሌ ለዚህም በ22 ስነፍጥረት አምላል 22 አርእስት ሰጥቶታል::

ከእነዚህም 12ቱ ምልጣን አላቸው 10 ሩ ግን ምልጣን የላቸውም ምልጣን ያላቸው «ብገዙኑ ውተላዝኑ» የተባሉ የሕጋውያን፡ ምልጣን የሌላቸው በተፈጥሮአቸው ፀንተው የሚኖሩ የደናግል ምሳሌ ነው።

2. *ጸሙ ድጋ* በዐቢይ ጾም የሚደርስ ነው ዘወረደ፣ ቅድስት፣ ምኩራብ፣ ደብረ ዘይት፣ ገብር ኄር፣ ኒቆዲሞስና ሰሙነ ሕማማት ተብሎ በስምንት ተከፍሏል።

3. *ምዕራፍ ፓሬፊያ* ማለት ነው የደረሰው በጠለምት ነው ምዕራፍ ዘዘወትር ምዕራፍ ዘዐቢይ ጾም፣ ብሎ በሁለት ከፍሎታል መሠረቱ መዝሙረዳዊት ሲሆን በውስጡ ብዙ ንዑሳት ክፍሎች አሉ።

4. *ዝማሬ* ምስጋና ማለት ነው። ዝማሬና መዋሥዕትን በደቡብ ጉንደር ዙር አባ በሚባል ቦታ ደርሶታል። ጎብስት፣ ጽዋዕ፣ መንፈስ፡ አኩቴትና ምሥ ጢር ብሎ በአምስት ከፍሎታል። አምስት ክፍል መሆኑ ጎብስት ሥጋውን ጽዋዕ ደሙን ያመለክታልና የአምስቱ አዕማደ ምሥጢር የአምስቱ ቅንዋት ምሳሌ ነው።

5. *መዋሥዕት* - ምልልስ፣ ሰዋሰወ ነፍስ፣ ማለት ነው ለአዕርጎ ነፍስ በፍትሐት ጊዜ የሚደርስ ነውና ያስ ይሁን ለሙት ድርሰት ደርሶ ማዘንን ከማን አግኝቶታል ቢሉ ከዳዊት ይላል። ዳዊት ለሳኦልና ለናታን ግጥም ገጥሞ አልቅሶላቸዋል። 1ኛ ሰሙ 1: 17- 27 በዘመነ ሐዲስ ስም ዮሐንስ

ኤጲስቆጶስ ዘዳግስቆ ለሞተ ሰው ድርሰት እያደረሰ ያዝንላቸው ያለቅስላቸው ነበረ ድርሰቱ ግን የኔማ ጀግናው የኔማ ሳተናው ሽሽ ተበላሽ የሚል ሳይሆን በሞቱ ሞትን ያጠፋ ጌታ አምላክ ከሞተ ነፍስ ክርዳቱ ገሃነም

እንዲያድነው ለሕይወት እንዲያበቃው የሚለምን ጸሎት ነው።
እስከ ድረስ የተገለጹት ድርሰቶቹ አምስቱ ጸዋትወ ዜማ በመባል ይታወቃሉ።
ከዚህ ሌላ የውዳሴ ማርያም፡ ቅዳሴ ማርያም ምን ዜማ የደረሰ እሱ ነው። ማይኪራህ በሚባል ቦታ ሳለ እመቤታችን ቅዱስ ኤፍሬምን ከቂሳርያ አባ ሕርያቆስን ከብህንሳ በደመና ጠቅሳ እርሱ ካለበት አምጥታ አንተ ውዳሴዬን አንተ ቅዳሴዬን ነግራችሁት በዜማ ያድርሰው ብላቸው ነግረውት ውዳሴዋን ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ያለውን በአራራይ የእሑድን በዕዝል፣ቅዳሴዋን በግዕዝና በዕዝል፡ አድርሶታል። ከዚህም አያያዙ 13 ቀን ቅዳሴያት ሁሉ በዜማ አድርሷል። ቅኔንም አመልቶ አስፍቶ ባይናገረው እንጂ ደራሲው እርሱ ነው። ዜማውም ሶስት ዓይነት ነው፤ ግዕዝ ዕዝል አራራይ፣ ግዕዝ የአብ ዕዝል የወልድ አራራይ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው።



ወልደ አምላክነት የእመቤታችንን ወላዲተ
ቤታችንን ወላዲተ አምላክነት ይነቅፍ ነበርና
አምላክን የወለደች ብትሆንስ ለሴቶች ይህን የደም
ቸው ነበር ብሎ ዕርቃኗን አስቅሎ ክርስቶስን
ላክ ድንግል ማርያምንም ወላዲተ አምላክ የሚል
ኢያላችሁ ትፋጠት አለ። እየሄዱ ይተፋጠት ጀመር።
ሉንስ ጠርዘቤጠር» ይላል ዮሐንስ ከዚያ ቁሞ ነበረ
እኔስ ወልደ እግዚአብሔር እንዲህ ባለግዘፀን
ቱም ድንግልና እንደተወለደ አምናለሁ
እድፈት ሳያስጸይፈው የእመቤታችንን ንጽሕናና
አካሏን ቢሰም ከአፋ ላይ እንደ ወርቅ
በቤተ መቅደስ የነበረች ስዕለ ማርያምም
ህርቱ እንደማር የጣፈጠ ለከሀዲ ግዘቱ እንደ ጦር
የተሳለ በእውነት አፈወርቅ ልሳነ ወርቅ» ብላ
ስክራለታለች። «ሰበ ሰማ ኃፍረተ ትክት ቅድመ
ሱባዔ፣ ተአምረ ፍቅርኪ ያርኢ ወያስተጎፍር
ልኪ ለዮሐንስ ጽጌ ትንሣኤ፣ ወደስቶ ወአእኩተቶ
ጉባዔ፣ አፈወርቅ እንዘትብል ጊዜያተ ክልዔ።

ኢቃደ እግዚአብሔር በአንጾኪያ ሊቀጳጳስነት
ሣለ ብዙ ተግሣጻት ጽፏል ብዙ ድርሳናት
ርቃዲዎስ ይባላል። ወዳጁ ነው። ሊጠይቀው ሄደ
ን ሳገኝህ ነገሩ ይጠፋኛል ነገሩን ሳገኘው አንተን
ሲወጣ ሲወርድ የሚኖር ነገር አለ፣ ወንጌላዊ
አመ ትወልድ ወልደ ዘበኵራ የበኩር ልጂን
ቃትም» /ማቴ 1: / ያለው። ከወለደች በኃላ
በሚያውቁበት ግብር አውቋታል ማለት ነውን
ደለም ጌታን ጸንሳ ሳለች ሥጋዌው በብዙ ጎብረ
ት በብዙ ጎብረ አምላል የተመሰለለትን ጌታ
ከየቅ መልኳ እየተለወለጠ ይታየው ነበረ፣
ግን በአንድ ጎብረ መልክዕ ታይታዋለችና ስለዚህ
ለት በዚህም ጊዜ ከግድግዳ ላይ የነበረች ስዕለ
መጥታ ሦስት ጊዜ በራሱ ላይ ዞራ «ሠናየ
አፈወርቅ ዮሐንስ ልሳነወርቅ» ብላ አወድሳው

ከቦታዋ ተመልሳለች። ንጉሡም ለመታሰቢያ ሁለት ልሳናተወርቅ አሠርቶ በግራ በቀኝ አድርጎላታል።

በዚህም ላይ ንጉሡ አርቃዶስ ንግሥቲቱ አውዶክስያ ልጅ እየወለዱ ይሞትባቸው ነበርና ሴት ልጅ በወለዱ ጊዜ እንዳትሞትብን ብለው እርሱን አጥምቅልን አሉት ሲሄድ መልአከ ሞት ከመንገድ ተገናኘው ወዴት ትሄዳለህ? አለው። የአርቃዲዎስን ልጅ ነፍሷን ከሥጋዋ ለይተህ አምጣ ብሎኝ ላመጣ እሄዳለሁ አለው። ቆየኝ ላጥምቃት ብሎት ሄደ። ካጠመቃት በኋላ ረስቶት በሌላ መንገድ ተመለሰ። የካህናት የመዓረጋቸውን ደግነት ለማጠየቅ /17/ ወዲያ ወዲህ ሳይል 10 ዓመት ቆሞ ቆይቷል። «እምነ አፋሁ ዘወርቅ ሰሚአ ግዘተ፣ እንበለ ይዕርግ ላዕለ ወእንበለ ይረድ ታሕተ፣ መልአከ ሰማይ ቆመ ዐሠርተ ዓመተ» እንዲል እርኬ።

በአሥረኛ ዓመቷ ለባልታጨች ልጃችንን መርቀልን ብለው ላኩበት ቀድሞ በሄደበት መንገድ ቢሄድ መልአከ ሞትን ቆሞ አገኘው ። ምነው ከዚህ ቆመህል? አለው። አንተ ቆይ ካልከኝ ጊዜ ጀምሮ ወዲያ ወዲህ ሳልል ቆሜአለሁ አለው። አጥፍቻለሁ ሂድ የታዘዝከውን ፈጽም አለው። ከዚያ ሲደርስ ሞታ ሲላቀሱ አገኘ። ነገሩን ነግሮ አጽናኗቸው ተመልሷል።

ንግሥቲቱ አውዶክስያ መፍቀሪተ ንዋይ ነበረች። በዓመት 3 ጊዜ የምታፈራ ለከተማ ቅርብ የሆነ ርስት ያላት መበለት ነበረች ርስቷን ነጠቀቻት። መጥታ ለርሱ ነገረችው መልሺላት አላት አምለልስም አለች። ርስተ ምድር ነጥቀሽ ርስተ ሰማይ ታገኚ መሰለሽ? ብሎ ከቅጽረ ቤተክርስቲያን እንዳትገባ ሥጋውን ደሙን እንዳትቀበል ከምእመናን እንዳትገናኝ አወገዛት። እርሷም በበኩሏ እሱ በነውር ምክንያት የሻራቸውን ኤጲስ ቆጳሳት በብሶባ ታሥሮ ይጋዝ ብለው እንዲፈርዱበት አደረገች። ታሥሮ ወደ ደሴቶ አጥራክስያ ተጋዘ። የሮሙ ንጉሥ አርያኖስ ዜና ገድሉን ስነ ጽድቁን እየሰማ ሲያደንቅ ይኖር ነበርና ባትመልሰው ጠቤ ካንተ ነው ብሎ ከአርቃዴዎስ ላከ። መልሱ ብሎ አስመለሰው ያች ግን ሰይጣን አነሣስቷታልና ሁለተኛ አሥራ አጋዘችው በዚያው አርፏል። እሷም አልተጠቀመችም እሱ ካረፈ በኋላ ጽኑ ደዌ አደረባት። ከመቃብሩ ሄዳ ቢድያለሁ ይቅር በለኝ እያለች ብዙ መከራ ተቀብላ ተፈውሳለች።

ዮሐንስ አፈወርቅ ሲቀደሰላት
ጠሪብ ተጋራሚ ምሁር ደግ አባት።
እውነተኛ መምህር ፊት አይቶ አያደላ
ንግሥትን ገሠጻት ደጋዋን በድላ።
በእግዚአብሔር ፊት ብትከብርላት ነፍሱ
ሰማያዊ መልአክ ታዘዘለት ለርሱ።
ቃሉ የጣፈጠ ትምህርት እሙን
አቃተሉ ፈቺው መናፍቃንን።
በዘንፍ መሀል አንጻች ላያፍር

ቀሞ ሲመክር የድንግልን ክብር
ድንግል በሥዕሏ አድራ በቀንዱው
አፈወርቅ ብላ አመደበችው
አንባይቀየሙት ነገሥት መነኮንት
ሰምቶ ቸል ከሚል የደጋን ጩኸት
ገሬዎችን ሁሉ ገሥጾ በእውነት
ደኻለኛል አለ መኖር በከንቱ
ጌታ እንዳልጉዳ እውነትን ተርቤ።
የቀናውን መንፈስ አላድሮ በአዲ።

አባ አፍኒ - /ከዘጠኙ ቅዱሳን/

ሐ. ፍልሰተ ሥጋሁ ለአቡነ ማር ተክለሃይማኖት

ዜና ዕረፍታቸው በገጽ እንደተገለጸው ጌታ በ57 ዘመን ደቀመዛ መዛሙርትህ ቤተክርስቲያን እንጸው ሥታህን ወደዚያ ያልፈሱታል። ብሉ ብሉ ነገሯቸው ነበረ። ጊዜው ሲደርስ 19 ቀን ለአቢ ምሌት ለአባ አባ ሕዝቅያስ ተገለደው ጌታዬ የነገረኝ ተሰፋ ሊፈጸም ጊዜው ደርሷልና በሩትም
በቅርብም ያሉ ደቀመዛሙርቴን ሰብስበህ በ12 ሥጋዬን አሳልሱ፣ እኔም ከቅዱስ ሚካኤል ጋር እመጣለሁ፣ ምልክት ይሆንህ ዘንድ ሰትገባ መብራቶቹን አጥፋ እኛ ስንመጣ ይበራል አሉት። እንዳሉትም ደቀመዛሙርቶቻውን ከሩትም ከቅርብም ሰብስቦ በዚህ ዕለት ሥጋቸው ካረፈበት ከመካነ አስቦ ቢዝሙ እንደ ሸቱ መጓዙ እምር አገኙተው ተሸክመው ወደ ቤተመቅዱስ ከቅዱስ ሚካኤል ጋራ መጥተው ከመንበሩ ተቀመጡ፣ ሲመጡም የጠፋት መብራቶች በሮተው ተገኝተዋል እኒያም በዕልልታ በደስታ አጽግቸውን ከእግረ መንበር አትረውታል።
ታሪኩ የተፈጸመው በ1349 ዓ.ም ቀን ነው።

ግንቦት 14 አባ ጳኩሚስ /ከ290 - 346 ዓ.ም/

ሀገራቸው ጽርዕ ነው። በገጻመ ጳውናስ በ 6 ሺህ መነኮሳት ተሹመዋል። ቀን ለማስተማር ለአገልግሎት ሌሊት ለበጊድ ለጸሎት ታግተው ይኖሩ ነበርና ሱታፌ ግንበረ መላእክት ተብለዋል። በጸሎታቸው ጥቂት ትምክህት ነበረባ ቸው። አንድ ሌሊት ሲሰግዱ

ላባቸው የቆሙበትን ምድሮ አራሰው ጌታ ተገልጾ አሁን ይህ ሁሉ ስግደት ይህ ሁሉ አሉት' ለማን ብለህ ነውሕ አላቸው ጌታዱ ላንተ ብዱ ነዋ አሉት በማግሥቱ በችንካር ተቸንክር በመስቀል ተሰቅሉ ታያቸው:: ጌታዱ አሁን ደግሞ መስቀልህ ለማን ብለህ ነውሕ አሉት ላንተ ብዱ ነዋአላቸው:: ይህ ሁሉ ትናንት በተናገርኩት አይደለምን ደግ አላደረግሁም ብለው ተጸጽተዋል:: በሚጸልዩም ጊዜ ሽትና ሲኦል በዓይነልቡና ይታያቸው ነበር አንድ ቀን ባያቸው በወደድሁ ነበር አሉ:: የታዘዘ መልአክ ነጥቆ ወስዶ ጻድቃንን በሽት ሲያመሰግኑ ኃጠ ኣንን ሰሚአል ዋይ ዋይ ኪሉ አላያቸው:: ከዚህ በኋላ መላ ዘመናቸውን ስለኃጥአን ሲያዝኑ ሲያለቅሱ ኖረዋል:: ጊዜ ዕረፍታቸው ሲደርስ ጌታ ጎዘንህን አየሁልህ ልመናህንም ሰማሁልህ በስምህ የተማጸነውን ሁለ ከሞተ ነፍስ ከርደቱ ሸነም አድንልሃለሁ ብሉ ተስፋቸውን ነግሯቸው በዚህ ዕለት ወርዷል::

ግንቦት 16 ኢያሱ ሲራክ

ኢያሱ ማለት መድኃኒት፣ ሲራክ ግለትም ጠቢብ ግለት ነው:: ሲራክ የጥበብ ስሙ ነው አባቱ አልዓዛር ይባላል:: መጽ ሲራ 5:1 ጌታ ጥበብ ገልጾለት የጥበብ ሁሉ መገኛዋ ክእግዚአብሔር ዘንድ ነው ዓለም ሳይፈጠር ጥበብ ከርሱ ጋር ነበረች ብሉ ስለጥበብ ተናግሯል:: ሲራ 1:1 ከመሳፍንት ሙሴን ከነገሥታት ዳዊትን ከነቢያት ኢልያስ ኢልሳዕና ኢርምያስን አብነት እያደረገ ታላቅ የጥበብና የምክር መጽሐፍ ጽፏል መጽሐፉም ከ 46ቱ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አንዱ ነው::

ከሦርክ መልስ ከ 470 ዓ/ዓ ወዲህ የተነሣ መሆኑን መጽሐፉ ያመለክታል

ግንቦት 17 ኢጲፋንዮስ ኢጲስቆጶስ /ከ 315 - 403 ዓ.ም/

ወላጆቹ አይሁዳውያን ነበሩ አባቱ ሞቶ እናቱ እርሱንና እኅቱን የምታሳድግበት አጥታ ስትቸገር እርሱ ያላቸውን አንድ አህያ ሊሸጥ

ይዞ ሲሄድ ከጎዳና ፊላታዎስ የሚባል ደግ ሰው አገኘው:: ዋጋውን ሊነጋገረው አህያው ዘሎ ኩላሊቱን ረገጠው ፣ ወደቀ ፊላታዎስ የክርስቶስ ኢየሱስን ሰም ጠሮቶ ቢጎትተው ተነሣ:: አህያውንም ውደቅ ቢለው ወድቆ ቀረ:: ኤጲፋንዮስ በስሙ የወደቀውን የምታነሣበት የቆመውን የምትጥልበት ኢየሱስ ማነው? አለው:: ኢየሱስማ ለቤዛ ብዙኃን ከሰማያት ወርዶ ከድንግል ተወልዶ ዕውር ቢያበራ ሙት ቢያስነሣ ወገኖቹ አይሁድ ጸልተው ተመቅኝተው ሰቅለው የገደሉት አምላክ ወልደአምላክ ነው:: አለው ይህን በልቡ አኑሮ ባየው እየተደነቀ ወደ ቤቱ ተመለሰ::

ከዚህ በኋላ ባለጸጋ አጉት ነበረው እሱንም እኅቱንም ወስዶ አሳድጎ ሀብቱን አውርሷቸው ዐረፈ:: አንድ ቀን ከአባ ሉክዮስ ጋር በመንገድ ተገናኝተው እየተጨዋወቱ ሲሄዱ አንድ ችግረኛ ስመ እግዚአብሔር ጠራባቸው:: አባ ሉክዮስ ወርቅ ብር የለውምና የለበሰውን አውልቆ ሰጠው:: ወዲያው መልአክ ከበረዶ የነጻ ልብስ ሲያሳናጽፈው አይቶ አባቴ አምላክህን አመልከው ዘንድ ሃይማኖትህን አስተምረኝ አለው:: አስተምሮ አጥምቆታል:: ከፍጹምነትም እንደሚደርስ አውቆ መዓርገ ምንኩስና አሰጥቶታል በዚህ ጊዜ የ17 ዓመት ወጣት ነበረ:: ከዚህ በኋላ በጾም በጸሎት ተወስኖ በትጎርምት የሚኖር ቢሆን ሀብተ ፈውስ ተሰጥቶት ሕመማንን የሚፈውስ ሆኗል፣ ሙትም አንሥቷል::

መምህሩ አባ ኤላርዮን መንፈስ ቅዱስ ገልጾለት ጌታ የብዙኃን አባት እንድትሆን መርጦህልና፣ ቆጵሮስ ሂድ ተሾምልን ቢሉህ አይሆንም አትበላቸው አለው:: ከበዓቱ መውጣቱን ከመምህሩ መለየቱን ባየወድም ፈቃደ እግዚአብሔር ነውና ሁለት ብላቴኖች አበሰጥሎ ሄደ:: ጌታም ለቆጵሮሱ ኤጲስቆጶስ ሁለት ብላቴኖች ያስከተለ ሁለት የወይን ዘለላ የያዘ ኤጲፋንዮስ የሚባል ገዳማዊ ወደ ገበያ ይመጣል አሱን ሹመው አለው:: ቢሄድ ሁለት የወይን ዘለላ ይዞ ሁለቱን ብላቴኖች አስከትሎ ሲገበያይ አገኘው ኤጲፋንዮስ የምትባል አንተ አይደለህምን አለው:: አዎን አለ ጌታ ያዘዘኝ አለና ተከተለኝ ብሎ ወስዶ ሾመው:: በሶስተኛው ቀን ቅስና ሰጠው ኋላም እርሱ ሲሞት ኤጲስቆጶስነት ተሹሟል:: ተሹሞም ላለ ብዙ ድርሳናት ደርሷል ብዙ ተሣሣጻት ጽፏል::

ንግሥቲቱ አውዶክስያ የአንዲት መበለት ርስት በመንጠቋ ምክንያት የሐንበ አፈሠርቅ አውግዞ ከማኅበረ ምእመናን ለይድት

ነፍርና የሃይማኖት ሕጸጽ ሳይኖርብኝ በክንቱ አመግኖልና መተተህ እይልኝ ብላ ላከችበት ሄደ ተይ ያለሽን ተዪው አላት ይህንንስ አልተውም አለች እንግዲያውስ የሺቀጳጳሱን ቃል ልታከብሪ ፈተንሽ ነፍር አላት ይህንን ካልኮነ አብያተ ክርስቲያናትን አዘግቼ አብያተ ጣያታትን አስከፍታለሁ አለችው:: ከርሱ ዘንድ ሄዶ ወንድሜ ጥቂት ጊዜ ምእመናን ከመከራ አረፉ ስንል በዚህ ምክንያት ደግሞ መከራ ቢመጣው ደግ ነውን ተውው አለው:: ርስተ ምድር ነጥቃ ርስተ ሰማይ ታገኛለችን አይሆንም አብያተ ጣአታትንም ብታስከፍት ለርሷ ይበሳታል አለ::

ተመልሶ ከንጉሥ ሊሰናበት በጣ ጊዜ ኤሊፋንዮስ ዮሐንስ አፈወርቅን ከሹመቱ ሻረው ከመንፈሩ አዋረደው ብላ በሐሰት አስወራች:: ዮሐንስን ሊሰናበት ሲሄድ ምነው እንዲህ አደረግኸኝ? አለው ኧረ ምንም አላደረግሁብህም አለ:: መሄድማ ትሄዳለህ ከመንበርህ ግን አትቀመጥም በመንገድ ትሞታለህ አለው:: እርሱም በዘኩሉ መመለስማ አይቀርም ትመለሳለህ ነገር ግን ሁለተኛ ተግዘህ ትሞታለህ አለው:: የጠብ አይደለም የዮሐንስ ሞት ለኤሊፋን ዮስ የኤሊፋንዮስ ሞት ለዮሐንስ ተገልጸላቸው ነው እንጂ ይኸውም አልቀረ ዮሐንስ አፈወርቅ በዕርቅ ከተመለሰ በኋላ ሁለተኛ ተግዞ በዚያው ዐርፏል:: ኤሊፋንዮስም ጥቂት ቀን ተጉዞ ሳይደርስ ከመንገድ በዚህ ዕለት ዐርፏል:: 11 ቀን ተጉዘው በ28 ደራሱ፣ በሃይማኖት ሕጸጽ በሞግባር ጻጎዕ የሻራቸው ሁለት ዲያቆናት አናስቀብርም ብለው መቃብር ከልከለውት 40 ቀን ተቀመጠ ይህንንም ያህል ቀን ሲቆይ መዓዛው አልተለወጥም ነበር::ኋላ ግን አንድ ዲያቆን ቢማጸነው እኒያን በተአምራት አጥፍቶ ተቀብሯል::

ክቡር መንፈሳዊ ኤሊፋንዮስ
ታማኝ ባለሟሉ ለመንፈስ ቅዱስ
ገና በልጅነት በሠጣትነቱ
በዘጊድ ተቀጣ በደም ሰውነቱ
ልጓደትን አብዝቶ ቢገልም ጉልበቱ
ያሬዛቸው ነበር ሕዝቡን በስብከቱ
አምላኩ ክርስቶስ ነውና ብርታቱ::
ከሞተ በኋላ ሥጋው ሆኖ በድን
ጻድቃን የመሰሉ ተንኪዛዎችን
ተጣቸው ለሕዝቡ ትምህርት እንዲሆን
ፈጣሪ ተጣልቶን እንዳንሆን እኩል
አደብጀንምና ይቅርብን ተንኪል

ምሳ 10 :29 ፣ 12: 2

ግንቦት 18 በዓለ ጲራቅሊጦስ

ጌታ ዐሚያረግ ጊዜ ደቀመዛሙርቱን አንትሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢያሩሳሌም እስክ ትለብሱ ኃይለ እምአርያም ሉቃ 24:49 ብሏቸው ዐርጎ ነበር:: ተስማሮ የማያስቀር ምሉ የማይከዳ ነውና ባረገ በ10ኛው ኪተኃሣ በ50ኛው ቀን ጲራቅሊጦስን ሰደሳቸዋል::

ጲራቅሊጦስ ማለት መንፈስ ጽድቅ መንፈስ ሕይወት ባሕርያዊ እስትንፋስ እካዛዊ ሕይወት አካላዊ እስትንፋስ ማለት ነው ስለምን ቆይቶ በ10ኛው ቀን ላከላቸው ቢሉ በ10ኛ መዓረግ የጠነን እኛ ነፍርንና ወደ ክብራችን ወደ መዓረጋችን እንደመለስን ለማጠየት ነው ዳግመኛም 10ሩን ቃላት ቢጠብቁ መንፈስ ቅዱስ ኮሚሰጥ መሆኑን ለማጠየት ነው::

"መአስተርአይምሙ ልሳናተ እሳት ከፉሳት ከመ እሳት ዘይትከፈል" ይላል በአምላለ እሳት አድርባቸዋል:: ወዲያውም የሚያውቁት ጸንቶላቸው የማያውቁት ተገልጸላቸው ቀድሞ ኮሚናገሩት ከዕብራይስጥ ቋንቋ ሌላ 71 ቋንቋዎች ተገልጸውላቸው ምሥጢር የሚተረጉሙ ሆነዋል:: ከአይሁድ ወገን እኩሌቶቹ ይህ ነገር ምን ይሆን? አሉ እኩሌቶቹ "እስብ ጻዕፈ ጸግቡ - ጉሽ ጠጅ ጠጥተው ሰክረው የሆነ ያልሆነውን ይቀባጥራሉ "አሉ:: ቅዱስ ጴጥሮስ ሀሣባቸውን አውቆ አኮ ከመትትሐዘብሙ አንትሙ ስኩራን እሙንቱ ዘትበሉ ሰክረዋል የምትሉ እናንተ እንደምትጠረጥሯቸው አይደለም እስመ ነግህ ብሔሩ ወሰቢሁ ሠለስቱ ሰዓት - ጊዜው ግለጻ ሰዓቱም ሶስት ሰዓት ነውና፣ ጻሩ ግን እሰወጥ እምነመንፈስ የ ጲበ ኩሉ ዘሥጋ (ኢዩ 2: 28) ተብሎ የተነገረ ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ይህን ያደረገ እናንተ ጸልታቸሁ ተመቅኝታችሁ የሰቅላችሁት ክርስቶስ ኢየሱስ ነው እኛም ነቢያት ትንቢት የተናገሩለት ምሳሌ የመሰሉለት አምላክ መልደ አምላክ ለመሆኑ፣ ከሙታን ተለይቶ ለመነሣቱ ለማረጉ ዳግመኛም በክብር በምስጋና ለመምጣቱ ምስክሮች ነን አላቸው ምንተ ንግበር አኃዊነ አውን ምን እናድርግ አሉ "ነስሑ ወተጠመቁ በስሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ከክፋታችሁ ተመልሳችሁ በስሙ ተጠመቁ አሏቸው "ወተመስኩ በይእቲ ዕለት መጠነ ሠላሳ ምዕት ነፍስ " ይላል ሶስት ሺህ ሕዝብ አምነው ተመ

ምቀዋል:: ሐዋ 2:1-41 ይህ የተፈጸመ በ33 ዓ.ም በዚሁ ቀን በዕለተ እሑድ ነው:: ዕለቱን ሊቃውንት ሀብተ መንፈስ ቅዱስ የተሠጠበት፣ ወደ የሀገራቸው በተመለሱ ጊዜ በአሕዛብ መካከል የሚያስተዋውቋትንና የሚመሰክሩላትን 3000 ምእመናን ያገኘችበት ዕለት ስለሆነ የቤተክርስቲያን የልደት ቀን ሲሉ ጠርተውታል::

4. ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ እመቤታችን ከሌሎች ቅድሳት አንስት ጋር አብራቸው ለጸሉት ትዕ:ጋ ነበር ሐዋ 1:14፤2:1